የከተሞችን አቅም ለማሳደግ
የሚተገበረው መርሀ ግብር
ገጽ 10

ወስኖ ራስን መለወጥ!
ገጽ 11

ቅድመ ምርመራ-
የማህፀን በር ጫፍ ካንሰርን ለመከላከል
ገጽ 12

ኢፕድ
# አዲስ ዘመን
83ኛ ዓመት ቁጥር 166 የካቲት 16 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ቅዳሜ
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!






# የሐዋሳና የጅማ አዳዲስ የደረቅ ወደብ ተርሚናሎች ግንባታ በመጋቢት ወር ይጀመራል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- የሐዋሳና የጅማ አዳዲስ የደረቅ ወደብ ተርሚናሎች ግንባታ እስከ ቀጣዩ የመጋቢት ወር መጨረሻ ድረስ እንደሚጀመር የኢትዮጵያ ባሕር፣ ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አስታወቀ፡፡

ለሁለቱ ደረቅ ወደቦች ለመጀመሪያ ዙር ግንባታ 300 ሚሊዮን ብር ተመድቧል።

በኢትዮጵያ ባሕር፣ ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ የወደብና ተርሚናል አገልግሎት ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ ምህረትአብ ተክሉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ድርጅቱ ከማስፋፊያ ግንባታዎች በተጨማሪ አዳዲስ የደረቅ ወደብ ተርሚናሎችን ግንባታ እያከናወነ ይገኛል፡፡

በሐዋሳና በጅማ ሁለት አዳዲስ የደረቅ ወደብ ተርሚናሎች ግንባታን እስከ መጋቢት ወር መጨረሻ ድረስ ለመጀመር ዝግጅት ተደርጓል ያሉት አቶ ምህረትአብ፤

የሐዋሳና የጅማ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




# «ኢትዮጵያ የምትታወቀው የሱማሊያን ጨምሮ የጎረቤቶቿን ሰላም ለማስከበር መስዋዕትነት በመክፈል ነው»

- ካፒቴን መርሻ ግርማ
የቀድሞ የኢትዮጵያ ባሕር ኃይል አመራር

**አስቴር ኤልያስ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ የምትታወቀው የሶማሊያን ጨምሮ የጎረቤቶቿን ሰላም ለማስከበር መስዋዕትነት በመክፈል ነው ሲሉ የቀድሞ የኢትዮጵያ ባሕር ኃይል አመራር ካፒቴን መርሻ ግርማ አስታወቁ፡፡

ካፒቴን መርሻ፣ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት

«ኢትዮጵያ የምትታወቀው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - በረሀን ታደሰ

# አውደ ርዕዩ ኢትዮጵያ ለዓለም ሰላምና ለጥቁር ሕዝቦች ነፃነት የከፈለችው ዋጋ በጉልህ የታየበት ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- አውደ ርዕዩ ኢትዮጵያ ለዓለም ሰላምና ለጥቁር ሕዝቦች ነፃነት የከፈለችው ዋጋ በጉልህ የታየበት መሆኑን የዲፕሎማሲ ሳምንት አውደ ርዕይን የጎበኙት

አውደ ርዕዩ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ጉዳት ለደረሰባቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች አራተኛ ዙር ሰብዓዊ ድጋፍ ተጀመረ

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋ ጉዳት ለደረሰባቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ የሚሆን አራተኛ ዙር ሰብዓዊ ድጋፍ እየተጠናቀቀ ባለው ሳምንት መጀመሩን የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ገለጸ፡፡

የኮሚሽኑ የሕዝብ ግንኙነት ከፍተኛ ባለሙያ አቶ አታለለ አቡሀይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ለትግራይ ክልል 15 ወረዳዎች የሚሆን ከ27 ሺህ በላይ ኩንታል ምግብ ነክና አልሚ ምግቦች ከድሬዳዋ መጋዘን ወጪ ተደርጎ ተጓጉዟል፡፡

በሦስተኛ ዙር ድጋፍ ከፍተኛውን ወጪ የሸፈነው መንግሥት እንደነበር ጠቁመው፤ በአራተኛ ዙር ድጋፍ

ጉዳት ለደረሰባቸው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል










አቶ ካሳሁን ፍልፍሉ

# ክልሉ

## የልማትና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን ለመመለስ እየሠራ መሆኑን አስታወቀ

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የልማትና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን በፍትሐዊነት ለመመለስ በሚያስችል መልኩ እየሠራ መሆኑን የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል አስታወቀ፡፡

የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ጽሕፈት ቤት የመልካም አስተዳደርና አካባቢ ጉዳዮች ኃላፊ አቶ ካሳሁን ፍልፍሉ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ከዜጎች ጋር በቅርበት በመወያየት አቅም በፈቀደ መጠን የልማትና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን በፍትሐዊነት ለመመለስ እየተሠራ ነው፡፡

በክልሉ ከሕዝብ ጋር የተጀመሩ ውይይቶች ሰፍተው እስከ ገጠር ቀበሌዎች እንደሚወርዱ የጠቆሙት አቶ ካሳሁን፤ በሕዝብና በመንግሥት መካከል አለመግባባቶች ካሉ ውጤታማ ሥራ ለመሥራት አዳጋች ስለሚሆን በየተቋማቱ ያሉ የመልካም አስተዳደር ችግሮች ተቆጥረው መታወቅና ምላሽ ማግኘት አለባቸው ብለዋል፡፡

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ከተደራጀ በኋላ ለብዙ ዘመናት ይነሱ የነበሩ የአደረጃጀት ጥያቄዎች ምላሽ እንዲያገኙ በማድረግ በልማት ሥራዎች ላይ ማተኮር አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት የተለያዩ አካባቢዎችን በዞን የመደራጀት ጥያቄዎች በሙሉ እንዲመለሱ መደረጉንም አንስተዋል፡፡

የመንግሥት አሠራር ለሕዝብ ግልጽና ተጠያቂነትን የሚያሰፍን መሆን እንዳለበት የሚገልጹት አቶ ካሳሁን፤ የመልካም አስተዳደር ችግር የማይገባበት ቦታ የለም ሲሉ ጠቅሰዋል፡፡

ተቋማት በልማት ፍትሐዊነት፣ በሥልጣን ክፍፍል፣ በአገልግሎት አሰጣጥ ላይና በሌሎችም ጉዳዮች የእቅዳቸው አካል ሊያደርጉት ይገባል ብለዋል፡፡

ችግሮችን ነቅሶ አውጥቶ እልባት በመስጠት ዜጎች ተረጋግተው ከመንግሥት ጋር በመሆን ልማትን እንዲያሳልጡ እየተሠራ ይገኛል ሲሉም አክለዋል፡፡

የመንግሥት ተቋማት በውስጣቸው ከሚያስተዳድሯቸው ሠራተኞች ጀምሮ ቅሬታዎችን በማዳመጥና በግልጽ በመወያየት ችግሮችን መፍታት አለባቸው የሚል መርህ ተይዞ እየተሠራ እንደሚገኝም አመላክተዋል፡፡

ክልሉ ከኬንያ ጋር በሚዋሰንባቸው አካባቢዎች በአርብቶ አደሮች ላይ የሚደረጉ ትንኮሳዎች እንዲሁም ከብት የመነጣጠቅና ከድንበር ጋር የተያያዙ የተለያዩ አለመግባባቶች መኖራቸውን ጠቁመው፤ በሀብት ምክንያት የሚፈጠሩ አለመግባባቶች ወደአላስፈላጊ መቃቃር አምርተው የንብረት ውድመትና የዜጎች መፈናቀል እንዳይከተል በሰላም መፍታት በሚቻልባቸው ጉዳዮች ላይ እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በ12 ዞኖች 32 ብሔር ብሔረሰቦችን ያቀፈው የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በይፋ የተመሠረተው በ2015 ዓ.ም ማገባደጃ ላይ ነው፡፡

# ኢትዮጵያዊነትን በልኩ ከፍ ለማድረግ ኪነጥበብን መጠቀም ያስፈልጋል

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያዊነትን በልኩ ከፍ ለማድረግ ኪነጥበብን በመሣሪያነት መጠቀም እንደሚያስፈልግ የአዲስ አበባ ባህል ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ሂሩት ካሳው (ዶ/ር) ተናገሩ፡፡

«ኢትዮጵያዊነት የኪነጥበብ ሠረገላ የወል ትርክት አለላ» በሚል መሪ ሃሳብ እየተካሄደ የሚገኘው 15ኛው ከተማ አቀፍ የኪነጥበብ ፌስቲቫል መክፈቻ በጊዮን ሆቴል መስከ ትናንት ተጀምሯል።

መርሐግብሩን በንግግር የከፈቱት የቢሮ ኃላፊዋ፤ ኢትዮጵያዊነትን ለማፅናት፣ ይበልጥ ለማነፅ እንዲሁም ሀገርን ወደ ብልፅግና ለማሻገር የኪነጥበብ ሚና ከፍተኛ ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያዊነት ልኩን በመጠነ መልኩ ከፍ ለማድረግ ኪነጥበብን እንደ ዋንኛ መሣሪያ መጠቀም ያስፈልጋል ሲሉ ተናግረዋል።

ብዝሃነትን ጠብቆና አክብሮ በመኖር ሂደት ላይ ኪነጥበብ ጉልህ ዐሻራ እንዳለው የጠቆሙት ኃላፊዋ፤ በመዲናዋ ዜጎች ኢትዮጵያዊነትን አክብረው እንዲኖሩ በኪነጥበብ ዘርፉ በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን አመላክተዋል።

ኪነጥበብ በማኅበራዊ አገልግሎት ብቻ ሳይሆን በኢኮኖሚ መስክም የማይተካ ሚና አለው ነው ያሉት ኃላፊዋ፤ በአዲስ አበባ ከተማ ለኪነ ጥበብ ዘርፉ ዕድገት የሚረዱ የመሠረተ ልማት ግንባታዎችን በማከናወን የኢትዮጵያዊነት ልዕልና በኪነ- ጥበቡ ውስጥ እንዲንፀባረቅ እየተሠራ ነው ብለዋል።

በብልፅግና ፓርቲ የአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ሞገስ ባልቻ በበኩላቸው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለባለሙያዎች እውቅና በመስጠት ዘርፉን ማበረታታቱን አንስተዋል፡፡

ግዙፉን የዓድዋ ድል መታሰቢያን ጨምሮ ትላልቅ ሜጋ ፕሮጀክቶች የኪነ ጥበብ ሥራዎች ለሕዝብ እይታ የሚበቁባቸውን መሠረተ ልማቶች በትኩረት እያከናወነ መሆኑን ገልጸዋል።



ሂሩት ካሳው (ዶ/ር)

ኢትዮጵያውያን በአንድነት ተሰባስበው ለሀገራቸው ሉዓላዊነት መስዋዕትነትን ከፍለው ባስመዘገቧቸው የዓድዋን ድል የመሳሰሉ አንፀባራቂ ድሎች የኪነጥበብ ዐሻራ የጐላ ነው ያሉት ኃላፊው፤ የጋራ ማንነትን በማጉላት የሀገረ መንግሥት ግንባታን ለማፋጠን መንግሥት አበረታች እንቅስቃሴዎችን እያደረገ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

«ኢትዮጵያውያን በደም የተሳሰርን በባህል የተወራረስን ብቻም ሳንሆን በርካታ የወል እውነቶች ያሉን ነን» ያሉት ኃላፊው፤ ይህንን ሀገራዊ አሰባሳቢ ገዥ ትርክቶች ከፍ እንዲሉና ወንድማማችነት፣ እህትማማችነት እንዲሁም አብሮነታችን እንዲጠናከር መሥራት ያስፈልጋል ብለዋል።

ኪነ ጥበብን ከፍ በማድረግ ለቆመችለት ሀገር የመገንባት እንዲሁም ሕዝብን የማስተሳሰር ዓላማ ለማዋል ሁሉም ባለድርሻ አካል የድርሻውን ሊወጣ ይገባልም ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

በፌስቲቫሉ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የኪነጥበብ ባለሙያዎች፣ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት፣ የተለያዩ ትምህርትቤቶች መምህራንና ተማሪዎች እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል። ትናንት የተጀመረው ከተማ አቀፍ ፌስቲቫሉ ነገ ይጠናቀቃል።

# ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ለተማሪዎች የማጠናከሪያ ትምህርት እየሰጠ ነው

**ውብሸት ሰንደቁ**

ወልቂጤ፡- ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ በአካባቢው ለሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ለሀገር አቀፍ ፈተና ተፈታኝ ተማሪዎች የማጠናከሪያ ትምህርት እየሰጠ መሆኑን አስታወቀ።

የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማኅበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት ዮሐንስ ገብሩ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚታየው የተማሪዎች ዝቅተኛ ውጤት በወልቂጤ አካባቢም ይታያል። ዩኒቨርሲቲውም ችግሩን ለማቃለል ለተማሪዎች የማጠናከሪያ ትምህርት በመስጠት እና ለመምህራን ሥልጠና በመስጠት እየሠራ ነው።

የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና የተማሪዎች ውጤት ማሽቆልቆል በሀገር አቀፍ ደረጃ የትምህርት ስብራቱ ማሳያ ነው ያሉት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፤ ስብራቱን ለመጠገን ዩኒቨርሲቲው በአካባቢው በሚገኙ ትምህርት ቤቶች እየሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

እንደ ዶክተር ዮሐንስ ገለፃ፤ በአካባቢው በሚገኙ ትምህርት ቤቶች የማጠናከሪያ ትምህርት የተጀመረው ካለፈው ዓመት ጀምሮ ነው። ባለፈው የትምህርት ዘመን ብቻ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ለሚማሩ 5 ሺህ 885 ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲው መምህራን የማጠናከሪያ ትምህርት ተሰጥቷል።

የማጠናከሪያ ትምህርቱ የተሰጠው በጉራጌ፣ በምሥራቅ ጉራጌ እና በሌሎች ወረዳዎች በሚገኙ ትምህርት ቤቶች መሆኑን የገለጹት ዶክተር ዮሐንስ፤ በመርሐ ግብሩ 20 ያህል ትምህርት ቤቶች ተጠቃሚ መሆናቸውን አብራርተዋል።

ማጠናከሪያ ትምህርት በመስጠት 50 የዩኒቨርሲቲው መምህራን መሳተፋቸውን ገልጸውም፤ መምህራኑ ከማጠናከሪያ ትምህርት በተጨማሪ በትምህርት ቤቶች እያስተማሩ የሚገኙ መምህራንን የማሰልጠን ሥራ ሠርተዋል ብለዋል።

ዩኒቨርሲቲው ባዘጋጀው የመምህራን ሥልጠና መርሐ ግብር 1 ሺህ 100 የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን ሥልጠና ወስደዋል ሲሉም አብራርተዋል።

በዘንድሮው ዓመትም ተመሳሳይ የማጠናከሪያ ትምህርት እና የመምህራን ሥልጠና በተለያዩ አካባቢዎች በሚገኙ ትምህርት ቤቶች እንደሚሰጥ የተናገሩት ዶክተር ዮሐንስ፤ ለዚህም ዝግጅቶች እየተደረጉ እንደሚገኙ አብራርተዋል።

ዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ማኅበረሰብ ተኮር ሥራዎችን እየሠራ እንደሚገኝ እና አጠናክሮ እንደሚቀጥልም አብራርተዋል።



ዮሐንስ ገብሩ (ዶ/ር)



# ኤጀንሲው በ700 ሚሊዮን ብር ያስገነባው ዘመናዊ ሕንፃ ዛሬ ይመረቃል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- ዘመናዊ ግብዓቶች ተሟልተውለት በ700 ሚሊዮን ብር የተገነባውን ሕንፃ ዛሬ አስመርቆ ወደአገልግሎት እንደሚያስገባ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተ-መዛግብትና ቤተ-መጻሕፍት ኤጀንሲ (ወመዘክር) አስታወቀ፡፡

የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ይኩኖአምላክ መዝገቡ ትናንት በሰጡት መግለጫ እንዳመለከቱት፤ ዛሬ የካቲት 16 ቀን 2016 ዓ.ም ተቋሙ የተመሠረተበትን 80ኛ ዓመት በማክበር አዲስ ያስገነባው ሕንፃ ተመርቆ ወደአገልግሎት ይገባል።

አዲሱ ሕንፃ 17 ወለሎች ያሉትና በመንግሥት ከ700 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ ተደርጎበት የተገነባ መሆኑን አመላክተው፤ ሕንፃው መዛግብትን ለማደራጀት ምቹ ተደርጎ የተሠራ በመሆኑ ኤጀንሲው ሥራውን አጠናክሮ እንዲቀጥል የሚያግዘው ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ተቋሙ የመዛግብት ማከማቻ እንደመሆኑ ዘመኑን ባገናዘበ መልኩ በቴክኖሎጂ ተደግፎ የተገነባው ሕንፃ ለተገልጋዮች ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር ዳይሬክተሩ አንስተዋል።

ሕንፃው ወደአገልግሎት ሲገባም ተገልጋዮች ቀድመው ምን ዓይነት መረጃ መኖሩን የሚመለከቱበትና ሕጉ በሚፈቅደው ልክ ደግሞ ባሉበት ሆነው የሚፈልጉትን መዛግብት የሚያገኙበትን ቴክኖሎጂ የያዘ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

ሕንፃው የቤተ መዛግብትና የቤተመጻሕፍት አገልግሎት ከመስጠት በተጨማሪ የስዕል ኤግዚቢሽን ማሳያ፣ የስዕል ስቱዲዮ፣ የሕፃናት ቤተ መጻሕፍት፣ የሥልጠና ክፍሎች፣ የመሰብሰቢያ አዳራሾች ያሉት ሲሆን፤ ንባብ ላይ ጥናት ለሚያከናውኑ ሰዎች የተሻለ አገልግሎት የሚሰጥበት ነው ብለዋል፡፡

ዛሬ ከፍተኛ በመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች፣ በአንባቢያን፣ በመጽሐፍ አዟሪዎች እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በሚገኙበት ሕንፃው እንደሚመረቅ አስታውቀው፤ ከምርቃቱ ማግስት ጀምሮ ማንኛውም ሰው የሚታደምባቸው የተለያዩ ዝግጅቶች መኖራቸውን ገልጸዋል፡፡

ተቋሙ ለ80 ዓመታት የተለያዩ ሰነዶችን በመሰብሰብና በማደራጀት ለመረጃ ፈላጊዎች ተደራሽ ሲያደርግ ቆይቷል ያሉት አቶ ይኩኖአምላክ፤ በሀገሪቱ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ታሪኮች ላይ ትልልቅ ዐሻራ ያኖሩ ሰዎችን በማፍራት የማይተካ ሚና መጫወቱንም ጠቁመዋል።

በተጨማሪም ተቋሙ ከኢትዮጵያ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር በግዕዝ የተጻፉ ሰነዶችን በቀላሉ ወደ አማርኛ መቀየር የሚችልና መረጃዎች በቀላሉ ማግኘት የሚቻልበት ቴክኖሎጂ እያበለጸገ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት ኤጀንሲ በ1936 ዓ.ም በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመን የተመሠረተ ሲሆን፤ ከአዲስ አበባ በተጨማሪም በተለያዩ ክልሎች እንዲሁም በማረሚያ ቤቶች አብያተ መጽሐፍትን እያቋቋመ ስልጠና እየሰጠ የሚገኝ ተቋም መሆኑ ዳይሬክተሩ አስረድተዋል።

# የቲቢ በሽታን በምርመራ የመለየት አቅም 73 በመቶ ደርሷል

## - የአሜሪካ ተራድኦ ድርጅት 156 የሕክምና መሣሪያዎች ድጋፍ አደረገ

**ሳሙዔል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ የቲቢ በሽታን በምርምራ የመለየት አቅም 73 በመቶ መድረሱን የጤና ሚኒስቴር አስታወቀ። የአሜሪካ ተራድኦ ድርጅት ከ3 ሚሊዮን ዶላር በላይ ዋጋ ያላቸው 156 የቲቢን በሽታ መመርመር የሚያስችሉ የሕክምና መሣሪያዎች ለጤና ሚኒስቴር ድጋፍ አድርጓል።

የቲቢን በሽታ መመርመሪያ (ጄኔክስፐርት) የሕክምና መሣሪያዎቹን ለጤና ሚኒስቴር ያስረከቡት የአሜሪካ ተራድኦ ድርጅት (ዩ ኤስ ኤይድ) ተልዕኮ ዳይሬክተር ስኮት ሆክላንደር ሲሆኑ የተረከቡት ደግሞ የጤና ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ደረጀ ዱጉማ ናቸው።




የጤና ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ደረጀ ዱጉማ በወቅቱ እንደገለጹት፤ በአሁኑ ጊዜ በሀገሪቱ ወደ 600 የሚጠጉ የቲቢና ተያያዥ መመርመሪያ መሣሪያዎች ሲኖሩ እንደሀገርም የቲቢ በሽታን የመለየት አቅም 73 በመቶ ደርሷል፡፡

ኢትዮጵያ በ2030 ዓ.ም የቲቢ በሽታን በ90 በመቶ ለመቀነስ ጥረት እያደረገች ትገኛለች ብለው፤ በመጪው ዓመት በቲቢ በሽታ ላይ ሀገር አቀፍ ጥናት እንደሚደረግ አመላክተዋል፡፡

የአሜሪካ ተራድኦ ድርጅትም ይህ ግብ እንዲሳካ ድጋፍ እያደረገ ነው ያሉት ዶክተር ደረጀ፤ ከአሜሪካ ተራድኦ ድርጅት 156 የቲቢ በሽታ መመርመሪያ የሕክምና መሣሪያዎችን ተረክበናል ብለዋል።

የአሜሪካ ተራድኦ ድርጅት ባለፉት ዓመታት ለኢትዮጵያ በእናቶችና ሕፃናት ዙሪያ፣ በሥርዓተ ምግብ፣ በበሽታ መከላከል እና በአጠቃላይ ለጤናው ዘርፍ በርካታ ድጋፍ ሲያደርግ ቆይቷል። አሁን ደግሞ የተላላፊ በሽታዎች ስርጭትን ለመቀነስና የሟቾች ቁጥርን ዜሮ ለማድረስ ድጋፍ እያደረገ ይገኛል።

ባለፉት ዓመታት ዩ ኤስ ኤይድ ከ319 በላይ የሕክምና መሣሪያዎች ድጋፍ ለጤና ሚኒስቴር አስረክቧል ያሉት ዶክተር ደረጀ፤ አሁን ያደረገው ድጋፍ ከ3 ሚሊዮን ዶላር በላይ ዋጋ የሚያወጣ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

ይህም ከቀጣይ ሳምንት ጀምሮ በግጭት ለተጎዱ አካባቢዎች እና የተላላፊ በሽታዎች ስርጭት ከፍተኛ በሆኑባቸው አካባቢዎች ይሰጣል ብለዋል።

እንደ ዶክተር ደረጀ ገለፃ፤ በኢትዮጵያ በየዓመቱ ከ119 ሺህ በላይ ሰዎች በቲቢ ይያዛሉ። ይህንን ቁጥር ለመቀነስ የሕክምና መሣሪያዎች ጉልህ ሚና አላቸው። በድጋፍ የተገኙት የሕክምና መሣሪያዎች ከሰውነት ፈሳሽ በመውሰድ በአጭር ደቂቃ ውስጥ የቲቢ በሽታ ያለበትን ሰው መለየት የሚያስችሉ ናቸው፡፡

መሣሪያዎቹ ከቲቢ በሽታ በተጨማሪ ኤች.አይ.ቪ.ን ጨምሮ 40 የሚደርሱ ተላላፊ በሽታዎችን መመርመር እንደሚያስችሉ ተናግረዋል።

መመርመሪያ መሣሪያዎቹ እጅግ ዘመናዊና የመጨረሻ ሞዴል በመሆናቸው መድኃኒት የለመደ ተላላፊ በሽታን በቀላሉ መለየት ያስችላሉ ያሉት ዶክተር ደረጀ፤ በቀጣይ በየወረዳው አንድ የቲቢ መመርመሪያ መሣሪያ እንዲኖር እየተሠራ ነው። ይህም በተላላፊ በሽታዎች የሚከሰትን የሞት ቁጥር እንዲቀንስ ያደርጋል ብለዋል።

የአሜሪካ ተራድኦ ድርጅት ዳይሬክተር ሚስተር ስኮት ሆክላንደር በበኩላቸው፤ የአሜሪካ ተራድኦ ድርጅት በኢትዮጵያ ትልቁ ድጋፍ አድራጊ ድርጅት መሆኑን ጠቅሰዋል።

በየዓመቱም የ154 ሚሊዮን ዶላር ድጋፍ ያደርጋል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ይህም በሀገሪቱ ዘመናዊ የሕክምና አሰጣጥ እና ተደራሽ የሕክምና አገልግሎት እንዲኖር ያስችላል ብለዋል።

የአሜሪካ ተራድኦ ድርጅት በኢትዮጵያ የሚያደርገው ድጋፍ ተጠናክሮ ይቀጥላልም ብለዋል፡፡

# የአንጋፋው ድምፃዊ ጌታቸው ካሳ ሥርዓተ ቀብር ተፈጸመ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- የተወዳጁና አንጋፋው ድምጻዊ ጌታቸው ካሳ ሥርዓተ ቀብር ተፈጸመ፡፡

የቀብር ሥነ-ሥርዓቱ የአርቲስቱ ቤተሰቦች፣ ወዳጅ ዘመዶች፣ የሙያ አጋሮች እንዲሁም የሙያ አድናቂዎች በተገኙበት ትናንት በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ቤተክርስትያን ተፈጽሟል፡፡



አርቲስት ጌታቸው ካሳ ከአባቱ አቶ ጺጋዬ መኮንንና ከእናቱ ከወይዘሮ ሳንካምየለሽ ደጀኔ ጥር 3 ቀን 1939 ዓ.ም በአዲስ አበባ የካ ሚካኤል አካባቢ መወለዱን የሕይወት ታሪኩ ያስረዳል።

ወላጅ አባቱ ሙዚቃ ውስጥ እንዳይገባ ከገባም በስማቸው እንዳይጠራ በመከልከላቸው፤ አርቲስት ጌታቸው ለሙዚቃ ካለው ፍቅር የተነሳ የአባቱ ስም በባለቤቱ አባት ስም ቀይሮ ወደ ሙዚቃው ዓለም በይፋ የተቀላቀለ አርቲስት ነበረ።

አርቲስት ጌታቸው ካሳ፤ ሀገሬን አትንኳት፣ አዲስ አበባ፣ ሳይሽ እሳሳለሁ፣ ልውሰድሽ አንድ ቀን፣ የከረመ ፍቅር፣ እመኛለሁ፣ ትዝ ባለኝ ጊዜ በሚሉት ዘፈኖቹ ይታወቃል፡፡

ድምጻዊ ጌታቸው በሐረርጌ ጠቅላይ ግዛት የሐረር ፖሊስ ኦርኬስትራ የተቀላቀለ ሲሆን፤ አሃዱ ያለበት አዝመሪኖ የኤርትራ ትግሪኛ ሙዚቃ ለሙዚቃ የተሻለ ዝንባሌ እንዲኖረው አስችሎታል።

ድምጻዊ ጌታቸው ካሳ የራሱ የሙዚቃ ፈጠራ የታየበትን «ሳይሽ እሳሳለሁ» የተሰኘ ሙዚቃው በጊዜው የነበሩ ሸክላ ሙዚቃ አሳታሚዎች ቀልብ ውስጥ እንዲገባ አድርጎት እንደነበርም ይነገራል፡፡

ከመድረክ ሥራዎቹ በተጨማሪ በበርካታ ምሽት ክበብ ሙዚቃን የተጫወተው አርቲስቱ፤ ከሙዚቃ ጎን ለጎን ክራርና ፒያኖ ይጫወት እንደነበር የሕይወት ታሪኩ ያስረዳል።

ለ28 ዓመታት ኑሮውን በአሜሪካን ሀገር ቢያደርግም ለሀገሩ ከነበረው ጥልቅ ፍቅር የተነሳ ዜግነቱን ሳይለውጥ ወደ እናት ሀገሩ መመለስ መቻሉ የሙያ አጋሮቹ በነበረው የሽኝት መርሐ ግብር ላይ ተናግረዋል።

በተጨማሪም አርቲስቱ ለ50 ዓመታት በመዚቃ ውስጥ ማሳለፉንና ለኢትዮጵያ የሙዚቃ ኢንዱስትሪ ማደግ ጉልህ ድርሻ ማበርከቱ ተገልጿል፡፡

በኢትዮጵያ ሙዚቃ ኢንዱስትሪ ማደግ ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው የሚነገርለት አርቲስት ጌታቸው ካሳ፤ የመጀመሪያውን በጥበቡ በለጠ የተገጠመው እመኛለሁ የተሰኘውን ዜማ ለመድረክ አብቅቶ በሕዝብም ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ አስችሎታል፡፡

ድምጻዊ ጌታቸው ካሳ ባደረበት ሕመም በሕክምና ሲረዳ ቆይቶ የካቲት 13 ቀን 2016 ዓ.ም በተወለደ በ77 ዓመቱ ከዚህ ዓለም በሞት መለየቱ ይታወሳል፡፡

# ኢንስቲትዩቱ፣ አርሶ አደሮች በመጪዎቹ ቀናት የሚኖረውን እርጥበት ለመጠቀም እንዲዘጋጁ አሳሰበ

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- አርሶ አደሮች በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረውን እርጥበት ለመጠቀም እንዲዘጋጁ የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት አሳሰበ፡፡

በመካከለኛው፣ በሰሜን ምሥራቅ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች በአንዳንድ ቦታዎቻቸው ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ ኢንስቲትዩቱ አስታውቋል፡፡

ኢንስቲትዩቱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጠው መረጃው እንዳስታወቀው፤ አርሶ አደሮችና የሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊውን ግብዓት ከወዲሁ በማዘጋጀት የሚኖረውን እርጥበት በአግባቡ ለመጠቀም የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ማከናወን ያስፈልጋቸዋል፡፡

ኢንስቲትዩቱ በመግለጫው እንዳመላከተው፤ በሰሜን ምሥራቅ፣ በመካከለኛው በደቡብ ምዕራብ እንዲሁም በስምጥ ሸለቆና አጎራባች አካባቢዎች የተሻለ ጥንካሬ የሚኖራቸው በመሆኑ በበልግ አብቃይ አካባቢዎች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡

ይህንንም እርጥበት ጥቅም ላይ ለማዋል አስፈላጊውን ግብዓት ከወዲሁ በማዘጋጀት የሚኖረውን እርጥበት በአግባቡ ለመጠቀም የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ማከናወን ያስፈልጋቸዋል፡፡

እንደ ኢንስቲትዩቱ ገለጻ፤ የአየር ሁኔታው የአፈር ውስጥ እርጥበትን በማሻሻል የበልግ ወቅት ሰብሎችን በወቅቱ ለመዝራት ይጠቅማል፡፡ በተጨማሪም ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ ፍላጎትን ከማሟላት አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

በመካከለኛው ዓባይ፣ የላይኛውና የመካከለኛው አዋሽ ጊቤ፣ የስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛው አዋሽ፣ ገናሌ ዳዋ እንዲሁም በጥቂት የላይኛው ተከዜ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ የአየር ሁኔታ ይኖራቸዋል፡፡

ከኦሮሚያ ክልል ኢሉባቦር፣ ጅማ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ምዕራብ አርሲና አርሲ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፣ ከአማራ ክልል ምሥራቅ ጎጃም፣ የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች እንዲሁም የሰሜን ሸዋና የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ ዝናብ የሚኖራቸው ይሆናል፡፡

የሲዳማ ክልል ዞኖች የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፣ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ ሲሆን፣ በጥቂት ስፍራዎቻቸው ላይም ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡

በአየር ሁኔታ ትንበያው መሠረት በሰሜን ምሥራቅ፣ በመካከለኛው በደቡብ፣ ደቡብ ምሥራቅ፤ ምሥራቅ እንዲሁም በስምጥ ሸለቆና አጎራባች አካባቢዎች በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ ኢንስቲትዩቱ ገልጿል፡፡

በምሥራቅ አማራ፤ በደቡብ ምዕራብ እና በመካከለኛው የሀገራችን አካባቢዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙም አብራርቷል፡፡

## የሐዋሳና..

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የደረቅ ወደቦቹን ግንባታ በ2016 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ ለማስጀመር ዕቅድ ተይዞ በተለያዩ ምክንያቶች መዘግየቱን አስታውሰዋል።

ተቋሙ የፌዴራል የግዢ መመሪያ የሚከተል መሆኑን አቶ ምህረት አብ ገልጸው፤ ግንባታቸው ላለመጀመሩም ምክንያቱ የግዢ ሂደቱ ላይ ችግር በማጋጠሙ ነው ብለዋል፡፡

ድርጅቱ ግንባታውን ለማስጀመር ሦስት ጊዜ ጨረታ ያወጣ ቢሆንም የግዢ መመሪያ የሚያሟሉና ብቃት ያላቸው ተወዳዳሪ ተጫራቾች ባለማግኘቱ በተደጋጋሚ ጨረታ መሰረዙ አስታውቀዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በጅማ ለሚከናወነው የደረቅ ወደብ ግንባታ የቦታ ርክክቡ ላይ የተወሰነ መዘግየት ተፈጥሮ የነበረ ሲሆን፤ በአሁኑ ጊዜ ግን ከ20 ሄክታር በላይ መሬት በመረከብ የማስተር ፕላንና የቢዝነስ ፕላን ጥናት መጠናቀቁን ገልጸዋል፡፡

እንዲሁም በሐዋሳ ለግንባታው የተሰጠው ቦታ ሦስት ጊዜ ስፍራው እንዲቀየር መደረጉን የገለጹት ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ አሁን ላይ ድርጅቱ ለቦታው ካርታ መቀበሉንና ግንባታ ለማስጀመር የሚያስችለውን ቅድመ ዝግጅት ማጠናቀቁን ጠቅሰዋል፡፡

በመሆኑም የሁለቱም ደረቅ ወደብ ተርሚናሎች ቅድመ ግንባታ ሂደት በተቻለው ፍጥነት አጠናቅቆ እስከ መጋቢት ወር መጨረሻ ግንባታቸውን ለመጀመር እየተሠራ መሆኑን አቶ ምህረትአብ ገልጸዋል፡፡

ለሁለቱ ደረቅ ወደቦች ለመጀመሪያ ዙር ግንባታ 300 ሚሊዮን ብር መመደቡን አስታውቀው፤ ለቀጣይ ዙር ግንባታዎች ደግሞ ተጨማሪ በጀት እንደሚመደብ አስረድተዋል።

የሚገነቡት ወደቦች ከኮምቦልቻ፣ ከሰመራ እንዲሁም ከመቀሌ የደረቅ ወደብ ተርሚናሎች ጋር የሚመጣጠን አቅም እንደሚኖራቸው አመላክተው፤ አንድ ሺህ 500 ኮቴይነሮችን የማስተናገድ አቅም ይኖራቸዋል ብለዋል፡፡

ግንባታዎቹ በደቡብ የሀገሪቱ ክፍል ያለውን የንግድ እንቅስቃሴውን ለማነቃቃት፣ የወጪ ገቢ ንግድን ለማቀላጠፍ እንዲሁም በወደብ የሚቆዩ ዕቃዎችን ኪራይ ወጪ ከመቀነስ አንጻር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል ሲሉ አስረድተዋል።

ፕሮጀክቶቹ በመጋቢት ወር ግንባታቸው ከተጀመረ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ እንደሚጠናቀቁ የገለጹት ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ የቢሮ፣ የመጋዘንና የተለያዩ አገልግሎቶች የሚሰጡባቸው ግንባታዎች እንደሚከናወኑ ጠቁመዋል።

## አውደ ርዕዩ ኢትዮጵያ ለዓለም ሰላምና ለጥቁር...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ፖላንዳዊቷ እንስት በአታ ስኮሩፓ ገለጹ፡፡

«ዲፕሎማሲያችን ለብሔራዊ ጥቅማችን» በሚል መሪ ሃሳብ በሳይንስ ሙዚየም ከተከፈተ ወራትን የተሻገረው የዲፕሎማሲ ሳምንት አውደ ርዕይ ኢትዮጵያውያንን ጨምሮ በተለያዩ ሀገራት ዜጎች በመጎብኘት ላይ ይገኛል።

አውደ ርዕዩን ሲጎበኙ ያገኘናቸው ፖላንዳዊቷ እንስት በአታ ስኮሩፓ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ የአውደ ርዕዩ ጎብኚዎች ከተለያዩ አካባቢዎች የመጡ ቢሆንም ኢትዮጵያ ለዓለም ሰላምና ለጥቁር ሕዝቦች ነፃነት የከፈለችውን ዋጋ በጉልህ መረዳት እንዲችሉ የሚያግዝ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ጓደኞቼን ለመጎብኘት ነው የመጣሁት ያሉት በአታ፤ አውደ ርዕዩን የመመልከት ዕድል በማግኘቴ ተደስቻለሁ፤ አስደሳችና አስተማሪ ሆኖ አግኝቼዋለሁ ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያን ዲፕሎማሲያዊ ታሪክ ከጅምሩ አንስቶ አሁን እስከደረሰበት ደረጃ ድረስ ከአውደ ርዕዩ መገንዘባቸውን ጠቁመው፤ በዚህም ኢትዮጵያ በጣም አስደናቂና ከተለያዩ ሀገራት ጋር መልካም የሚባል የዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ታሪክ ያላት ሀገር መሆኗን መረዳት እንደቻሉ ገልጸዋል፡፡

አውደ ርዕዩ የኢትዮጵያን ዲፕሎማሲ አካሄድና ብሔራዊ ጥቅሟን ለማስከበር የሄደችበትን ርቀት የሚያስረዳ ነው ያሉት በአታ፤ ቅኝ ያልተገዛች ብቸኛዋ የአፍሪካ ሀገር ከመሆኗ በተጨማሪ ለሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ነፃነት ተምሳሌት መሆን መቻሏን አንስተዋል፡፡

እንደ በአታ ገለጻ፤ የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲያዊ ጉዞ መልካምና ሰፊ በመሆኑ በዓለም ላይ ተጽዕኖዋ ትልቅ እንዲሆን አድርጓል፡፡ ይህም ከአፍሪካ አንድነት ድርጅት ምስረታ ጀምሮ እስከ ተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባልነትና በዓለም ሰላም የማስከበር ሂደት ውስጥ ተሳታፊ እንድትሆን አስችሏታል፡፡

የቀድሞ የኢትዮጵያውያን የጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ንቅናቄ በዓለም ላይ ትልቅ ሚና እንደነበረው ያስታወሱት በአታ፤ ይህን ተከትሎ እስከ አሁንም ድረስ በአሜሪካ ውስጥ የ'ብላክ ላይፍ ማተር' እንቅስቃሴዎች ተጠናክረው መቀጠላቸውን ለአብነት ጠቅሰዋል፡፡

አውደ ርዕዩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለአፍሪካ ብሎም ለመላው ዓለም ያበረከተው አስተዋፅኦ ምንድን ነው የሚለውን የሚያስረዳ በመሆኑ ሁሉም አካል ሊጎበኘው ይገባል ብለዋል።

«ኢትዮጵያ እየሄደች ያለችበት ዲፕሎማሲያዊ አካሄድ የሚያስደንቅ ነው፡፡ ለመሥራት ለመለወጥ ምቹ ሀገር ናት» ያሉት በአታ፤ ለመልማት እየጣረች ያለች ሀገር በመሆኗ ከሌሎች ሀገራት ጋር ያላትን ትስስር ልታጠናክር እንደሚገባ መክረዋል፡፡

ኢትዮጵያውያን የመተባበርና የመተጋገዝ ባህል ያላቸው ዜጎች በመሆናቸው በቀላሉ ከሌሎች ሀገራት ጋር በስምምነት በመሥራት አብሮ የማደግ ዕድላቸው ሰፊ መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

## ጉዳት ለደረሰባቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

አሰጣጥ ረጂ ድርጅቶች በመቀላቀላቸው ድጋፉ ከፍ ይላል ተብሎ ስለሚጠበቅ በቂ በሆነ መንገድ ድጋፍ ለሚፈልጉ ዜጎች ተደራሽ ይሆናል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በአማራና አፋር ክልሎችም ድጋፉ ይቀጥላል ያሉት አቶ አታለለ፤ በኮሚሽኑ ስምንቱ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች በተለመደው መልኩ ከተደራጁ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ግዢ በመፈጸም በመጠባበቂያ መጋዘኖች ክምችት ማድረጉ መቀጠሉንና በቂ ክምችት መኖሩን አመልክተዋል፡፡

በአንደኛና ሁለተኛ ዙሮች በሰው ሠራሽና በተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት የቅድሚያ ቅድሚያ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተብሎ ለተጠቀሱና ልየታ ለተደረገላቸው ሰባት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ዜጎች ርዳታ መሰጠቱን፣ በሦስተኛ ዙር ደግሞ ለስድስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ዜጎች ድጋፍ መደረጉንም አስታውሰዋል፡፡

በትግራይ ክልል በድርቅና በተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት ርዳታ ለሚፈልጉ በአንደኛ፣ በሁለተኛና በሦስተኛ ዙር ርዳታ ለሁለት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ዜጎች በስድስት ወራት 894 ሺህ 302 ኩንታል ምግብ ነክ ርዳታ ተሰጥቷል፡፡

አራት ነጥብ አራት ቢሊዮን የሚጠጋ ብር ለትግራይ ክልል ድጋፍ ወጪ ተደርጓል፡፡ ከዚህ ውስጥ መንግሥት አንድ ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር ሲያወጣ፤ ለጋሾች ሦስት ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር አውጥተዋል ብለዋል፡፡

በመንግሥት በተሠራው የዲፕሎማሲ ሥራ በአንደኛና ሁለተኛ ዙር ያልተሳተፉ ረጂ ድርጅቶች በሦስተኛው ዙር ተቀላቅለው የሰብዓዊ ድጋፍ ማድረጋቸውን አንስተዋል፡፡

በተለይም በአማራ ክልል ዋግ ኽምራ፣ ሰሜን ጎንደር፣ ማዕከላዊ ጎንደር፣ ደቡብ ጎንደር፣ ሰሜን ወሎ፣ ደቡብ ወሎ፣ ኦሮሞ ብሔረሰብ ዞን፣ ሰሜን ሸዋና ምሥራቅ ጎጃም አካባቢዎች በአጠቃላይ 23 ወረዳዎች ሁለት ሚሊዮን የሚጠጉ ዜጎች ተረጂዎች እንደነበሩ አመልክተዋል፡፡

በትግራይ ክልልም 31 የሚጠጉ ወረዳዎች ሰሜን ምዕራብ፣ ማዕከላዊ፣ ደቡብ ምሥራቅና ደቡባዊ ትግራይ በሚባሉ አካባቢዎች ሁለት ሚሊዮን የሚጠጉ ተረጂዎች ያሉ ሲሆኑ፤ በአፋር ክልል ዞን አንድ፣ ዞን ሁለት፣ ዞን አራት እና ዞን አምስት በድርቅ የተፈናቀሉ 321 ሺህ የማኅበረሰብ ክፍሎች እንዳሉ ጠቁመዋል፡፡

በአማራ ክልልም በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ጉዳት ለደረሰባቸው ሁለት ሚሊዮን ለሚጠጉ ዜጎች ርዳታ ተሰጥቷል፡፡ በዓይነትና በገንዘብ በመንግሥት አንድ ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ብር፤ በለጋሾች ሁለት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር በአጠቃላይ አራት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር የሚጠጋ ገንዘብ ወጪ ተደርጓል ብለዋል፡፡

በአፋር ክልልም በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋ ጉዳት ለደረሰባቸው 302 ሺህ ርዳታ ፈላጊዎች 85 ሺህ 853 ኩንታል ምግብ ነክ ነገሮች ድጋፍ መደረጉንም ተናግረዋል፡፡ በአካባቢያቸው ምግብ ገዝተው እንዲጠቀሙ 25 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር ተጨማሪ ገንዘብ መሰጠቱንም ነው የገለጹት፡፡

## «ኢትዮጵያ የምትታወቀው...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ እንዳስታወቁት፤ ኢትዮጵያ ከራስ ገዟ ሱማሌላንድ ጋር ያደረገችው የባሕር በር የምታገኝበት የመግባቢያ ስምምነት ሱማሊያን ሉዓላዊነቴ ተደፍሯል በሚል እሳቤ ማስቆጣቱ አስገራሚ ነው፡፡ ነገር ግን ኢትዮጵያ ጎረቤት ሀገር ለሆነችው ሱማሊያ እና ለሌሎች ሀገሮች ሰላም መከበር ስትል ወታደሮቿን መስዋዕት አድርጋለች፡፡ ከዚህ የተነሳ ኢትዮጵያ የምትታወቀው የጎረቤቶቿን ሰላም ለማስከበር መስዋዕትነት በመክፈል እንጂ በየትኛውም ሀገር ጉዳይ ጣልቃ በመግባት ማወክ አይደለም፡፡

ኢትዮጵያ ሰላማዊ በሆነ መንገድ ልማቷን ማካሄድ እንጂ የጦርነት ፍላጎት የላትም ብለዋል፡፡ ነፃነቷን በማስከበር እና ለሌሎች ነፃነት አርዓያ በመሆን የምትታወቅ ሀገር፤ ዛሬ በአዲስ ማንነት ተገልጻ የማንንም ሀገር ሉዓላዊነትን የምትደፍር ሀገር አለመሆኗን ተናግረዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሰላም አስከባሪ ኹከትና ብጥብጥ ባለበት ተገኝቶ ሰላም በማስከበር የሚታወቅ ነው ያሉት ካፒቴኑ፤ በዚህ ተግባሩም አህጉሩን ከማኩራት ባለፈ በሌሎችም ሀገራት የሚታወቅ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

እኛ ያቀረብነው ጥያቄ የባሕር በር ይከፈትልን የሚል ነው ያሉት ካፒቴን መርሻ፣ የትኛውንም ሀገር የመውረር ፍላጎትም የሌለን መሆኑ ሊታወቅ ይገባል ብለዋል፡፡ ይህ የባሕር በር ጥያቄ ደግሞ ልማት እንጂ ጦርነት መሻት እንዳልሆነም አመልክተዋል፡፡

ከራስ ገዟ ሱማሌላንድ ጋር ያደረግነው ስምምነት በሱማሊያ ሉዓላዊነት ላይ ጣልቃ መግባት እንዳልሆነ ጠቅሰው፤ ሱማሊያ ኢትዮጵያን ለመኮነን ከማሰቧ በፊት በጠረጴዛ ዙሪያ መወያየትን ምርጫ ማድረግ ነበረባት ሲሉ ገልጸዋል፡፡ የቱንም ያህል ኢትዮጵያን ጣልቃ ገብ ናት ብሎ በመኮነን መናገር የልማት ጥማቷን ማቆም አይቻልም ብለዋል፡፡

እንደ እርሳቸው ገለጻ፤ ኢትዮጵያ ለሱማሊያ ሕዝብ ሰላም ወታደሯን ልካ ተዋግታለች፡፡ የሀገሪቱ ሉዓላዊነት እንዳይደፈርም መስዋዕትነት ከፍላለች፡፡ ከአልሸባብ ጋር ተዋግታ ወታደሯን ለሰላም ስትል ሰውታለች፡፡

ያንን ሁሉ መስዋዕትነት እየከፈለች እዚህ የደረሰች ኢትዮጵያ የልማት ጥያቄ አነሳች እንጂ በማንም ሉዓላዊነት ላይ ጣልቃ አልገባችምም ብለዋል፡፡

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# “ኢትዮጵያ የባሕር በር ማግኘቷ ወደ ቀደመው ክብርና ዝናዋ ይመልሳታል”

ካፒቴን መርሻ ግርማ
የቀድሞ የኢትዮጵያ ባሕር ኃይል አመራር

አስቴር ኤልያስ



ፎቶ ፡- ሐዲስ አብርሃ

**የዛሬው የዘመን እንግዳችን ካፒቴን መርሻ ግርማ ይባላሉ፡፡ ተወልደው ያደጉት አዲስ አበባ ከተማ እንጦጦ ራጉዔል ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ነው፡፡ አባታቸውን ጨምሮ ቤተሰቦቻቸው የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ናቸው፡፡ እንግዳችን አባታቸውን በሞት የተነጠቁት ሕጻን ሳሉ በመሆኑ አያውቋቸውም፡፡**

**በወቅቱ ተፈሪ መኮንን ያስተምር የነበረ ወንድም ስላላቸው እድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ እዛው ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት አስገቧቸው፡ እስከ 12ኛ ክፍል ከተማሩ በኋላ መሆን የሚፈልጉት የባሕር ኃይል ነበር፡፡ ውጥናቸውም ተሳክቶ በ1949 ዓ.ም ባሕር ኃይሉን ተቀላቀሉ፡፡ በወቅቱ ባሕር ኃይል ሰዎችን ሲቀበል ለሁለተኛ ዙር ሲሆን፣ እርሳቸውም የዚያ ዕድል ተጠቃሚ መሆን ቻሉ፡፡**

**የዛሬው እንግዳችን ካፒቴን መርሻ የኢትዮጵያን ባሕር ኃይል ከዛሬ 67 ዓመት በፊት ተቀላቅለው ሀገራቸውን ሲያገለግሉ የቆዩ ሲሆን፣ በደርግ ዘመን የባሕር ኃይል ምክትል አዛዥ፤ ቀጥሎም በወቅቱ እርሳቸው ዘንድ ያሉ ወደ 15 የሚጠጉ መርከቦች አዛዥ የሆኑም ናቸው፡፡**

**እርሳቸው ብዙን ጊዜ ንግግራቸው ፊት ለፊትና እውነት ነው፡፡ ከዚህ የተነሳም በአለቆቻቸው ዘንድ እንደስጋት ይቆጠራሉ፡፡ ብዙ ጊዜ እውነት ስለሚናገሩም የመሾም ዕድሉ ጥቂት ለማይባል ጊዜ ሲያልፋቸው ቆይቷል፡፡ አዲስ ዘመንም ዘለግ ላለ ዓመት ኢትዮጵያን በባሕር ኃይሉ ዘርፍ ያገለገሉትን ካፒቴን መርሻ ግርማን ስለቀድሞው ባሕር ኃይልና መሰል ጉዳዮችን አስመልክቶ ቆይታ በማድረግ በእንግዳ ዓምዱ ይዟቸው ቀርቧል፡፡ መልካም ንባብ፡፡**

**አዲስ ዘመን፡- የባሕር ኃይል ትምህርት የተማሩት የት የት ሀገር ነው?**

**ካፒቴን መርሻ፡-** ትምህርቴን እየተማርኩ ሳለ አሰብ የነበረው የኢትዮጵያን ባሕር ኃይል ስለመቀላቀል ነው፡፡ 12ኛ ክፍል እንዳጠናቀቅኩም ለሁለተኛ ዙር ምዝገባ ሲያደርግ የነበረውን ባሕር ኃይል የተቀላቀልኩት ሳላመነታ ነው፡፡ በባሕር ኃይል ኮሌጅም ለሦስት ዓመት ተኩል ተምሬ ለመመረቅ በቃሁ፡፡ በወቅቱ ለሥልጠና እንዲያግዝ የኖርዌይ መርከብ መጥቶ ስለነበር እንደተመረቅሁ ወዲህ ወዲያ ለማለት አልፈለግሁም፡፡ ዘመድ አዝማድም ለመጠየቅ አልወደድሁም፡፡ በቀጥታ ያደረግሁት ነገር ቢኖር እኔም ጨምሮ 16 ከምንሆነው ጋር ያቀናሁት ወደመርከቧ ነው፡፡ በዚያም መርከብ ከሌሎቹ ጓደኞቼ ጋር በመሆን ልምምድ እያደረግሁ በቀጥታ ያቀናሁት ወደኖርዌይ ነው፡፡ በኖርዌይም ባሕር ላይ ለአንድ ዓመት ያህል ሥልጠና አደረግሁ፡፡ በቀይ ባሕር፣ ሜዲትራንያን ባሕር፣ አትላንቲክ ውቂያኖስ ላይ ልምምድ ሳደርግ ቆየሁ፡፡

በኖርዌይ የነበረኝን የአንድ ዓመት ሥልጠናዬን አጠናቀቅሁ፡፡ ከአንድ ዓመት ቆይታ በኋላም በቀጥታ ያቀናሁት ወደ እንግሊዝ አገር ነው፡፡ ወደስፍራው ያቀናነው እኔን ጨምሮ አዛዥ የሆኑ ሰዎች ናቸው፡፡ በእንግሊዝ የመለማመጃ ማዕከል ስለመሣሪያ፣ ስለናቪጌሽን (የመርከቦችን እንቅስቃሴ የመምራት ጥበብ) እንዲሁም ስለኮሙኒኬሽን ተማርሁ፡፡ እዚያም ልክ እንደኖርዌይ ሁሉ በተመሳሳይ የአንድ ዓመት ቆይታ ነበረኝ፡፡

የእንግሊዝ አገር ቆይታዬን አጠናቅቄ ወደኢትዮጵያ ተመለስኩ፡፡ እንደመጣሁም ሁሉም በተለያየ ቦታ ተመደበ፤ እኔም የሠልጣኞች አስተዳደር ሆንኩ፡፡ ያንን የአስተዳደር ጊዜ እንደጨረስኩ የሄድኩት አነስተኛ መርከብ ላይ ሲሆን፣ የሄድኩትም በምክትል አዛዥነት ነው፡፡

የተሰጠኝን ኃላፊነት ከተወጣሁ በኋላ ያቀናሁት ለድኅረ ምረቃ ትምህርት (Postgraduate) ወደ ሀገረ አሜሪካ ነው፡፡ ከአሜሪካ ስመለስ ምፅዋ የነበረው ኃይል ከምፅዋ ተነስቶ እንደገና ዶንጎላ ላይ ተመሠረተ። በዚያን ጊዜ የእንግሊዛዊው ካፒቴን ቢቲ ምክትል ሆኜ ሠርቻለሁ፡፡ እዛው እየሠራሁ ሳለ የእንግሊዛውን ካፒቴን ቦታ በመያዝ አዛዥ ለመሆን በቃሁ፡፡ በዚያን ጊዜ አዝ የነበረው የመርከብ ብዛት አራት ነው፡፡

ከቆይታ በኋላ እንደገና ወደአገረ አሜሪካ ሳንዲያጎ በማቅናት የማኔጅመንት (Management) ትምህርት ለመማር ቻልኩ፡፡ ከአሜሪካ ቆይታ በኋላ ተመልሼ ወደኢትዮጵያ በመምጣት በናቪጌሽንና ኮሙኒኬሽን (Navigation and Communication) ማለትም የመገናኛ ሥራውን ስሠራ ቆየሁ፡፡ ከዚህ ሥራ በኋላ የሄድኩት ወደ አሥመራ ሲሆን፣ መዳረሻዬንም ያደረግሁት ከአሥመራ 50 ኪሎ ሜትር ራቅ ወደምትለዋ ዶንጎሎ ነው፡፡ እኔ በደርግ ዘመን የባሕር ኃይል ምክትል አዛዥ ነበርኩ፡፡ ቀጥሎም እኔ ዘንድ ያሉ 15 የሚጠጉ መርከቦችንም በአዛዥነት እሠራ ነበር፡፡

በወቅቱ ምፅዋ ውጊያ በነበረበት ወቅት የመርከቦቹ አዛዥ የነበርኩት እኔ ነኝ፡፡ የዚያን ጊዜ በጦሩ ተከብበን ነበር፡፡ ይሁንና ማንም ወደእኛ ሊጠጋ አልቻለም። በጥይት በመምታት እንዳይገቡ ማድረግ ችለናል፡፡ በዚያን ወቅት ጭነን ያመጣነው ታንኩንም መድፉንም ጭምር ነው፡፡ ከምፅዋ ያመጣነው መሣሪያ ሁሉ ዳህላክ ደሴት እንዲቀመጥ ተደረገ፡፡ ስለሆነም የትኛውም አይነት መሣሪያ ከዚህ የተነሳ በጠላት እጅ ሊገባ አልቻለም፡፡ ምፅዋ የተያዘው መሣሪያ ካወጣን በኋላ ነው፡፡

እዚህ ላይ አንድ ነገር ለመጥቀስ እወዳለሁ፡፡ እኔ ከባሕር ኃይሉ በተጨማሪ ለዚሁ ለባሕር ኃይሉ ስሠራ ወሳኝ የሆነውን የበረራ ትምህርት የመማር ጽኑ ፍላጎት ነበረኝና ወደእሥራኤል አገር አቅንቼ የበረራ ትምህርት ተማርኩ፡፡ ይሁንና ይህን የበረራ ትምህርት መማሬን አየር ኃይል አልወደደውም፡፡ ይሁንና የመማሬ ምስጢር በባሕር ላይ ቅኝት ለማድረግ ያመቸ ዘንድ ታስቦ እንጂ ለሌላ አይደለም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- እርስዎ የሥራ ዘመንዎን ያሳለፉት በባሕር ኃይል ውስጥ ነው፤ በመሆኑም ባለፉት ዘመናት በዘርፉ የነበረውን ሒደት እንዴት አገኙት?**

**ካፒቴን መርሻ፡-** በባሕር ኃይሉ ውስጥ ትልቁ ችግር የነበረው በተለይ በደርግ ዘመን የኃላፊነቱን ቦታ ራሱ የባሕር ኃይሉ እንዲወስንበት ከመተው ጣልቃ ለመግባት መሞከሩ ነው፡፡ የነበረው ችግር አዛገፉ አለ፤ ከአዛገፉ በተጨማሪ ደግሞ ካድሬው አለ፤ የደርግ አባል የሆነ ሠራተኛ አለ፡፡ ከአዛገፉ ጋር ያሉት እነዚህ አካላት ችሎታውም ማዕረጉም የላቸውም፡፡ ስለዚህ በደርግ ጊዜ ከጣልቃ ገብነትም አልፎ አብዛኛው በባሕር ኃይሉ ውስጥ ያሉት የደርግ ካድሬዎች ናቸው ማለት ይቻላል።

እኔ በበኩሌ ግን እንዲህ አይነቱ አካሄድ እምብዛም ስለማይመቸኝም ከካድሬ ጋር መሥራት ደስ አይለኝም ነበር ፡፡ እሺም አልላቸውም፤ አልቀበላቸውም፡፡ እንዲህ በማለቴም ሆነ ያለውን እውነታ ፊት ለፊት ተጋፍጬ ስለምናገር ብዙ ፈተና ደርሶብኛል፡፡ ከመገደልም ተርፌያለሁ፡፡ ምክንያቱም ካድሬነቱን እንጂ ችሎታው የላቸውም፡፡ ስለዚህ ባሕር ኃይል ፖለቲካ አይደለም፡፡ በእውቀት የሚመራ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በወቅቱ አሰብ የኢትዮጵያ እንደነበረች ይታወቃል፤ በመሆኑም አሰብ መሰጠት አልነበረበትም በሚል ብዙዎች ይቆጫሉና በዚህ ላይ ስሜትዎ ምንድን ነው?**

**ካፒቴን መርሻ፡-** አሰብ ከኤርትራ ጋር ግንኙነት የለውም፡፡ ከነበረውም የነበረው ከወሎ ግዛት ጋር ነው። ነገር ግን በወቅቱ የነበሩ አካላት ከእጃቸው አወጡት፡፡ ምክንያቱም አሰብ በውሎ ውስጥ የሚገኝ እንደመሆኑ የኢትዮጵያ እንጂ የኤርትራ ግዛት አለመሆኑ የሚታወቅ ጉዳይ ነው፡፡ በወቅቱ የነበረው ጦር አካባቢውን ለቅቆ ስለሄደ ያዙት፡፡ አሰብን ማጣት ማለት ብዙ ነገራችንን የማጣት ያህል የሚቆጠር ነው፡፡ በብዙዎችም ዘንድ የሚታወቀው ሐቅ በእዛ አካባቢ የሚኖሩት አብዛኞቹ አፋሮች መሆናቸው ናቸው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በአፄ ኃይለሥላሴና በደርግ ዘመን የነበረውን የባሕር ኃይሉን ሁኔታ ልዩነቱ የሚገለጸው እንዴት ነው?**

**ካፒቴን መርሻ፡-** በደርግ ጊዜ ኦፊሰሮችን ለማቅረብ ፈቃደኛ አልነበረም፡፡ ደርግ ሥልጣኑን ከተረከበ በኋላ በኃይለሥላሴ ዘመን የነበሩትን የባሕር ኃይል አካላትን በጥርጣሬ የሚያይ ነበር፡፡

ደርግ ሥልጣኑን ከተረከበ ከጥቂት ዓመታት በኋላ ማለትም በ1970 ዓ.ም አካባቢ እኔ ተይዤ ወደ አዲስ አበባ መጣሁ፡፡ አዲስ አበባ ከገባሁ በኋላ ደግሞ አጋጣሚ ሆኖ በመታመሜ ሆስፒታል ገባሁ። በዚያን ጊዜ አዲስ አበባ የነበረውን የባሕር ኃይል ወደ አሥመራ ወሰዱት፡፡ እንደ እኔ አመለካከት ከሆነ እንደዛ መሆን አልነበረበትም፡፡ ይህ ሁሉ የእብደት ሥራ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ እኔ ወደኋላ ላይ ወደመከላከያ ውስጥ ገባሁ፡፡ እዛም ብዙ ሳልቆይ እንደገና ከመከላከያ አንስተውኝ በምክትል አዛዥነት ማዕረግ ወደ ምፅዋ መልሰው ላኩኝ፡፡

በእርግጥ ሰው መመረጥ ያለበት በችሎታው ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡ በወቅቱ አስቀድሜ ጠቆም ለማድረግ እንደሞከርኩት ደርግ ደግሞ ካድሬ የተባለውን ሁሉ ሾመ፡፡ ደርግ የራሱ የሆነውን ሰው እያመጣ ይህኛው ቦታ ለዚህ ሰው በሹመት ተሰጥቶታል ይል ነበር፡፡ ያኛው ቦታ ደግሞ ለዚያኛው ሰው እያለ የእኔ የሚላቸውን ሲሾም ቆየ፡፡ መሆን የነበረበት በዘርፉ ትክክለኛ እውቀት ያለውና ለሹመቱም ብቁ የሆነ ሰው ነበር፡፡ ነገር ግን ደርግ ያንን ማድረግ አልወደደም፡፡

ምንም እንኳ ደርግ የራሱን ሰው እያመጣ ሹመት እንዲሰጠው ቢያደርግም፤ እኔ ካፒቴን የሆንኩት በዚያው በደርግ ዘመን ነው፡፡ ለቦታው የሚጠይቀውን እውቀት በማሟላቴ ካፒቴን ልሆን ችያለሁ፡፡ በጃንሆይ ጊዜ ደግሞ ኮማንደር ነበርኩ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በወቅቱ የነበረው የባሕር ኃይል ከሰው ኃይሉ በተጨማሪ የመሣሪያ ሁኔታ ምን ይመስል ነበር?**

**ካፒቴን መርሻ፡-** ኢትዮጵያን ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በሚመሩበት ዘመን ኃይለኛ ባሕር ኃይል ነው የሚባለው የግብፅ እና የኢትዮጵያ ነው፡፡ በዚያን ወቅት የመን ባሕር ኃይል የለውም፡፡ እኛ በወቅቱ ወደ ሳዑዲ ዓረቢያ ለጉብኝት ስንሄድ መርከብ አቁመው ነው፡፡ ወደብ አልነበራቸውም፡፡ በወቅቱ እንዲያውም ከተማ ውስጥ ስንቀሳቀስ በከተማቸው ውስጥ የአማርኛ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# “ኢትዮጵያ የባሕር በር ማግኘቷ ወደ...

ከ6ኛው ገጽ የዞረ

ተናጋሪዎች በርከት ያሉ እንደነበር አስታውሳለሁ። የመንን አልኩ እንጂ እነሶሪያም ሆኑ ሊቢያ በዚያን ወቅት የላቸውም፡፡

ከዚህ አንጻር ሲታይ ሀገራችን ኢትዮጵያ ትልቅ ሀገር ናት፡፡ ትልቅነቷ ደግሞ ጠቀሜታው ለእርሷ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም የአፍሪካ ሀገራት ጭምር ነው፡፡ በጥንት ጊዜ ብቻ ሳይሆን በቅርብም ለጎረቤት ሀገራት የምታደርገው አስተዋፅዖ በቀላሉ የሚመዘን አይደለም። ሌላው ቀርቶ ደቡብ ሱዳንን ያሠለጠንን እኛ ነን፡፡ ከሠላሙም አንጻር ስንታይ ኢትዮጵያ የሌላውን ሠላም ለመንሳት ይቅርና በሌላ ኃይል አማካይነት የታጣን ሠላም በማስመለስ ረገድ ሚናዋ ላቅ ያለ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የባሕር ኃይሉንም ሆነ የባሕር በሩን አስፈላጊነት እንዴት አዩት?**

**ካፒቴን መርሻ፡-** ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ባሕር ኃይል ያስፈልጋል ማለታቸው መልካም ነው፡፡ ኢትዮጵያ ቀድሞም ቢሆን የባሕር ኃይል የነበራት ሀገር መሆኗ ግልጽ ነው፡፡ ከባሕር ኃይሉ ጎን ለጎን ደግሞ በኢኮኖሚያችንም ማደግ አለብን። ባሕር ኃይሉም ሆነ የየባሕር በሩ ሲታሰብ አብረው መታወስ ያለባቸው በርካታ ጉዳዮች አሉ። ከእነዚህ ውስጥ አንዱ የባሕር በሩን የማግኛ ስልት ነው። ለምሳሌ ኤርትራን መውሰድ እንችላለን፡፡ ኤርትራ የእርሻ መሬት የላትም፡፡ በዚያ ላይ ደግሞ ወደቡን እምብዛም አትጠቀምበትም፡፡ ካልተጠቀመችበት በብዙ መንገድ ልታተርፍ የምትችለው የባሕር በርና ወደብ ለኢትዮጵያ በማቅረብ ነው፡፡ በዚህ መላ መጠቀም ብትችል ለእርሷ መልካም ነበር፡፡

የባሕር በር እንዳልኩት ነው፤ አስፈላጊነቱ አጠያያቂ አይደለም፡፡ ኢትዮጵያ በአህጉሯ ያላት ተሰሚነትም ሆነ ታላቅነት እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ የባሕር በር ደግሞ ሲታከልበት ምን ያህል ልትተልቅ እንደምትችል መገመት አይከብድም፡፡ ደግሞም የብዙ ሕዝብ ባለቤት ናት፡፡

ስለዚህም ባሕር ኃይል ያስፈልገናል፡፡ ቀድሞም ቢሆን የሰጠነው ራሳችን ነን፡፡ በወቅቱ ጅቡቲ የእኛ ነበር፤ ደርግ ወስዶት ቢሆን ኖሮ ችግር አልነበረውም። ጅቡቲንም ምፅዋንም የሰጠነው እንደዚያው ነው። እንዲያም ሆኖ በአሁኑ ወቅት ጥያቄው ተነስቷል፡፡ ተነስቶ ብቻ አይቀርም፤ መልሰን የባሕር በር ማግኘት እንችላለን የሚል አመለካከት አለኝ፡፡ ነገር ግን አንድ ነገር መጠየቅ ተገቢ ነው፡፡ ኤርትራ እና ኢትዮጵያ ልዩነታቸው ምንድን ነው? ከባሕልም ከትስስርም አንጻር ሲታይ ልዩነት የለንም፡፡ ለበርካታ ዓመታትም አብረን ኖረናል፡፡ ስለዚህ ለሁለቱም ሀገራት አዋጭው አብሮ መሥራት ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የባሕር ኃይሉን ለማቋቋም ከቀድሞው የባሕር ኃይል ሰዎች የተመረጣችሁ ምን ያህል ሰዎች ናችሁ? ያካፈላችሁት ልምድ ምንድን ነው? የተጠራችሁትስ በማን ነበር?**

**ካፒቴን መርሻ፡-** ጥሪው ደርሶን የነበረው ከጥቂት ዓመታት በፊት ነው፡፡ በእርግጥ ከቀድሞዎቹ የባሕር ኃይል አባላት በመጀመሪያ የተጠራሁት እኔ ነኝ፡፡ ጥሪውም የደረሰኝ በመከላከያ አማካይነት ነው፡፡ በወቅቱ ሊያነጋግረኝ የመጡት ሰው ባሕር ኃይል ማቋቋም እንደሚፈልጉ አጫወቱኝ፡፡ እኔም እንዴት አድርጋችሁ ለማቋቋም ፈለጋችሁ ስል መልሼ ጠየቅኩት፡፡ እርሱም ማቋቋም የምንፈልገው በብርጌድ፣ በጄኔራል እያለ ገለጸልኝ፡፡ እኔም መልሼ ይህ እኮ ጦር ሠራዊት አይደለምና እንዴት ተደርጎ ነው እንደዚያ የሚሆነው ስል አስተያየቴን ሰጠሁ። በጉዳዩ ላይ ተነጋገርን፡፡ ቀጥሎም ሌሎች የቀድሞ የሥራ ባልደረቦቼን ጭምር ጠሩን፡፡ እኛን ሲጠሩን በወቅቱ በመከላከያ ሚኒስትርነት መሥሪያ ቤቱን ሲመሩ የነበሩት ኢንጂነር አይሻ ሲሆኑ፣ በወቅቱ ስለእኛ የነበራቸው ግንዛቤም በጣም ግሩም ነው፡፡

በመሆኑም ከሚመለከታቸው ጋር ተወያየን፤ የመጀመሪያው ነገር እኛ የዘርፉን መቋቋም ሁኔታ መጀመር የፈልግነው ከስር ነው፡፡ ኦፊሰሮቹ ደግሞ ያንን አልወደዱትም፡፡ በወቅቱ ደግሞ ከባሕር ኃይል ሌላ አማካሪ ነበራቸው፡፡ እንዲያም ሆኖ በወቅቱ የነበሩት ሚኒስትር ስለጉዳዩ እውቀት ነበራቸውና በመምጣታችን እና ለማማከር ዝግጁ በመሆናቸው ደስተኛ ነበሩ፡፡

በወቅቱ በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ባሕር ኃይል ዋና አዛዥ ሪር አድሚራል ክንዱ ገዙ ጋርም ተገናኘን፡፡ እና የሚያስፈልገው ነገር ከማክሮ ጀምሮ እንደሆነ ለመግለጽ ሞከርን፡፡ ይህ ማለት ባሕር ኃይልን ከመሠረቱ፣ ከትምህርት ቤቶቹ፣ ለየማዕረጉ ከሚሰጠው የትምህርት አይነትና ትምህርቱ ለምን ያህል ጊዜ የሚሰጥ ስለመሆኑ ለሦስት ዓመት ሙሉ ካሪኩለም አዘጋጀን፡፡

እኛ በአዲስ መልክ ለተቋቋመው የባሕር ኃይል ከመሠረቱ ጀምሮ በጠቀስኩት ልክ በየደረጃው ለሚሰጠው የትምህርት ዘርፍን ጨምሮ ለሦስት ዓመት የሚሆን ካሪኩለም እናዘጋጅ እንጂ ቀጣይ የሚሆነው ሐሳባቸውን ብዙ አላወቅም፡፡ እንደየዘርፋቸው ግን ብቁ የሚሆን የሰው ኃይል እንዲኖራቸው ስለፈለጉ ይመስለኛል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ደንብና ሥርዓቱንም (ሬጉሌሽን) ያዘጋጀን ሲሆን፣ እሱን ገና አልሰጠናቸውም።

**አዲስ ዘመን፡- ደንብ እና ሥርዓቱን ያልሰጣችኋቸው ባለመጠናቀቁ ነው?**

**ካፒቴን መርሻ፡-** እንደእሱ አይደለም፤ የሠራነውን ሰጥተናቸዋል፡፡ የሚፈልጉንን ያህል ቆይተናል፡፡ ከዚያ በኋላ ግን የማናስፈልግ በመሆናችን በዚያው ቀረን፡፡ በእርግጥ በብዙ ሁኔታ የመከርን ቢሆንም ያዘጋጀነውንም ደንብ ግን አልሰጠናቸውም። ደንቡን ያዘጋጀነው አራት ሰዎች ስንሆን፣ አንደኛውን አጋራችንን ሕይወቱ ያለፈው በቅርቡ ነው፡፡ አንደኛውም ትንሽ አመም አድርጓቸዋል፡፡ እኔ እና ኮሞዶር ጥላሁን መኮንን አለን፡፡ ያጠናቀቅነውም ሁለታችን ነን፡፡ የሠራነው ሰፋ ያለ ደንብና ሥርዓት በመሆኑም ሲጠይቁን ለመስጠት ዝግጁዎች ነን፡ ከዚህ ባሻገር በርካታ ሥራ ሰጥተናቸዋል፤ አማክረናቸዋልም።

**አዲስ ዘመን፡- በጽሑፍ ያዘጋጃችሁትን ገና አልሰጣችሁም ማለት ነው?**


**ካፒቴን መርሻ፡-** እሱማ በጽሑፍም ሰጥተናል፡፡ በወቅቱ እንዲያውም መመሪያውን እያዘጋጀን ባለንበት ወቅት ለምሳሌ እነርሱ 30 ሰዎችን አምጥተው ነበር። እኛም ግንዛቤ ሰጠናቸውና ራሽያ ለስድስት ዓመት ትምህርት እንዲማሩ ተላኩ፡፡ በእርግጥ በአሁኑ ወቅት ይምጡ አይምጡ አላውቅም፡፡ በወቅቱ ከመሄዳቸው በፊት ግን ገለጻ እንድናደርግላቸው ባዘዙን መሠረት ያለውን ሁኔታ በአግባቡ ገለጻ አድርገንላቸዋል፡፡ እነዚህ ሰዎች ተምረው መጥተው ከሆነ በዘርፉ መሥራት በሚያስችላቸው ላይ ነው መመደብ ያለባቸው ባይ ነኝ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ የባሕር በር ለማግኘት በርካታ አማራጮችን እያማተረች ነው፤ ይሄንን እንዴት ያዩታል?**

**ካፒቴን መርሻ፡-** እኔ ኢትዮጵያ መቼም ቢሆን የባሕር በር ታጣለች የሚል አመለካከት የለኝም፡፡ ሁሌም ቢሆን ልቤን የሚሞላው የባሕር በር ታገኛለች የሚለው ሐሳብ ነው፡፡ ምክንያቱም ኢትዮጵያ የባሕር በር የግድ ማግኘት አለባት፡፡ ነገር ግን ይህን የባሕር በር ለማግኘት ጥበብ ያስፈልገዋል፡፡ ለምሳሌ ምሥራቅ አፍሪካን ብንወስድ ሱማሊያ፣ ኬንያ፣ ሱዳን፣ ኤርትራ ስምምነት ፈጥረው አብረው መሄድ የሚችሉ አገራት እንደሆኑ አስባለሁ፡፡ ስለዚህ አማራጩ የየሀገራቱ ስምምነት ነው ባይ ነኝ፡፡

ምፅዋ የኢትዮጵያ ግዛት የነበረ ነው፡፡ በወቅቱ በጣሊያን ይወሰድ እንጂ የእኛ የኢትዮጵያውያን ነው፡፡ ለምሳሌ ቮሊቢያን ብንወስድ የባሕር በር የሌላት አገር ናት፡፡ ይሁንና አሁንም የባሕር ኃይል አላት፡፡ ስንት ዓመት ሆናት ባሕር ኃይል ካቋቋመች? እስካሁን ግን የባሕር ኃይል ይዞታ አላገኘችም፡፡ አሁን ግን በተወሰነ ደረጃም ቢሆን በር ሊከፍቱላቸው ነው፡፡ ስለዚህ የኢትዮጵያም እንዲሁ ነው፡፡ ኢትዮጵያ የባሕር በር የምታገኘው ደግሞ በጉልበት ሳይሆን ሠላማዊ በሆነ መንገድ ነው፡፡መንግሥት ከሶማሊ ላንድ ጋር የደረሰበትም ስምምነት ሠላማዊነቱን የሚመለከት ነው፡፡

በተለይ ደግሞ በሌላ መንገድ ሌላ አማራጭ ሊሆን የሚችለው ከመሪዎቹ ባሻገር የኢትዮጵያ እና የኤርትራ ሕዝብ ፍላጎቱ ምንድን ነው? የሚለው ጉዳይ መጤን አለበት፡፡ ሕዝቡ አሁንም ቢሆን እንደ አንድ ቤተሰብ የሚቆጠር ነው፡፡ ትግራይና ኤርትራ ልዩነት የላቸውም። የአንዱ አባት እዛ የሌላው እናት እዚህ ነው ማለት ይቻላል፡፡



**አዲስ ዘመን፡- በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ከወጣው ከዓለም አቀፍ ሕግ አኳያ ያለውን ሁኔታ እንዴት አዩት?**

**ካፒቴን መርሻ፡-** ዓለም አቀፍ ሕጉ አንድ የባሕር በር ያለው አገር ስምምነት ላይ በተመሠረተ ሁኔታ ባሕር ሕግ እንዲያገኝ ይፈቅዳል፡፡ ደግሞም ኤርትራም ሆነች ጅቡቲም ሆነች ሌላው ጎረቤት አገር የኢትዮጵያ ባሕር በር ማግኘት እነርሱኑ የበለጠ የሚጠቅም መሆኑን መዘንጋት የለባቸውም፡፡ የአንዱ የጎረቤት ሀገር የኢኮኖሚ እድገት ለሌላውም ጎረቤቱ የሚተርፍ መሆኑን መዘንጋት የለባቸውም፡፡ ሕጉም ቢሆን ከዚህ አንጻር ሲታይ የሚደግፈው ነው፡፡

ምክንያቱም እንኳን ኢትዮጵያ ይቅርና ቻይና፣ አሜሪካ፣ ፈረንሳይ እና ሌሎችም ከተለያየ አካባቢ ያውም በብዙ ሺ ኪሎ ሜትር ተጉዘው መጥተው በቀይ ባሕር አካባቢ መሆናቸው ሊዘነጋ አይገባም። እንዲያውም ለኢትዮጵያ ባሕር ኃይል መልሶ ማቋቋም ወቅት ከፈረንሳይ ሰው ወደ እኛ መምጣት አልነበረበትም የሚል አመለካከት አለኝ፡፡ ምክንያቱም ፈረንሳዮች ጅቡቲን በቅኝ ሲገዙ የነበሩና አሁንም ድረስ አብረዋቸው ያሉ መሆናቸው ሊዘነጋ አይገባም ፡፡

አሁን ቀይ ባሕር ለሁሉም ለአካባቢው ሀገራት ስጋት እየሆነ ነው፡፡ ይሁንና ራሽያ፣ ኢራን፣ ቻይና እና አሜሪካ ሁሉ ባሉበት ኢትዮጵያ የት አለች? ኬንያ አብዛኛው ጊዜ ግንኙነት ያላት ከእንግሊዞች ጋር ነው። ስለዚህ ከእነርሱ ጋር ልታብር ትችላለች፡፡፡ ሱማሊያ ደግሞ ቀድሞም ቢሆን ለኢትዮጵያም እምብዛም ወዳጅ የምትባል አገር አይደለችም፡፡ ስለዚህ ቀይ ባሕር ላይ መብቱ እንዳይኖረን ከተደረገ እና የወደብ ተጠቃሚነታችንን ገለል የሚያደርጉ ከሆነ እንዴት እና ምን ሊሆን እንደሚችል ማሰቡ ብቻ በቂ ነው፡፡

ስለዚህ የባሕር በሩን በስምምነት መርሕም ሆነ በሕግም ጭምር መጠየቅ እንችላል፡፡ ጎን ለጎን ደግሞ በዲፕሎማሲያዊ መንገድ መሄድ እንችላለን፡፡ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እንደተናገሩት፤ ወደብም ሆነ የባሕር በር የምንሻው በጦርነት አለመሆኑ ነው፡፡ የጦርነት አማራጭ የሚያዋጣ አይሆንም፡፡ ምክንያቱም ማን ከማን ጋር ይገዳደላል? ይህን መረዳት ተገቢ ነው፡፡ አንዱ ሌላውን ባከበረ መንገድ የሚሠራ ሥራ ውጤታማ ስለመሆኑ አያጠራጥርም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በዚህ አጋጣሚ የሚያስተላልፉት መልዕክት ይኖርዎ ይሆን?**

**ካፒቴን መርሻ፡-** ግራም ነፈሰ ቀኝ የባሕር በር ማግኘት አለብን፡፡ ኢትዮጵያ ትልቅ አገር ናት። ዳር ድንበሯ ዛሬ ላይ ያለው ሳይሆን እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ድረስ የሚዘልቅ እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ይናገራሉ። ስለሆነም ይህች ታላቅ አገር የባሕር በር ማግኘት የግድ ይላታል፡፡ የማግኛ ዘዴው ደግሞ በርካታ ሲሆን፣ ሕጋዊም ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ነው። ይሁንና እኛ ማግኘት የምንፈልገው ሕጋዊ በሆነ መንገድ ሲሆን፣ እሱም በመስማማት ነው፡፡

ምክንያቱም ጦርነት መቼም ቢሆን አዋጭ አይሆንም፡፡ በቀጣይም ቢሆነም ማን ወዳጅ ማን ጠላት ነው የሚለውን በአግባቡ መለየት መልካም ነው። ወዳጅ መስለው መሣሪያ የሚሸጡ በርካታ ናቸው፡፡ ስለሆንም ኢትዮጵያ አንድነቷን ጠብቃና ሠላሟን አስጠብቃ በኢኮኖሚዋ የተዋጣላት ልትሆን ይገባታል፡፡ ሕዝቡ ደግሞ ከዚህ ጎን ለጎን ራሱ እያለማ እና ለሠላም ዝግጁ እየሆነ መጓዝ ይጠበቅበታል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ለቃለ ምልልሱ ፈቃደኛ ስለሆኑ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡**

**ካፒቴን መርሻ፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

# ተናጋሪው ዶሴ

# ከሞት ፍርድ እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ያስቀጣው የውንብድና ወንጀል

አስመረት ብሥራት



ሠርቶ ማግኘት አግኝቶ የተሻለ ሕይወት መኖር የብዙ ሰዎች ሕልም ነው። ሰዎች መኖር ለሚፈልጉት የምቾት ኑሮ ሲሉ ያዋጣኛል ያሉትን መንገድ በሙሉ ይከተላሉ። ገሚሱ ጥሮ ግሮ በላቡ ያፈራውን ሀብት ለመጠቀም ሲነሳ ገሚሱ ደግሞ ያለፋበትን ሀብት ለማጋበስ ሲጥር ይታያል። ይህን ሀሳብ ያነሳነው ከአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን የተዘጋ ዶሴ አገላብጠን ያገኘነውን ታሪክ ልናካፍላችሁ ስለወደደን ነው።

ወጣቶች ናቸው። ያለፉበትን ጥሪት መሰብሰብ ሕልማቸው የሆኑ ቀማኞች ናቸው በአንድ ላይ የተሰበሰቡት። ሁሉም ያለድካምና ልፋት የገንዘብ ቁልል ውስጥ መዋልና ማደርን ነው ዓላማ ያደረጉት። ሕልማቸውን እውን ለማደረግ ከማስፈራራት እስከ መግደል የሚደርስ የዱርዬዎች ቡድን ነው። እንደ ጣሊያኖቹ ማፊያዎች የሚፈሩ፤ ሁሉን ነገር በጉልበት የሚያደርጉ የጭካኔ ጥግ ድረስ ሲሄዱ ምንም የማይጎረብጣቸው ናቸው።

ሁሉም በጠዋቱ የወጣትነት እድሜ ክልል ላይ የሚገኙ በባዶ ጉራ እራሳቸውን ወጥረው በውድ ልብሶች መድመቅ፤ ውድ ጌጦችን ከማድረግ አንስቶ ውድ መኪናዎችን ለመንዳት በመመኘት ያገኙትን ሁሉ መንጠቅና መዝረፍ ተቀዳሚ ሥራቸው ሆነ።

አንድ አይነት ክንፍ ያላቸው ወፎች አንድ ላይ ይበራሉ እንደሚባለው የተለያየ አካባቢ ተወልደው ቢያድጉም፤ ከተለያየ አይነት የኢኮኖሚ ደረጃ ካላቸው ቤተሰቦች ቢፈጠሩም ሕልምና ፍላጎታቸው አንድ አይነት ሊያውም በሰው ላብ መክበር ነውና ማንም ነጋሪ ሳያስፈልጋቸው ተስማምተው ወደ ሥራ ገብተዋል።

የተገናኙት ሁሉም ተሰብስበው የሚቅሙበት ጫት ቤት ውስጥ ነው። በተለያየ አጋጣሚ ወደ ጫት ቤቱ የመጡት እነዚህ ወጣቶች ስሜትና ፍላጎታቸውን እየለዩ በአንድ ተሰባስበው ደርዘን ሞልተዋል። የነጠቁትንም ፤የቀሙትንም በሙሉ ይዘው እዛው በመምጣት የሚሸጠው ተሽጦ እንደ ሀብታም መኖርን ይለማመዱበታል።

የምቾት ሕይወት ልምምዳቸውን በዘረፉት ገንዘብ አጠናክረው የቀጠሉት ወጣቶች ሠርቶ ለማግኘት ማቀዳቸው ትተው የሰውን ሀብት እንዴት የራሳቸው ማድረግ እንደሚችሉ በማሰብ ጭንቅላታቸውን ወጥረው ይውላሉ።

አቤል ኢሳያስ ተስፋዬ፣ አቤል አዋየው አሊ፣ አቤል ግደይ በረኸ፣ ሀብታሙ ወንድሙ ገብረየስ፣ ዳንኤል ጎይቶም ተስፋዬ ፣ ናትናኤል ግደይ በረኸ፣ ዳንኤል ዮሐንስ ገብረ መድን፣ ዮናስ ፍፁም ከበደ፣ ናትናኤል ረዳኢ ኪሮስና ሌሎች አንድ ላይ በመሆን ውድ ሆቴሎች ሀብታሞች የሚውሉበት መዋል ያዘወትሩ ነበር። ይህን ማድረጋቸው ደግሞ የተሻለ ገንዘብ ያለው ተዘራፊ ለማግኘት ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥርላቸው ይናገራሉ።

ከዚህ ቀደም እንደ ጓደኛ የቀረቡትን የመኪና መለዋወጫ ባለቤት አጭበርብረውና አደንዝዘው ጥሪቱን በሙሉ ወስደዋል። ማንም ሳይደርስባቸው የተለያዩ ጥበቦችን እየተጠቀሙ የሰው ገንዘብን ማራቆት የለመዱት እነዚህ ቀማኞች ውሎ እያደር ፍላጎታቸው በመጨመሩ የተነሳ ጠንከር ያለ የዘረፋ አቅድ በማውጣት ሕይወትን ሊቀይር የሚችል ስርቆትን ለመስረቅ አቀዱ።

ለዘረፋው ሥራ አመች እንዲሆን ባለፀጋዎች የሚውሉበትን ቦታ በማዘወተር ማንን ቢዘርፉ የተሻለ ገቢ ሊያገኙ እንደሚችሉ ማቀድ ጀመሩ። በላባቸው ያላመጡትን ገንዘብ በመበተን ሀብታም መስሎ በመታየት፤ ከሰዎች ጋር በመቀራረብ የተለያዩ መረጃዎችን ማሰባሰብ ጀመሩ። በዚህም ከባለፀጋዎቹ መካከል አምስቱን ለይተው ብዙም ዋጋ ሳያስከፍል ሊዘረፍ የሚችል ሰው ለማግኘት ጥረት ማድረግ ጀመሩ። በቀላሉ እጅ ውስጥ ለማስገባትም አለኝ የሚሉትን ምርጥ አማራጭ ሁሉ ለመጠቀም ወሰኑ።

### የተጠናው የዘረፋ እቅድ

አቶ ኪዳነ ማሪያም ወልዱ በተለያዩ የንግድ ዘርፎች ላይ ተሠማርተው ሀብት ያካበቱ ሀብትን በሀብት ላይ ለመደረብ ሥራን አማራጫቸው ያደረጉ ታታሪ ግለሰብ ናቸው። እኚህ ሰው ለመዝናናት ፀጥ ያሉ ውስኪ ቤቶችን ምርጫቸው ያደርጉ ነበር።

ሁካታ የበዛበት ቤት ምቾት ስለማይሰጣቸው በዝግ የሚያስጠቅሙ ትልልቅ ውስኪ ቤቶች ውስጥ ያጠመደ አያጣቸውም ነበር። ያኔ ለዘረፋ እቅዳቸው ምቹ ሰው ሲፈልጉ የነበሩት የዘረፋ ቡድን አባላት ወደ ውስኪ ቤቱ ሲመላለሱ ነበር ያገኟቸው። ወዳጅ መስለው ቀርበው የሀብታቸውን ልክ ሲያጠኑ ከቆዩ በኋላ ለዘረፋ ምቹ እቅድ ያወጡላቸው ጀመር።

ለቀናት አቶ ኪዳነ ማሪያም ቤት አካባቢ የመሸገው የዘረፋ ቡድን በምን ሰዓት ጥበቃ እንደሚላላ በማጥናት ለዘረፋ ምቹ የሆነውን ሰዓት አጥንተው ጨረሱ። ጥናቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ለጉዳዩ ማስፈፀሚያ የሚሆን ግብዓት ለማሟላት መዘጋጀት ጀመሩ።

የዘረፋ ቡድኑ አባላት የተጠናውን እቅድ አዘጋጅተው ከጨረሱ በኋላ ነበር አልባሳትን። የጦር መሣሪያዎችንና ተሽከርካሪን ማዘጋጀት የጀመሩት። ዛሬ ላይ ዝግጅቱ ተጠናቆ ለዘረፋ የሚሆን ሙሉ ትጥቅ ያሟላ የማፊያ ቡድን ተፈጠረ። ይህ ቡድን ሕልሙን እውን ለማድረግ በጊዜ ተኝቶ በሌሊት ለመንቃት ተዘጋጅቷል።

### ዘረፋ

ሙሉ ትጥቁን ያሟላው የዘረፋ ቡድን በደንብ የተዘጋጀ እራት በልቶ መጠጥ ብጤም ቀማምሶ ሙሉ ትጥቁን አሟልቶ ግዳዩን ወደ ሚጥልበት ቦታ ተንቀሳቀሰ። እለቱ ታኅሣሥ 16 ቀን 2014 ዓ.ም ነበር። በግምት ከሌሊቱ 9፡30 ሰዓት አካባቢ ሲሆን በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 መሪ 20 ሜትር ጎላጉል አጠና ተራ ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ የተገኘው ይህ ቡድን የሥራ ክፍፍል አድርጎ ዘረፋ ለመፈፀም ወደ አቀደው ቤት ተጠጋ።

የዘራፊው ቡድን የማይገባ ብልጽግና ለማግኘት በማሰብ ሽጉጥ፣ ጩቤ፣ እና ገጀራ ይዘው የግል ተበዳይ መኖሪያ ቤት ግቢ በር ገንጥለው ገቡ። በቡድንና በኃይልና በብዛት ጥቁር ልብስ ለብሰው ነበር በር ገንጥለው ወደ ግቢው ውስጥ የገቡት። በኃይልና በብዛት የገቡትን ዘራፊዎች የተመለከቱት ተበዳዮች በድንጋጤ ከመቆም በስተቀር እራሳቸውን ለመከላከል የሚያስችል ምንም ጥረት ማድረግ አልቻሉም ነበር።

በኃይል ወደ ቤቱ ውስጥ የገቡት ዘራፊዎች ውስጥ የነበሩትን ሰዎች በማስፈራራት ያለውን ንብረት በሙሉ በመለቃቀም ቀድመው ባዘጋጁት ተሽከርካሪ ላይ መጫን ጀመሩ። በዘረፋቸውም አጠቃላይ የዋጋ ግምታቸው 365 ሺ ብር የሚያወጣ የተለያዩ ንብረቶችን በመውሰድ ከአካባቢው ለመሰወር መታተር ጀመሩ።

ከዚህም በተጨማሪ ከላይ በተገለፀው ቀንና ቦታ ከሌላኛው የግል ተበዳይ መኖሪያ ቤት ውስጥ የግቢውን የአጥር ሽቦ በከተር ቆርጠው በመግባትና በማስፈራራት አጠቃላይ የዋጋ ግምታቸው 1 ሚሊዮን 13 ሺ 200 ብር የሚያወጣ የተለያዩ አይነት ንብረቶችን በመውሰድ ከአካባቢው ተሰወሩ።

ዘረፋው እንደተፈፀመባቸው ከድንጋጤ ያቸው መለስ ያሉት ተበዳዮች ለፖሊስ ጉዳዩን ያመለከታሉ። ፖሊስም ጥቆማው ከደረሰው ጊዜ ጀምሮ እነዚህን ዘራፊዎች ዱካ መከታተል ጀመረ። እልህ አስጨራሽ ከሆነ ክትል በኋላ ተጠርጣሪዎቹ በቁጥጥር ስር ዋሉ፡፡

### የፖሊስ ምርመራ

1ኛ አቤል ኢሳያስ ተስፋዬ፣ 2ኛ አቤል አዋየው አሊ፣ 3ኛ አቤል ግደይ በረኸ፣ 4ኛ ሀብታሙ ወንድሙ ገብረየስ፣ 5ኛ ዳንኤል ጎይቶም ተስፋዬ፣ 6ኛ ናትናኤል ግደይ በረኸ፣ 7ኛ ዳንኤል ዮሐንስ ገ/መድን፣ 8ኛ ዮናስ ፍፁም ከበደ፣ 9ኛ ናትናኤል ረዳኢ ኪሮስ የተባሉ ዘጠኝ ተከሳሾች በሁለት ክሶች የተከሰሱ ሲሆን፣ በ1ኛ ክሳቸው ላይ ተከሳሾች የማይገባቸውን ብልጽግና ለማግኘት በማሰብ ታኅሣሥ 16 ቀን 2014 ዓ.ም በግምት ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ተኩል አካባቢ ሲሆን በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 መሪ 20 ሜትር ጎላጉል አጠና ተራ ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ ካልተያዙ ግብረ-አበሮቻቸው ጋር በመሆን ሽጉጥ፣ ጩቤ፣ እና ገጀራ ይዘው የግል ተበዳይ መኖሪያ ቤት ግቢ በር ገንጥለው ገብተዋል።

ከዛም ወደ ውስጥ በመግባት ተበዳዮችን በማስፈራራት አጠቃላይ የዋጋ ግምታቸው ሦስት መቶ ስልሳ አምስት ሺ ብር የሚያወጡ የተለያዩ ንብረቶችን ወስደዋል። ከዚህም በተጨማሪ በ2ኛ ክስ ላይ ከላይ በ1ኛ ክስ በተገለፀው ቀንና ቦታ ከሌላኛው የግል ተበዳይ መኖሪያ ቤት ውስጥ የግቢውን የአጥር ሽቦ በከተር ቆርጠው በመግባትና በማስፈራራት አጠቃላይ የዋጋ ግምታቸው 1 ሚሊዮን 13 ሺ 200 ብር የሚያወጣ የተለያዩ አይነት ንብረቶችን በመውሰድ ከአካባቢው ተሰውረው ፖሊስ ባደረገው ክትትል የተያዙ በመሆናቸው በፍትሕ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ የልዩ ልዩ ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ሕግ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን በፈፀሙት የከባድ ውንብድና ወንጀል ክስ መሥርቶባቸው ክርክር ሲደረግ ቆይቷል።

### የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የክስ ዝርዝር

የክርክር ሂደቱ የታየውም በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 1ኛ የሰው ግድያና ከባድ ውንብድና ወንጀል ችሎት ሲሆን በችሎቱም የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ከተሰማ በኋላ ተከሳሾች እንዲከላከሉ ብይን ተሰጥቶ የመከላከያ ምስክሮችን አቅርበው እንዲያሰሙ ቀጠሮ ቢሰጣቸውም የመከላከያ ምስክር ባለማቅረባቸው ፍርድ ቤቱ የመከላከል መብታቸው ታልፎ በተከሳሾች ላይ የጥፋተኛነት ፍርድ ሰጥቷል።

### ውሳኔ

በተሰጠው የቅጣት ውሳኔ መሠረትም 1ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች በሌሉበት በሞት እንዲቀጡ፣ 2ኛ እና 5ኛ ተከሳሾች በሌሉበት በእድሜ ልክ ጽኑ እስራት፣ 9ኛ ተከሳሽ በሌለበት በ16 ዓመት ከ6 ወር ጽኑ እስራት፣ 3ኛ እና 8ኛ ተከሳሾች በሌሉበት በ16 ዓመት ጽኑ እስራት፣ እንዲሁም 6ኛ እና 7ኛ ተከሳሾች ቀርበው በ15 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡

ኢኮኖሚ

## ስኬት

# በዳበረ ልምድና ዕውቀት የተጀመረው እልፍ መኖ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

የእንስሳት ምርትን ለማሳደግ የመኖ ልማትና ሥነ አመጋገብን ማሻሻል ቀዳሚው እርምጃ ነው። በመኖ ልማት ዘርፍ የተሰማሩ ሙያተኞች በሀገሪቱ እየተበራከቱ የመጡትም በዚሁ ምክንያት ነው፡፡ እነዚህ ሙያተኞች ለዘርፉ እያበረከቱ ያለው አስተዋጽኦ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም፡፡ ሙያተኞቹ ለእንስሳት አርቢው አርሶ አደርና አርብቶ አደር እየፈጠሩ ባሉት ግንዛቤ የተቀነባበረ የእንስሳት መኖ የመጠቀም ልምድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየዳበረ መጥቷል፡፡

ይሁንና በሀገሪቱ ያለው የተመጣጠነ የእንስሳት መኖ አቅርቦት ካለው ፍላጎት ጋር ሲነጻጸር አጥጋቢ አለመሆኑ በስፋት ይነገራል፡፡ ለዚህም ዋናው ምክንያት በዘርፉ የሚስተዋሉ በርካታ ችግሮች በመኖራቸው ነው፡ ችግሮቹ ቢኖሩም ታድያ ያንን በመቋቋም የእንስሳት ምርትና ምርማነትን ለማሳደግ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እያበረከቱ የሚገኙ አምራች ድርጅቶች አልታጡም፡፡ ከእነዚህ መካከል የተቀነባበረ የእንስሳት መኖ እያቀረበ የሚገኘው እልፍ ማኑፋክቸሪንግና ኮሜርሻል አንዱ ነው፡፡

እልፍ ማኑፋክቸሪንግና ኮሜርሻል እንደ ሀገር በእንስሳት ሀብት ላይ እየተሰራ ያለውን ሥራ ውጤታማ ለማድረግ ከሚታትሩ ድርጅቶች መካከል ተጠቃሽ ነው። የድርጅቱ መስራችና ሥራ አስኪያጅ አቶ ቻላቸው ለገሰ በወጣትነት የዕድሜ ክልል ውስጥ ያለና ከእንስሳት ጋር ጥብቅ ቁርኝት ካለው አርሶ አደር ቤተሰብ የተገኘ ወጣት ነው፡፡ «ከአርሶ አደር ቤተሰብ እንደመውጣቴ ለእንስሳት ቅርብ ነኝ» የሚለው አቶ ቻላቸው፤ ተወልዶ ባደገበት በምዕራብ ጎጃም ፍኖተ ሰላም ዳሞት ላይ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ተከታትሏል፡፡

ከትምህርት ጎን ለጎን እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ በግብርና ሥራ የተሰማሩ ቤተሰቦቹን ማገዝ ተቀዳሚ ተግባሩ ነበር፡፡ በዚህም ለግብርና ሥራ እንዲሁም ለእንስሳት ልማት ቅርብ ሆኖ አድጓል፡፡ አርሶ አደር ከሆኑ ወላጆቹ በተጨማሪ በንግድ ሥራ የተሰማሩ ቤተሰቦቹን የማየት ዕድል ገጥሞታል፡፡ ለዚህም ነው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ባጠናቀቀ ማግስት ወደ ሥራ ያቀናው። «ከትምህርት ይልቅ ወደ ንግድ ሥራ እንዳዘነብል በንግድ ሥራ የተሰማሩት ዘመዶቼ ምክንያት ሆነውኛል» የሚለው አቶ ቻላቸው፤ ገንዘብ መቁጠር የጀመረው ገና በአፍላ የወጣትነት ዕድሜው ክልል ውስጥ ሆኖ ነው፡፡

ቤተሰቦቹ የተሰማሩት በስንዴ፣ በፓስታና በማካሮኒ ምርት ሲሆን፤ በወቅቱ አብሮ ተባብሮ መሥራት መቻሉ ዛሬ ለደረሰበት ደረጃ መነሻ እንደሆነው ይናገራል፡፡ እሱ እንደሚለው፤ በወቅቱ አፍላ የወጣትነት ዕድሜ ላይ በመሆኑ ሰርቶ አይደክመውም፡፡ በሁሉም የሥራ ዘርፎች ውስጥ ገብቶ ሠርቷል፡፡ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል በከፍተኛ ተነሳሽነት ለሚሰራው ሥራ የሚከፈለው ገንዘብ አሳስቦት አያውቅም፡፡ እሱን ያሳሰበው የነበረው ልምድ አዳብሮ ዕውቀት ሰንቆ የተሻለ ሥራ በመስራት ከተቀጣሪነት ወደ ቀጣሪነት መሸጋገር ነበር፡፡

ሃሳቡን ዕውን ለማድረግና በተግባር ለመከወን ያልፈነቀለው ድንጋይ የለም ቢባል ማጋነን አይሆንም። የስንዴ ዱቄት ፋብሪካ ውስጥ በሚሰራበት ወቅት የመኖ ወይም የፉሩሽካን ምንነት በሚገባ ማወቅና መረዳት ችሏል፡፡ ለእንስሳት መኖ ግብዓት መሆን የሚችለውን ጥሬ ዕቃ የማወቅ ዕድሉን በማግኘቱ ወደ ሥራው ለመግባት ብዙም አልከበደውም፡፡ ከፋብሪካው የሚገኘውን ተረፈ ምርት የእንስሳት መኖን በማቀነባበር ሥራ ላይ ለተሰማሩ ፋብሪካዎች ሲያቀብል ኖሯል። ይህን መነሻ በማድረግ የሚያውቀውን ሥራ በግሉ ለመሥራት «ሀ» ብሎ ጀመረ፡፡

ጅማሬው ከፋብሪካው የሚገኘውን ተረፈ ምርት አሰባስቦ ለመኖ አቀነባባሪ ፋብሪካዎች ማቅረብ ነበር። በዚህ ሥራ ውስጥ ታድያ ብዙ እንደተማረና ተጨማሪ አቅም መፍጠር እንደቻለ ነው የሚያስረዳው፡፡ እሱ እንደሚለው፤ ሥራውን በከፍተኛ ጉጉትና ተነሳሽነት በወጣትነት ሙሉ ልቡ ከላይ ታች ብሎ ሰርቷል፡፡ በብርቱ ጥረትና ትጋት መሥራት በመቻሉም ውጤታማ ሆኗል። «ቀስ በቀስ እንቁላል በእግሩ ይሄዳል» እንዲሉ ታድያ ከተረፈ ምርት አቅራቢነት ወደ ፋብሪካ ባለቤትነት የተሸጋገረው አቶ ቻላቸው፤ የፋብሪካ ባለቤት መሆን የቻለው በሙሉ አቅሙ መሥራት በመቻሉና መንግሥት ያመቻቸውን ዕድል አሟጦ መጠቀም በመቻሉ እንደሆነ አጫውቶናል፡፡



አቶ ቻላቸው ለገሰ

እሱ እንደሚለው፤ የአማራ ክልል መንግሥት የኢንቨስትመንት ቦታ ውሰዱ በሚል ያደረገውን ጥሪ ተከትሎ የኢንቨስትመንት ቦታ ወስዷል፡፡ ቦታውን የወሰደው ዱቄት፣ ፓስታና ማካሮኒ ለማምረት ነበር። ይሁንና ወደ ሥራው ከመግባቱ አስቀድሞ የተለያዩ ጥናቶችን አድርጓል፡፡ ባደረገው ጥናትም ከለገጣፎ ጀምሮ እስከ ሰሜን ሸዋ ሸዋሮቢት ድረስ ትላልቅ የእንስሳት እርባታዎች መኖራቸውን ማረጋገጥ ችሏል። አብዛኞቹ እርባታዎችም የወተት ላምና የዶሮ እርባታዎች ናቸው፡፡ ለእነዚህ እርባታዎችም በቀን ምን ያህል መኖ እንደሚያስፈልግና እያቀረበ ያለው ደግሞ ምን ያህል እንደሆነ መረጃ አሰባስቧል፡፡ ያሰባሰበው መረጃም በአካባቢው የእንስሳት መኖ አቅርቦት እጥረት መኖሩን አረጋግጦለታል፡፡

ይሄን ጊዜ ነው የሥራ ዘርፉን የመቀየር ሃሳብ የመጣለት፡፡ የኢንቨስትመንት ፈቃዱን የእንስሳት መኖ ማቀነባበር በሚል መቀየር የቻለው አቶ ቻላቸው፤ የእንስሳት መኖ የማቀነባበር ሥራውን አስቀድሞ ጥሬ ዕቃ በማቅረብ ያውቀው ነበርና ወደ ሥራው ሲገባ ብዙም አልተቸገረም፡፡ በወቅቱ የተቀነባበረ የእንስሳት መኖ ፋብሪካ በማቋቋም ምርቱን ለአካባቢው አርሶና አርብቶ አደር ለማቅረብ በነበረው ብርቱ ጥረት ወደ ሥራው መግባት ቢችልም በርካታ ውጣ ውረዶችን አሳልፏል፡፡ በዘርፉ ከፋብሪካ ምርቱን ከማቅረብ ጀምሮ ፋብሪካ ውስጥ ወዛደር ሆኖ ፉሩሽካ ላይ እያደረ ያሳለፋቸው ወቅቶች ጥቂት የሚባሉ አይደሉም፡፡

«እያንዳንዱ ጥረትና ልፋቴ ልምድ ለመቅሰምና ወንድሞቼ የደረሱበት ደረጃ ለመድረስ ነበር» የሚለው ቻላቸው፤ ሥራውን በሙሉ ልቡ ወዶና አክብሮ በብርቱ ትጋት የሚሰራ መሆኑን አጫውቶናል፡፡ ፉሩሽካ ከመሸጥ ጀምሮ አሁን ላይ የተለያዩ የእንስሳት መኖዎችን እያቀነባበረ የሚገኝ ፋብሪካ ከአዲስ አበባ በ65 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በሚገኘው ሰሜን ሸዋ ቡልጋ ከተማ ቱሉፋ ቀበሌ ውስጥ ነው፡፡ እዚህ ቦታ ላይ እየተመረተ ያለውን የእንስሳት መኖ በተለያዩ አካባቢዎች ተደራሽ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡

ፋብሪካው ሁሉንም የእንስሳት መኖ አይነቶች እያመረተ የሚገኝ ሲሆን፤ የወተት ላም፣ የበሬ፣ የጥጃ፣ የበግና የፍየል፣ የጋማ ከብቶች፣ የአሳማ፣ እንዲሁም ከአንድ ቀን ጫጩት ጀምሮ የቄብና የእንቁላል ጣይ ዶሮ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ የተባለውን መኖ ያቀነባብራል። በአጠቃላይ 15 የሚደርሱና ለማንኛውም እንስሳት ጠቃሚ የሆኑ የመኖ አይነቶችን በማምረት ይታወቃል።

እነዚህን የእንስሳት መኖ ለማዘጋጀት ታድያ በዋናነት የሚጠቀመው ጥሬ ዕቃ ከሀገር ውስጥ ሲሆን፤ እነሱም በቆሎ፣ አኩሪ አተር፣ የኑግ ፋጉሎ፣ የስንዴ ገለባ፣ የለውዝ ገለባ የሱፍና የሩዝ ገለባ ወዘተ ይገኙበታል። ከዚህ በተጨማሪ ከውጭ እንደ እንስሳቱ አይነት አስፈላጊ የሆኑ የተለያዩ ቫይታሚኖችና ኬሚካሎችን ይጠቀማል። በቀን ከ1200 እስከ 1500 ኩንታል የማምረት አቅም ያለው ይህ ፋብሪካ እንደ መኖ አይነቱ ከፍና ዝቅ የማለት ሁኔታ አለው፡፡

እልፍ መኖ ምርቶቹን በተለያየ መጠን የሚያዘጋጅና ማንም ሰው በአቅሙ ገዝቶ መጠቀም እንዲችል የሚያድግ በመሆኑ ከሌሎች የእንስሳት መኖ አቀነባባሪዎች ለየት ያደርገዋል፡፡ የሚሉት አቶ ቻላቸው፤ በተለይም ታች ያለው ገበሬ በቀላሉ ገዝቶ መጠቀም እንዲችል ከአምስትና አስር ኪሎ ጀምሮ ያቀርባል፡፡ ይህም አንድና ሁለት ዶሮ ያለው አርሶ አደር ምርቱን በቀላሉ ገዝቶ መጠቀም ያስችለዋል፡፡

የገበያ ተደራሽነቱን በተመለከተም የእንስሳት እርባታ አለ በተባለበት አካባቢ ሁሉ እልፍ መኖ ይገኛል፡፡ ሸገር ከተማን ጨምሮ በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ በሚገኙ የመሸጫ ሱቆቹ ተደራሽ እየሆነ ይገኛል። መሸጫ ሱቆቹ ከሚገኙባቸው አካባቢዎች መካከልም ሆለታ፣ ሱሉልታ፣ ለገጣፎ፣ አሌልቱ፣ ደብረዘይት፣ ቃሊቲ፣ ሻሸመኔና መቀሌ ድረስ የገበያ ትስስር ፈጥሯል። ምርቱ በሚቀርብባቸው በእነዚህ አካባቢዎችም እየተዘዋወሩ ሙያዊ ድጋፍና ክትትል የሚያደርጉ ሙያተኞች ስለመኖራቸው አስረድቷል፡፡

ለተመጣጠነ እንስሳት መኖ በሀገር ውስጥ ከሚገኘው ተረፈ ምርት በተጨማሪ ከውጭ የሚገቡ የተለያዩ ቫይታሚኖችና ኬሚካሎች አስፈላጊ ስለመሆናቸው ያነሳው አቶ ቻላቸው፤ ቫይታሚንና ኬሚካሎቹ የተመጣጠነና የተስተካከለ መኖ ለማግኘት አስቻይ መሆናቸውን ሲያብራራ፤ አንድ እንቁላል ጣይ ዶሮን በአንደኛ ደረጃ ለማምረት በትንሹ 17 የሚደርሱ የግብዓት አይነቶችን መጠቀም የግድ ነው። ለዚህም በዘርፉ የሰለጠኑና የብቃት ሰርተፊኬት ያላቸው ዶክተሮች አስፈላጊ መሆናቸውን በማንሳት ፋብሪካቸውም ይህንኑ መሰረት አድርጎ የሚሰራ መሆኑን ተናግሯል፡፡

መንግሥት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በአሁኑ ወቅት ግብርናው ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ ነገር ግን በዘርፉ የሚስተዋሉ በርካታ ችግሮች መኖራቸውን አመላክቷል፡፡ አርብቶ አደሩ ስለተመጣጠነ የእንስሳት መኖ እያወቀና እየተረዳ በመጣበትና ተጠቃሚ እየሆነ ባለበት በዚህ ወቅት በዘርፉ ያሉት ችግሮች መቀረፍ ካልቻሉ በሚፈለገው ልክ መጓዝ አይቻልም ባይ ነው፡፡ እሱ እንደሚለው፤ ተለምዷዊ በሆነው መንገድ ገለባ የበላች ላም በቀን ቢበዛ አምስት ሌትር ወተት ትሰጣለች፡፡ በተመሳሳይ የተመጣጠነ መኖ የተመገበች ላም ከ10 እስከ 15 ሌትር ወተት ትሰጣለች፡፡ ይህንን ገበሬው መረዳት በመቻሉና ውጤት በማግኘቱ መኖ የመጠቀም ፍላጎት ጨምሯል። ነገር ግን ጥሬ ዕቃው በውድ የሚገዛ በመሆኑ የመኖ ዋጋ እየናረ በመሆኑ መፍትሔ የሚያሻው ጉዳይ ነው ይላል።

በአሁኑ ወቅት መንግሥት ግብርና ላይ በርካታ ሥራዎችን እየሠራ መሆኑን በመግለጽ በተለይም የከተማ ግብርናን ለማስፋት በርካታ ዕድሎችን አቅርቧል የሚለው አቶ ቻላቸው፤ በእንስሳት መኖ ሽያጭ ላይ የነበረውን 15 በመቶ ቫት በማንሳት አርሶና አርብቶ አደሩ የመኖ ዋጋ እንዲቀንስለትና እንዲበረታታ ማድረጉ አንዱ ጥሩ ነገር ነው፡፡ ይሁንና ተረፈ ምርቱን የሚያቀርቡ ፋብሪካዎች ተረፈ ምርን የሚሸጡበት ዋጋ ፍትሐዊ አይደለም፡፡ ከዚህም ባለፈ ከቦታ ቦታ ዋጋው የሚለያይና አበረታች እንዳልሆነ ጠቅሶ የፋይናንስ አቅርቦትም እንዲሁ ሌላው የዘርፉ ማነቆ እንደሆነ ነው ያመላከተው፡፡

በእነዚህና መሰል ምክንያቶች እንቁላል፣ ስጋና ወተት ማህበረሰቡ በቀላሉ ማግኘት የማይችላቸው የቅንጦት ምግብ እየሆኑ ስለመምጣታቸው የሚናገረው አቶ ቻላቸው፤ «በተለይም እንቁላል የሀብታም ልጅ ምግብ እየሆነ ነው» ይላል፡፡ ኢትዮጵያን በመሰለች ለምለም ሀገር አብዛኛው ሕዝብ አርሶና አርብቶ አደር በሆነባት ሀገር፤ በቂ የእንስሳት ሀብት እያለን ዶሮ እያረባን እንቁላል፣ ወተትና ስጋ በቀላሉ ማግኘት አለመቻሉ ቁጭት ሊፈጥርብንና ብዙ ልንሠራ ይገባል ባይ ነው፡፡

አብዛኛው ኢትዮጵያዊ አርሶ አደር ሆኖ ስጋ፣ እንቁላልና ወተት ብርቅ ሊሆንበት አይገባም የሚለው አቶ ቻላቸው፤ ዘርፉ ገና ያልተነካና ያልተሠራበት ዘርፍ እንደሆነም ይናገራል፡፡ እሱ እንደሚለው፤ በዘርፉ ያለውን እጥረት ለማቃለል መንግሥት በከተማ ግብርና እየሠራ ያለው ሥራ የሚበረታታ ነው፡፡ ይሁንና መኖ አቀነባባሪ ፋብሪካዎች የጥሬ ዕቃ አቅርቦትና ዋጋ ላይ እየገጠመ ያለውን ችግር መፈተሽና መፍትሔ መስጠት እንደሚገባ አመላክቷል፡፡

ፋብሪካው 110 ለሚደርሱ ዜጎች የሥራ ዕድል የፈጠረ ሲሆን፤ ማህበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት ረገድም አበርክቶው የጎላ ነው፡፡ ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች መካከል ለምርቱ ተጠቃሚዎች ነጻ የትራንስፖርት አገልግሎትን ጨምሮ የአርሶ አደሩ ሀብት ንብረት ለሆኑት እንስሳት ነጻ ህክምና ይሰጣል። የተቀነባባረ መኖን በመጠቀም ውጤታማ መሆን የሚስችላቸውን የምክር አገልግሎት ለአርሶ አደሩ ይሰጣል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አቅም ለሌላቸው አርሶ አደሮች የዶሮ መኖ በብድር ያቀርባል። አርሶ አደሩም እንቁላል ጣይ ጫጩቶችን በማርባት እንቁላል መስጠት እስኪችል መኖ በብድር ይወስዳል፡፡ ዶሮዎቹ እንቁላል መስጠት ሲጀምሩ እንቁላሉን በመሸጥ ብድሩን መክፈል የሚችልበትን የብድር ሥርዓት ዘርግቶ ከአርሶ አደሩ ጋር በቅንጅት ይሰራል፡፡

መንግሥት ለግብርናው ዘርፍ የሰጠውን ትኩረት በመጠቀም በቀጣይ ግብርናውን የማዘመን ዕቅድ ያለው አቶ ቻላቸው፤ ለገበሬው ቅርብ በመሆን ከእርባታ ጀምሮ እስከ መኖ አቅርቦት የመሥራት ዕቅድና ፍላጎት አለው፡፡ ለአብነትም በዶሮ እርባታ ጫጩት ማቅረብና ጊደሮችንና በሬዎችን ጭምር በማርባት ማደለብ ለሚፈልጉ ዜጎች ከመኖው ጋር ለማቅረብና ሰፊ የሥራ ዕድል የመፍጠር ዕቅድ ይዞ እየሠራ ይገኛል።

በመጨረሻም መኖ ከሌለ እንስሳቱንም ሆነ የእንስሳት ተዋጽኦ ውጤቶችን ማግኘት የማይታሰብ በመሆኑ ከኢንዱስትሪ የሚወጡ ተረፈ ምርቶች በምን ዓይነት ሁኔታ ለገበያ መቅረብ እንዳለባቸው፣ የእንስሳት ዕርባታ ድርጅቶች ለመኖ ማዘጋጃ ፍጆታ የሚጠቀሙባቸውን የሰብል እህሎች ሊያገኙ የሚችሉበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር ከሚመለከተው አካል የሚጠበቅ የቤት ሥራ መሆኑን እያስታወስን አበቃን።

# መሠረተ ልማት

## የከተሞችን አቅም ለማሳደግ የሚተገበረው መርሀ ግብር

**በኃይሉ አበራ**



የከተማ ነዋሪውን ማህበረሰብ ያሳተፉ የከተማ መሰረተ ልማት ሥራዎች በሀገሪቱ በበርካታ ከተሞች ተግባራዊ እየተደረጉ ይገኛሉ። የመንገድ፣ የፍሳሽ ማስወገጃዎች፣ የአረንጓዴ ስፍራዎች ልማት፣ ከተሞችን ለኢንቨስትመንት እና ለነዋሪው ምቹ የማድረግ ሥራዎችም በፕሮግራሙ እየተሰሩ ይገኛሉ። 30 በመቶ ማህበረሰቡ የተሳተፈበት እና 70 በመቶ በዓለም ባንክ ድጋፍ እየተከናወነ የሚገኘው የከተሞች መሰረተ ልማት ፕሮግራም ዋና ትኩረቱ የከተሞችን አቅም ማሳደግ ነው። ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ በ117 ከተሞች መተግበር የጀመረው ፕሮግራም ከትግራይ ክልል ውጪ በሌሎች ክልሎች ከተሞች በማጠናቀቂያ ምዕራፍ ላይ ይገኛል። በዋናነትም የከተሞችን አቅም የማሳደግ እና የራሳቸውን የማዘጋጃ ቤታዊ ገቢ እንዲጨምሩ እንዲሁም ለዜጎች የሥራ እድል እንዲፈጠር ያለመው ፕሮግራም በከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር በኩል ተፈፃሚ እየሆነ ይገኛል።

በከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር የቤቶችና ከተማ ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ሄለን ደበበ፣ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተለያዩ ፕሮግራሞች ተቀርጾ መንግሥትን ውጤታማ ከማድረግ ጎን ለጎን በከተሞች አቅም ግንባታ ላይ ያተኮረ የመሰረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም እየተሰራ መሆኑን ይገልፃሉ። ከእነዚህ መካከል አሁን እየተከናወነ የሚገኘው፣ ከ2011 ዓ.ም እስከ 2015 ዓ.ም ለማጠናቀቅ ታስቦ የተጀመረው ፕሮግራም ነው። «ይሁንና በኮቪድ፣ በሰሜኑ ጦርነት እንዲሁም በሌሎች የተለያዩ የውስጥ ጉዳዮች ምክንያት በሚፈለገው መልኩ ለማስኬድ አልተቻለም። በዚህም የተነሳ አንድ ዓመት ተራዝሞ እስከ በተያዘው በጀት ዓመት እየተተገበረ ይገኛል» በማለት የከተሞች አቅም ግንባታ እና የመሰረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራሙ በኢትዮጵያ በሁሉም ክልሎች በሚገኙ 117 ከተሞች ላይ ተጨባጭ ውጤቶች የሚጠበቅበት መሆኑን ጠቁመዋል።

የፕሮግራሙ ዋና ዓላማም ከተሞች መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች በዘላቂነት እየተደገፉ የከተሞችን የኑሮ ችግሮች እንዲፈቱ እና በዘላቂነትም አቅማቸው አድጎ በራሳቸው ገቢ የከተማውን ፍላጎት ወይንም አጠቃላይ ካፒታላቸውን ሊሸፍን የሚችል ገቢ መሰብሰብ እንዲችሉ ትኩረት በማድረግ የሚሰራበት ነው። የከተማ ነዋሪው ማህበረሰብ ከእቅድ እስከ ተግባር ድረስ በሚገኙ ሂደቶች ተሳትፎ እንዲያደርግ በእቅድ፣ በማሳተፍ፣ በሳይት መረጣ፣ በመዋጮ፣ ጥራትን በማስጠበቅ ማሳተፍ አንዱ የስራው ሂደት አካል መሆኑን ያስታወሱት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ በየዘርፉ የማህበረሰብ ተሳትፎ እያደገ የመጣ መሆኑን ይገልጻሉ።

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም ተያያዥ የአሰራር ሥርዓት እና የህብረተሰበ ተሳትፎ በምን መልኩ ይመራል የሚል መመሪያ አዘጋጅቶ በከተሞቹ ተደራሽ አድርጎ 30 በመቶ እና ከዚያ በላይ በማዋጣት በየአካባቢው በሚሰሩ የመሰረተ ልማት ስራዎች ተሳትፎ እያደረጉ ይገኛሉ። መፀዳጃ ቤቶች፣ የመታጠቢያ ቦታዎች፣ የቆሻሻ መጣያ ቦታዎች ዝግጅትም የፕሮግራሙ አካል ሆነው በስፋት የሚሰሩ ናቸው። በሌላ በኩል የከተሞችን የማዘጋጃ ቤት ገቢ የመሰብሰብ አቅም ማሳደግ አንዱ የፕሮግራሙ አካል ነው። በ117 ከተሞች ፕሮግራሙ አሁን ያለበት ግምገማ ሲደረግ ተስፋ ሰጪ ውጤቶች አሉት ይላሉ።

አንዱ የፕሮግራሙ አቅም ግንባታ ሥራ ሲሰራ የከተሞች የገቢ ምንጭ የትኛው ነው? የበለጠ ገቢ ሊገኝ የሚችለው የትኛውን አገልግሎት ማስፋት ሲቻል ነው? በሚሉት ጉዳዮች ላይ ጥናት ይደረጋል። ጥናቶቹ በሚያመላክቱባቸው ዘርፎችም የተለያዩ የገቢ ማሻሻያ ርዕሶች በየምክር ቤቱ እየፀደቁ ተግባራዊ እየሆኑ መጥተዋል። በዚህ ሂደት በፕሮግራሙ ተጠቃሚ የሆኑ ከተሞች በቢሊዮን ብር የሚቆጠር ገቢ የመሰበሰብ አቅም ላይ መድረሳቸውን ይገልፃሉ።

ሌላኛው የፕሮግራሙ አካል የተሻሻለ መሰረተ ልማት ለከተማ ማቅረብ እና ሲስተም መዘርጋት መሆኑንም ይናገራሉ። ከዚህ አንፃርም ፕሮግራሙ ሲጀመር በከተሞቹ የነበረው በዋናነት የከተማ መሰረተ ልማት ላይ ትኩረት አድርጎ ሲሰራ የሥራ እድል በስፋት እንዲፈጠር ይፈለጋል። ይህም በከተሞቻችን የሥራ አጥነት ችግር በስፋት ያለ በመሆኑ ነው። ከአካባቢው ጋር ተስማሚ የሆኑ ኢንቨስትመንቶችም በፕሮግራሙ የተካተቱ ናቸው።

በፕሮግራሙ ባለፉት አምስት ዓመታት አንድ ሺህ 353 ኪሎ ሜትር የኮብልስቶን መንገዶች ተሰርተዋል። በየዓመቱም ጥገና ለሚያስፈልጋቸው ጥገና የሚደረግበት አሰራር ተዘርግቷል። የግራቬል (መንገድ የሚከፈትባቸውና በቀጣይ ለኮብልስቶን ወይም ለአስፋልት የሚያድጉ) 914 ኪሎ ሜትር መንገዶች ተሰርተዋል።

በፕሮግራሙ የግራቬል መንገዶችን በመስራት እና ለአስፓልት ግንባታዎች ዝግጁ በማድረግ ቀጣይ የአስፓልት ንጣፍ ሥራ እና ሌሎች ዋና ዋና የመንገድ ይዘቶችን፣ በግራና በቀኝ ዳር ያሉ የውሃ ማፋሰሻዎችን፣ የእግረኛ መንገዶችን እና የመንገድ አካፋዮች ሁሉ ከተሰሩ በኋላ የአስፓልት ንጣፉን በከተማው ወጪ የሚሰራባቸው ሁኔታዎች አሉ።

ከዚህ አንፃርም ውጤታማ ሥራ የሰሩ ከተሞች መካከል ጅግጅጋ፣ ሀዋሳ፣ ቢሾፍቱ፣ ጎንደር ከተሞችን ጨምሮ በርካታ ከተሞች ተስፋ ሰጪ ስራዎች መሰራታቸው በዓለም ባንክ፣ በከተማና መሰረት ልማት ሚኒስቴር፣ እንዲሁ በፓርላማም በተለያዩ አካላት ምልከታ ተደርጎበት ጥሩ አፈፃፀም ተመዝግቧል።

በፕሮግራሙ ትኩረት ተደርጎ የሚሰራው ሌላው የውሃ ማፋሰሻዎች ሥራ መሆኑን ሲያስረዱ፤ አብዛኞቹ የሀገራችን ከተሞች ከውሃ ማፋሰሻ አንፃር ጉድለት የሚታይባቸው ናቸው። በዚህም 974 ኪሎ ሜትር የመንገድ ፍሳሽ ማስወገጃዎች ተሠርተዋል።

በፕሮግራሙ ከተሞችን ለኢንቨስትመንት እና ለነዋሪው ምቹ ከማድረግ አኳያም ሰፊ ሥራዎች መሠራታቸውንም ይናገራሉ። ከዚህ ሥራ አንፃርም በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአብዛኛው ከተሞች ላይ ትልቅ ለውጥ እያመጡ ያሉባቸው ሁኔታዎች አሉ። በፕሮግራሙ 205 ሄክታር የአረንጓዴ ስፍራዎች እና ፓርኮች የወንዝ ዳር ፕሮጀክቶች በባቱ፣ በጅማ፣ ሻሸመኔ፣ ሀዋሳ ከተሞችን ጨምሮ በአብዛኛዎቹ ከተሞች ተከናውነዋል። እነዚህ ስራዎች ሲሰሩም የመንገድ ላይ መብራት ዝርጋታ፣ የገበያ ማዕከላት ግንባታ እና ሌሎች በርካታ ተያያዥ ስራዎች ከመንግሥት ጋር በጋራ ፋይናንስ ተደርገው የሚሰሩ ናቸው።

ከዓለም ባንክ በሚገኘው በጀት በተጨማሪ ከተሞች እና ክልሎች ለፕሮግራሙ የየድርሻቸውን መዋጮ ያደርጋሉ። ከዚህ አኳያም ባለፉት አምስት ዓመታት 859 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ዶላር በፕሮግራሙ ተግባራዊ መሆኑን አስታውቀዋል።

ከዚህም ውስጥ 691 ሚሊዮን ዶላሩ ከዓለም ባንክ የተገኘ ሲሆን፤ ከከተሞች እና ከክልሎች መዋጮ ደግሞ 248 ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ዶላር መዋጮ በማድረግ ሰፋፊ የመሰረተ ልማት ሥራዎችን በከተሞች ለመስራት የተቻለ መሆኑን ይገልጻሉ። ስድስት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ያህል የህብረተሰብ ክፍሎች በፕሮግራሙ ተጠቃሚ መሆን ችለዋል።

አጠቃላይ ፕሮግራሙ ካሳካቸው ግቦች መካከል በገንዘብ ሚኒስቴር የፖርቲፎሊዮ ግምገማ መሰረትም ሀገር ውስጥ ካሉ በርካታ ፕሮጀክቶች አኳያ ውጤታማ ፕሮጀክት መሆኑ የታየበት ነው። በአሁኑ ወቅትም ፕሮግራሙን በማጠቃለል ሁለተኛውን ዙር የከተሞች የአቅም ግንባታ እና የመሰረተ ልማት ፕሮግራም ለማስቀጠልም የቅድመ ዝግጅት እና የፕሮግራም ዲዛይን ሥራዎች እየተሰሩ መሆናቸውንም አመላክተዋል።

በፕሮግራሙ አማካኝነት ከተሞችን ገቢ ከማሳደግ አንጻር አንዱ የፕሮግራሙ አካል ረጂና አጋር አካላቱ ለሁልጊዜ ድጋፍ እያደረጉ የሚቆዩ ሳይሆኑ የከተሞቹን አቅም የማሳደግ እና ራሳቸውን ችለው ገቢ የሚያገኙበትን ሁኔታ መፍጠር ላይ ያተኮረ ነው።

በእነዚህ የመሰረተ ልማት ድጋፎች ረጂ አካላት ጨርሰው ሲወጡ ከተሞቹ ወደኋላ እንዳይመለሱ ተጨባጭ የመሰረተ ልማት ስራዎቹ ከተሞቹ ላይ ሲሰሩ ከተወሰነ ጊዜ ድጋፍ በኋላ የከተማው ኢንቨስትመንት የመሳብ አቅም ያድጋል። በከተሞች መሰረተ ልማት ሲዘረጋ አካባቢው መኖሪያ ከሆነም መንገድ ሲወጣለት መብራት ሲዘረጋለት የውሃ አቅርቦት ሲሟላለት አካባቢው እድገት ያሳያል። በዚህ መካከልም የመሬት አጠቃቀሙ እየተቀየረ ይመጣል። ከተማውም መሬቱን በጨረታ፣ በምደባ እና በተለያየ መንገድ ሲሰጥ የመሬት ዋጋ ያድጋል። በአካባቢውም ከዚህ ቀደም መኖሪያ ከሆነ ወደ ንግድ ሲያድግ ብዙ ነጋዴዎች ይፈጠራሉ። ለሥራ አጥ ዜጎችም የሥራ እድሎች እንዲሁም ተጨማሪ ወደ ታክስ ሥርዓት የሚገቡ ሰዎች እና ቦታዎችም ይፈጠራሉ። በዚህ ሂደትም የከተሞች ገቢ እየጨመረ ይሄዳል።

በቋሚነትም መሬት ላይ የሚመጡ ማሻሻያዎች ከመሬት የሚሰበሰበውን ግብር በማሻሻል የሚያመጧቸው ለውጦች አሉ። ለከተሞች መሰረተ ልማት በተዘረጋ ቁጥር ለኢንቨስትመንት ሳቢ እየሆኑ ይመጣሉ። አዳዲስ የሚፈጠሩ የኢንቨስትመንት እድሎችን ተከትሎም ሰፊ የሥራ እድል ይኖራል። በአረንጓዴ ስፍራዎችና ፓርኮች ላይ የሚሰሩት ፕሮግራሞቹ ፕሮጀክቶቹ ከተጠናቀቁ በኋላ ማዘጋጃ ቤቶች ቦታውን እያስተዳደሩና የራሳቸውን ገቢ እንዲፈጥሩ ለማስቻል እንዲሁም የሥራ ዕድል ለሚፈጠርላቸው ወጣቶች የማስረከብ ሥራ ይሰራል።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታዋ ገለፃ፣ ፕሮግራሙ ሁለት ዋና ዋና ምሰሶዎች አሉት። አሠራር ማዘመን እና የአቅም ክፍተትን መሙላት ነው። ከዚህ አንፃር የከተሞች የመረጃ አያያዝ፣ ፋይል የማደራጀት አቅም ላይ የነበረውን ክፍተት አቅም በመገንባቱና የምዝገባ ስራዎች በመጀመሩ እንዲሁም ወደ ዲጂታላይዜሽን ሥራ እየተቀየሩ በመምጣታቸው ምክንያት ወደ ታክስ ሥርዓት ያልገቡ ግለሰቦች እና ቦታዎች ወደ ታክስ ሥርዓት እንዲገቡም እድል እየተፈጠረ መሆኑን ነው ያስረዱት። ጥናቶች እየተደረጉ የማይሰበሰቡ ወይንም ገበያ አይገኝባቸውም ተብለው ችላ የተባሉ ጉዳዮች ላይም ትኩረት በማድረግ የመጡ ለውጦች ስለመኖራቸው ያምናሉ። ባለፉት አምስት የፕሮጀክት ዓመታትም በ117 ከተሞች ለ749 ሺህ 854 ዜጎች በቋሚና በጊዜያዊ የሥራ ዕድል ተፈጥሯል፡፡

በፕሮጀክቱ የመጨረሻ ዓመት ለማሳካት ከታቀደው አንፃር እስካሁን ከ90 በመቶ በላይ ውጤት ማግኘት ተችሏል። ማሳካት ያልተቻለው ማነቆም ተገምግሟል። በበርካታ ከተሞች ላይ ፕሮግራሙ ተደራሽ መሆን ቢችልም እንደሀገር ከነበረው የሕግ ማስከበር ጉዳይ ጋር ተያይዞ በትግራይ ክልል ፕሮጀክቱ በ2013 እና 2014 ዓ.ም መካከል ተግባራዊ መሆን አለመቻሉ ክፍተት የፈጠረ መሆኑን ገልጸዋል።

ከሰላም ስምምነቱ በኋላም ከ2015 ዓ.ም ጀምሮ አጠቃላይ ግምገማ ተደርጎ ከተሞቹ ወደ ተግባር የሚገቡባቸው ምቹ ሁኔታዎች መኖራቸው ተረጋግጧል። በመሆኑም በ2016 ዓ.ም ለትግራይ ክልል ገንዘቡ ተላልፎ አካላዊ ሥራዎቹ እና የአቅም ግንባታ ሥራዎች መሬት ላይ እየተሰሩ መሆናቸውን ነው ያስረዱት።

ሌላው ተግዳሮት የመሰረተ ልማት ዝርጋታ መሆኑን ያነሱት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ በተለይም ባለፉት ዓመታት በሀገር ደረጃ የግንባታ ቁሳቁሶች ዋጋ መጨመር ምክንያት በታቀደው መሰረት ማሳካት ያልተቻሉ ሥራዎች አሉ። እንዲሁም ከጥራት አንፃር እየተሻሻሉ የመጡ የመሰረተ ልማት ስራዎችና ማቴሪያሎች ቢኖሩም አሁንም ትኩረት የሚያስፈልጋቸው መሆኑን ተናግረዋል።

እሳቸው እንዳሉት በዓለም ባንክ የከተሞች ተቋማዊና የመሰረተ ልማት መርሀ ግብር (Urban Institutional and Infrastructure Development Program - UI-IDP) በኩል ገቢ መደረግ የሚገባው ገንዘብ ወደ ኢትዮጵያ መንግሥት አካውንት ሙሉ በሙሉ ገቢ ተደርጓል።

በትግራይ ክልል ከሰላም ስምምነቱ በኋላ ከግንቦት ወር ጀምሮ ባለፉት ስድስት ወራት ሰፊ ሥራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል። በፕሮግራሙ ስለሚሰሩ ስራዎች ከሁሉም የክልሉ ከተሞች ለተውጣጡ አካላት በዓድዋ ከተማ ሥልጠናዎች ተሰጥቷል።

በመቀጠልም በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እና በገንዘብ ሚኒስቴር መካከል የተቋቋመ ቡድን በክልሉ በሚገኙ ከተሞች አስቻይ ሁኔታዎች መኖራቸውን ምልከታ አድርጓል። በየደረጃውም ስራውን የሚያረጋግጡ ኮሚቴዎች መኖራቸው ተረጋግጧል። ከዚህ ቀደም የተከፈቱ አካውንቶችም አዲት ተደርገው መዘጋታቸው እና ሌላ አዲስ አካውንት መከፈቱን እና መዋቅሮቹ ሥራ ላይ የሚውሉ መሆናቸው ፍተሻ ተደርጓል።

በተጠናቀረው መረጃ ባለፉት ስድስት ወራት በፕሮግራሙ ተጠቃሚ ከሆኑ ከተሞች መካከል 272 ሚሊዮን ብር ወደ ትግራይ ክልል ተላልፏል። በዚህም የተለያዩ የመሰረተ ልማተ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ። ከመስሪያ ቤቱም የተውጣጣ ቡድን በሳይት ላይ ይገኛል። የዚህ አፈጻጸም ከተገመገመ በኋላም የሁለተኛው ዙር ቀጣይ ቀሪ ገንዘብ የሚላክ መሆኑንም ይጠቁማሉ።

አሁን ላይ ከትግራይ ክልል ውጪ ያሉ የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ከተሞች ገንዘቡ እየተላለፈ ሳይሆን የነበረውን ፕሮግራም የማጠቃለል ሥራ እየተሰራ መሆኑን ይገልፃሉ። እስካሁን የተንጠባጠቡ ስራዎች በተለይ ሰፋፊ ፓርኮች፣ ደረጃውን የጠበቀ ትላልቅ ቄራዎች ባሉባቸው ከተሞች ከመጪው ሰኔ ወር በፊት እንዲጠናቀቁ ድጋፍ የሚደረግ መሆኑንም አመላክተዋል።

# ወስኖ ራስን መለወጥ!

አስናቀ ፀጋዬ

እናቱ ማርገዟን ስታውቀው ለማስወረድ ተጣድፋ ወደ ሀኪም ቤት ሄደች፡፡ ሀኪሞች አይሆንም አሉ። ካለችበት የኑሮ ሁኔታ አንፃር ሌላ ልጅ መውለድ ለእርሷ የማይታሰብ ነው፡፡ ሀኪሞች እምቢ ቢሏትም እርሷ ግን ተደብቃ የአልኮል መጠጥ እየጠጣች ፅንሱን ልታጨናግፈው ሞከረች፡፡ ይሁንና ይህን ሁሉ ውጣውረድ አልፎ ልጁ ተወለደ፡፡ የሕፃኑ ቤተሰቦች ለፍቶ አዳሪ ናቸው፡፡

ልጁ አድጎ ጫማ የሚገዛለት ሰው እንኳን አልነበረም፡፡ ዘመዶቹ የጣሉትን አሮጌ ጫማዎች አድርጎ እግርኳስ ይጫወት ነበር፡፡ ጓደኞቹ በአባቱ የፅዳት ሥራ እያሾፉ ልቡን ይሰብሩት ነበር፡፡ አስተማሪው እንኳን ተማሪዎች በተሰበሰቡበት በአባቱ ድህነት ቀልዶበት ያውቃል፡፡ አባቱ ሰካራም ወንድሙ ሱሰኛ ነበሩ፡፡ እርሱም ትምህርት ይከብደው ነበር፡፡

ልጁ ግን እግር ኳስ ላይ በረታ፡፡ ምን ያደርጋል! የልብ ህመም ያዘው፡፡ መሮጥ፣ መራመድ ቁጭ ማለት እንኳን አቃተው፡፡ ትንፋሽ አጣ፡፡ ዶክተሩ እግር ኳስ መጫወቱን ያቁም፤ ወይም የልብ ቀዶ ህክምና ይደረግለት አለ፡፡ ቀዶ ህክምናው ካልተሳካ ሊሞት እንደሚችል በዶክተሩ ተነገረው፡፡ ያኔ ደግሞ እድሜው አስራ አምስት ዓመት ነበር፡፡ ለታላቅ ህልሙ ሲል ቆራጥ መሆን ነበረበት፡፡ ምንም ሳያመነታ የልብ ቀዶ ህክምናውን አደረገ፡፡

አስገራሚው ነገር ከቀዶ ህክምናው በኋላ እንደውም ፍጥነቱ ጨመረ፡፡ ታላቅ የመሆን ምኞቱ፣ ጥረቱ፣ ፅናቱ ተጨምሮ ዓለም የሚያከብረው የእግር ኳስ ተጫዋች ሆነ፡፡ የጎል ማሽን ይሉታል፡፡ ሚሊየኖች የእርሱን ማልያ በፍቅር ይለብሳሉ፡፡ በዓለም ላይ እጅግ አውቅናን ካተረፉ ጥቂት ሰዎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ታውቁታላችሁ! የምድራችን ታላቁ የእግር ኳስ ኮከብ ክርስቲያኖ ሮናልዶ ነው፡፡

አሁን ላይ ክርስቲያኖ ሮናልዶ የመጀመሪያው ቢሊየነር የእግር ኳስ ተጫዋች ነው፡፡ ተጫዋቹ ቆራጥ ሆኖ ያን ቀዶ ህክምና ባያደርግ ኖሮ ዛሬ ስለእርሱ አይወራም ነበር፡፡ ቆራጥ መሆን እንደሚያስከብር ከዚህ ሰው በላይ ምስክር የለም፡፡ አንተም የተሻለ ሰው ለመሆን መወሰን አለብህ፡፡ አንድ ውሳኔ ህይወትህን እስከመጨረሻው ሊለውጠው ይችላል፡፡ የምትፈልጋቸው ነገሮች በሙሉ ከፍርሃትህ ጀርባ ቁጭ ብለዋል፡፡ ቆራጥ ካልሆንክ ማንም አይፍልግህም፡፡ ለራስህ አትሆን፤ ወይ ለቤተሰብህ አትሆን አልያ ደግሞ ለምትወዳቸው አትሆንም፡፡ የሚያመነታ ሰው ሲባክን ይኖራል፡፡ ስለዚህ ቆራጥ መሆን አለብህ ወዳጄ!

የሀርቫርድ ዩኒቨርሲቲው ምሁር ዶክተር ፍሬድ ለስኪን አዕምሯችን በቀን ውስጥ ከ60 ሺ በላይ ሃሳቦችን ያስባል ይለናል፡፡ አብዛኛው ደግሞ ተደጋጋሚ ነው፡፡ ግማሹ ስለትናንት ነው፡፡ ቁጭት ነው፡፡ ብሶት ነው፡፡ ‹‹ወይኔ! እንዲህ ባላደርግ ኖሮ፣ አበላሸሁት፣ አጠፋው›› እያልን ነው የምናስበው፡፡ ግማሹ ደግሞ ስለነገ ነው፡፡ ‹‹እንዲህ ቢሆን ፣ እንዲህ ባገኝ የሚል›› ምኞት ነው፡፡ ለውጥ የሚጀምረው ደግሞ አሁን ላይ ትኩረት አድርገህ በመወሰን ነው፡፡

ከዚህ በፊት የወሰንካቸው ውሳኔዎች ያሳጡሁ ደስታ አለ፡፡ የአእምሮ ሰላም አለ፡፡ እንደውም ሰዎች መጥተው ‹‹አንተ ጀግና ነህ፡፡ እንዲህ በማድረግህ አደንቅሃለው›› ያሉህ ጊዜ አለ፡፡ ‹‹እህቴ አንቺ በጣም ጎበዝ ነሽ፣ እንዲህ በማድረግሽ ገርሞኛል›› ብለው ያደነቁሽ ወቅት አለ፡፡ ያ ወቅት በጣም ቆራጥ ሆነሽ የወሰንሽበት ነው፡፡ በዚሁ ቅፅበት ሱሱን ለማቆም መወሰን አለብሽ፡፡ ፈርተህ ያቋረጥከውን ትምህርት ለመቀጠል መወሰን አለብህ፡፡ እጀምራለሁ ብለህ እያመነታህ ያለኸውን ያን ሥራ ለመጀመር አሁን መወሰን አለብህ፡፡

በትምህርቴ፣ በስራዬ፣ በፍቅር ግንኙነቴ፣ በትዳሬ ወዘተ ለውጥ እፈልጋለሁ ብለህ ካሰብክ መጀመሪያ መወሰን አለብህ፡፡ ከዛ ወደ ተግባር መግባት አለብህ። ግን ‹‹እንዴት አድርጌ ልወስን፤ ሶፋ ላይ ቁጭ ብሎ ቁረጥ! ወስን ማለት ማን ያቅተዋል›› ካላችሁ ልክ ናችሁ፡፡ ለዚህ መንገድ ያስፈልጋል፡፡ መንገዱ ደግሞ እንሆ......

## መወሰን ለምን ይጠቅማል?



አንድን ነገር ለምን እንደምታደርገው ካወክ ጀምረህ አታቆመውም፡፡ አንዳንድ ሰው ይነቃቃል፡፡ የሚገርም ኃይልና ደስታ ይሰማውና ስፖርት መስራት ይጀምራል፡፡ አንድ ሰሞን ሰርቶ ሰልችቶት ያቆማል፡፡ በጠዋት መነሳት ይጀምራል፡፡ ከዛ ይሰለቸውና ‹‹እንዴ! ለነብሴ ነው ወይስ ለስጋዬ በጠዋት እየተነሳው ስፖርት የምሰራው›› ብሎ መነሳቱን ያቆማል፡፡ አየህ! የአንድን ነገር አላማ ስታውቅ ጀምረህ አታቆምም። ከወሰንክ ወሰንክ ነው፡፡ ስለዚህ ለምንድን ነው የምትወስነው? ባትወስን ምን ታጣለህ? ምን ትጎዳለህ? ህመሙን እወቀው፡፡ ካልወሰንክ ባለህበት ቆመህ ልትቀር ነው። ያ የምትፈልገው ህልም በቁምህ እያየኸው አፈር ሊበላው ነው፡፡ ስለዚህ መወሰን አለብህ፡፡

እንዳታፈገፍግ የምታጣውን ነገር ቀድመህ አስበው፡፡ ከዛ ደግሞ ብትወስን ምን ታገኛለህ? ደስታው ምንድን ነው? ብትወስን ራስህን በአስተሳሰብና በስብእና መገንባት ትጀምራለህ። ከዚህ በፊትም ቢሆን ብዙ ነገሮችን መቀየር የቻልከው በወሰንክባቸው ወቅቶች ነው፡፡ ህይወትህ በራስህ ቁጥጥር ውስጥ ይገባል፡፡ የህይወትህ ካፒቴን አንተ ራስህ ትሆናለህ፡፡ እስከምትችለው ማደግ ትጀምራለህ፡፡

በነገራችን ላይ አሁን አንተ ያለህበት ደረጃ ላይ ያደረሰህ ከዛሬ አምስትና አስር ዓመት በፊት አብረሃቸው ትውላቸው የነበሩ ሰዎች፣ ጓደኞችህ፣ ታነበው የነበረው መጽሐፍ፣ ታየው የነበረው ፊልም.... ወዘተ ብቻ ውሎህ ዛሬ ላይ አድርሶሃል፡፡ ነገ የምትርስበትንም የሚወስነው ዛሬ የምትወስናቸው ውሳኔዎች ናቸው፡፡ አየህ! ለመለወጥ ስትወስን ለምንድን ነው የምለወጠው? ምንድን ነው የሚጠቅመኝ ? ባልለወጥ ምን አጣለሁ? ባልወስን ምን እጎዳለሁ ማለት አለብህ፡፡

### መጠበቅ አቁም!

ብዙ ሰው የሆነ ሁኔታ እስኪፈጠር ድረስ ጥበቃ ላይ ነው፡፡ በህይወቱ የሆኑ ነገሮችና ክስተቶች እስኪመጡ፣ የሆነ ሰው መጥቶ እስኪረዳው እየጠበቀ ነው፡፡ እንዳትወስን ያደረገህ፣ እንዳትጠነክር ያደረገህ፣ ልፍስፍስ ያደረገህ ከሰው መጠበቅ ነው። ሁኔታዎች እስኪቀየሩ መጠበቅ ነው እንዳትወስን ያደረገህ፡፡

ማን እንዲመጣ ነው የምጠብቀው? ማንም አይመጣም፡፡ ማንንም አጠብቅ፡፡ የሆነ ሥራ ለመሥራት ሙድ ውስጥ ልግባ አትበል፡፡ ስራው ራሱ ያነቃቃህ፡፡ መርፌ የሚፈውስህ እያሳመመህ ነው፡፡ እድሎች እንኳን የሚመጡት በራስህ የምትችለውን ያህል ስትጀምር ነው፡፡ ቆመህ ስትጠብቅ ያልመጡ እድሎች መንቀሳቀስ ስትጀምር ግን በላይ በላይ ይደራረባሉ፡፡ ፍቅረኛ ሳይኖርህ ዞር ብለው ያላዩህ ሰዎች ፍቅረኛ ስትይዝ አላስቆም አላስቀምጥ ይሉሃል። ቆመህ ስትጠብቅ ያልመጣው ታክሲ እንኳን በእግር መንገድ ስትጀምር ‹‹የሞላ አንድ ሰው!›› ይልሃል፡፡

ይህች ዓለም የምታደላው ቁጭ ለሚል ሳይሆን ለሚሮጥ ነው፡፡ ከሰው ለሚጠብቅ አይደለም ለራሴ አላንስም ብሎ ለሚታገል ነው፡፡ ከሰው መጠበቅ ልብህን ይሰብረዋል፡፡ እድል እስኪመጣ ቁጭ ማለት ብኩን ያደርግሃል፡፡ መሮጥ አለብህ፡፡ መታገል አለብህ፡፡ እድል የሚመጣው ቁጭ ለሚል ሳይሆን ለሚዘጋጅ ነው፡፡ ካልተዘጋጀህ እድሉ ቢመጣ ራሱ ታባክነዋለህ፡፡ ተዘጋጅ! መጠበቁን አቁምና ጊዜህ እንዳይባክን አሁኑኑ ወስን፡፡

> ‹‹የተሻለ ሰው ለመሆን መወሰን አለብህ፡፡ አንድ ውሳኔ ህይወትህን እስከመጨረሻው ሊለውጠው ይችላል፡፡ የምትፈልጋቸው ነገሮች በሙሉ ከፍርሃትህ ጀርባ ቁጭ ብለዋል። ቆራጥ ካልሆንክ ማንም አይፍልግህም። ለራስህ አትሆን፤ ወይ ለቤተሰብህ አትሆን አልያ ደግሞ ለምትወዳቸው አትሆንም። የሚያመነታ ሰው ሲባክን ይኖራል፡፡ ስለዚህ ቆራጥ መሆን አለብህ ወዳጄ!››

### ወደኋላ መመለስ የለም!

ወደኋላ የሚመልሱህን ነገሮች አስወግድ፡፡ እንዳትለወጥ፣ ቆመህ እንድትቀር፣ እንድትፈዝ ... ሰዎች እየተለወጡ ነው፡፡ አንተ ግን ቆመሃል፡፡ እንደዛ እንድትሆን ያደረገህ ምንድን ነው? እስቲ ቁጭ በልና አስበው፡፡ ውሎህ ነው፣ ጓደኞችህ ናቸው፣ በዙሪያህ ያለ ሰው ነው፣ ማን ነው? አንዳንድ ጊዜ የተመረዘ እጅ የሚቆረጠው ባለቤቱ ስለማይፈልገው አይደለም፡፡ ሌሎቹን የሰውነት ክፍሎች ስለሚመርዛቸው ነው፡፡

ውሎህን የምትቀይረው፤ አትችልም፣ አትርረባም፣ የትም አትደርስም ከሚሉ ሰዎች የምትሸሸው ስለማትወዳቸው አይደለም፡፡ ግን ቆራጥ እንዳትሆን፣ የውሳኔ ሰው እንዳትሆን እያደረጉህ ስለሆነ ነው፡፡ ህልምህን ቆፍረው እየቀበሩት ስለሆነ ነው፡፡ ውሎህን ለመቀየር ምንድን ነው የያዘህ? ምንስ ነው የጎተተህ? አስቲ ይህን አስብ፡፡ ቆራጥ ስትሆን ሰዎች እንኳን ያከብሩሃል፡፡ እሱ እኮ ከወሰነ ወሰነ ነው ይሉሃል፡፡

አንዳንድ ሰው ያቆመውን ሱስና መጥፎ ልማድ የሚጀምረው ከነዛ ሰዎች ጋር ሲገናኝ ነው፡፡ ወይ የሆነ የለመደው ቦታ መልሶ ሲውል ነው፡፡ ስለዚህ እንደዚህ አይነት ነገሮችን ከህይወትህ አስወግድ፡፡ የማይጠቅሙህን ሰዎች ከህይወትህ ቆርጠህ አውጣ፡፡ ለውጥ መጀመር ቀላል ነው፡፡ እስከ ፍፃሜው መጓዝና መጨረስ ነው ከባዱ፡፡ ከፍፃሜው ላይ ለመድረስ ግን ወደኋላ ማየት የለብህም፡፡ ወደኋላ እንድታይ የሚያደርጉህን ሁኔታዎች፣ ሰዎች እንደሆኑ ለይተህ አውጣና ከህይወትህ ቆርጠህ ጣላቸው፡፡

### ኃላፊነት ውሰድ

ሰበበኛውን ቅበረው፤ ያለበለዚያ አንተኑ ይቀብርሃል፡፡ በህይወት ውስጥ አንዳንዱን ሰው ከፍ የሚያደርገው፤ ሌላውን ደግሞ ዝቅ የሚያደርገው ችግሮች አይደሉም፡፡ ውሳኔዎች ናቸው፡፡ እንጂማ! አንተን የገጠመህ ችግር እኮ ሁሉንም ይገጥመዋል፡፡ ትምህርት ናላውን ያዞርበታል፡፡ ሥራ ይከብደዋል፡፡ ሥራ ፍለጋ ሲንከራተት ይውላል፡፡ አብዛኛው ሰው እንደዛ ነው፡፡ በትዳሩ ደስተኛ አይደለም፡፡ አንተን የገጠመህ ችግር ሁሉም ይገጥመዋል፡፡ ልዩነቱ ችግሩ አይደለም፡፡ ለችግሩ የምትሰጠው ምላሽ ነው፡፡ የምተሰጠው ምላሽ ደግሞ ኃላፊነት መውሰድ መሆን አለበት፡፡

ኃላፊነት መውሰድ ማለት ከፈጣሪ ቀጥሎ ለራሴ ያለሁት እኔ ነኝ ብሎ ለውጡን መጀመር ነው፡፡ ከማንም አለመጠበቅ ነው፡፡ ሁኔታዎች እስኪቀየሩ አለመጠበቅ ነው ኃላፊነት መውሰድ፡፡ ከእኛ የባሰ ሁኔታ ውስጥ ሆነው ህይወታቸውን የቀየሩ ብዙ ሰዎች አሉ፡፡ አንተ እድለ ቢስ ስለሆንክ አይደለም። ሰነፍ ስለሆንክ አይደለም፡፡ በተፈጥሮ ያልታደልክ ሰው ስለሆንክም አይደለም፡፡ ኃላፊነቱን ስላልወሰድክ ነው፡፡ ስለዚህ ኃላፊነቱን ውሰድ፡፡ ወዳጄ! በምድራዊ ችግር ተስፋ መቁረጥ የለብህም፡፡ ምክንያቱም አንዱ በር ሲዘጋ ሌላው ይከፈታልና፡፡


### ከወሰንክ አድርገው!

ልብህ አምኖበት ከወሰንክ ወደተግባር ግባ፡፡ አእምሮህ ካሰበ፤ ልብህ ከወሰነ ድርጊት ያስፈልጋል። ለመብላት መወሰን አያጠግብም፡፡ በተግባር መብላት አለብህ፡፡ ባለህበት የምትቀረው ወስነህ ወደ ድርጊት ካልገባህ ነው፡፡ መወሰን ሌላ ነገር ነው፤ ወደ ተግባር መግባት ደግሞ ሌላ ጉዳይ ነው፡፡ መድኃኒቱ አለኝ ብትል ምን ዋጋ አለው! ካልዋጥክ አትድንም። ከወሰንክ ወደ ተግባር መግባት አለብህ፡፡ ውሳኔ አቅጣጫህን ይቀይረዋል፡፡ ድርጊት ደግሞ መንገዱን ያስጀምርሃል፡፡ የማይቆም ጥረት ከፍፃሜ ያደርስሃል። ዋናው ግን መጀመርህ ነው፡፡

ለአንተ ለመለወጥና ለመወሰን ወሳኙ ጊዜ የባነንክበትና የነቃህበት ሰአት ነው፡፡ እሱም አሁን ነው፡፡

# ቅድመ ምርመራ- የማህፀን በር ጫፍ ካንሰርን ለመከላከል

**እየሩስ ተስፋዬ**




ወይዘሮ ለምለም ካሣሁን (ለዚህ ጽሑፍ ሲባል ስማቸው የተቀየረ) የማህፀን በር ጫፍ ካንሰር ታማሚ ናቸው፡፡ ሕመሙ ሲበረታባቸው ከአርሲ ወደ አዲስ አበባ ለተሻለ ሕክምና ከመጡ አንድ ዓመት ሊሞላቸው ነው፡፡ በአሁን ወቅት በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ሕክምናቸውን እየተከታተሉ ይገኛሉ፡፡ አሁን ደግሞ በጤናቸው ላይ መሻሻል እያዩ መጥተዋል፡፡

የአምስት ልጆች እናት የሆኑት ወይዘሮ ለምለም፤ በበሽታው ምክንያት መገለል ደርሶባቸዋል፡፡ ከዚህ ቀደም የተለያየ ሕክምና አድርገዋል፡፡ በአሁን ወቅትም የጨረር ሕክምናቸውን እየተከታተሉ ነው፡፡ ከትናንት ዛሬ የተሻለ እንደሆነ አምነው ከሕመማቸው ለመፈወስ ሕክምናቸውን አጥብቀው እየተከታተሉ ይገኛሉ፡፡

እ.ኤ.አ በ2020 የዓለም የጤና ድርጅት ባወጣው ሪፖርት መሠረት ከ600ሺህ በላይ ሴቶች በማህፀን በር ጫፍ ካንሰር ተጠቅተዋል፡፡ ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው ሀገራት፣ በክትባት እጥረትና አስቀድሞ ምርመራ ለማድረግ በቂ ግብዓት ባለመኖር ምክንያት ከፍተኛ የሞት መጠን እንደሚመዘገብም ይኸው መረጃ ያሳያል፡፡ በዚህ መረጃ መነሻነት የማህፀን በር ጫፍ ካንሰር በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሴቶች ሞት ምክንያት ከሆኑ በሽታዎች መካከል በግንባር ቀደምነት ይጠቀሳል፡፡

በበሽታው በአብዛኛው እድሜያቸው ከ23 እስከ 49 ዓመት የሚሆኑ ሴቶች እንደሚያጠቃም ነው በዓለም አቀፍ ደረጃ የተሠሩ ጥናቶች የሚያመለክቱት፡፡ በአፍሪካም ከጡት ካንሰር ቀጥሎ የማህፀን በር ጫፍ ካንሰር የብዙ ሴቶችን ሕይወት በመቅጠፍ በሁለተኛ ደረጃ መቀመጡን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

ዶክተር ማለደ ቢራራ በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ኮሌጅ የማህፀንና ፅንስ ስፔሻሊስት ሐኪም ናቸው፡፡ እንደ እርሳቸው ማብራሪያ፣ የማህፀን በር ጫፍ ካንሰር ከማህፀን የታችኛው ክፍል የሚነሳ ነው፡፡ ይህ ካንሰር 99 በመቶ የሚመጣው ‹‹ሂውማን ፓፒሎማ ቫይረስ›› (Hpv) በተባለ ቫይረስ አማካኝነት ነው፡፡ ቫይረሱ እንዲመጣ የሚያደርጉ የተለያዩ አጋላጭ ሁኔታዎች አሉ፡፡

ከነዚህም ውስጥ አንዱ ከዚህ በፊት የአባላዘር በሽታ መኖር ነው፡፡ ከአንድ በላይ የወሲብ ጓደኛ መኖርና ግንኙነት ማድረግ እንዲሁም በለጋነት እድሜ ቶሎ ወሲብ መጀመርም ሌላው አጋላጭ ምክንያት ነው፡፡ በሌላ በኩል ብዙ ልጅ መውለድም ለቫይረሱ አጋላጭ ከሚያደርጉ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ሆኖ ይጠቀሳል፡፡

ዶክተር ማለደ እንደሚናገሩት፣ የማህፀን በር ጫፍ ካንሰር ሕመም ሲጀምር ምንም አይነት ምልክቶችን ላያሳይ ይችላል፡፡ በዚህም የተነሳ ቫይረሱ በሰውነት ውስጥ ገብቶ ምልክቶች ለማሳየት እስከ አስር ዓመታት ስለሚፈጅበት ምልክቶቹን በቶሎ አውቆ ወደ ሕክምና ለመሄድ አዳጋች ይሆናል። ከዚህ ጋር ተያይዞም ቫይረሱ በሰውነት ውስጥ የሚኖረው ሥርጭት እየበዛ እና እየተስፋፋ ሲሄድ ምልክቶቹ መታየት ይጀምራሉ፡፡

በሽታው ሳይታወቅ በቅድመ ካንሰርነት ደረጃ የሚታይ ሲሆን በአብዛኛው ጊዜ የሚከሰተው ግን በ20ዎቹ እና በ30ዎቹ የዕድሜ ክልል ውስጥ ነው፡፡ ምልክትም አይኖረውም፡፡ ስለዚህ ስለዚህ ማንኛውም ለአቅመ ወሊድ የደረሰች ሴት ወደ ጤና ተቋማት በማምራት እና ምርመራ በማድረግ ራሷን ማወቅ እንደሚኖርባት በጤና ባለሙያዎች ይመከራል፡፡

የማህፀን በር ጫፍ ካንሰር ቅድመ ምርመራ በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ ሳይገደብ በተለያዩ ቦታዎች ምርመራ ማድረግ የሚቻልባቸው ሁኔታዎች ተፈጥሯል፡፡ በሽታው በቅድመ ካንሰር ደረጃ ላይ ከተገኘ በሀገር ውስጥ ሕክምናውን መከታተል ይቻላል፡፡ የሕክምና ክትትል በሚገባ ከተደረገም በሽታው የሚድን እና የሚጠፋ ነው፡፡

> **‹‹የማህፀን በር ጫፍ ካንሰር ሕመም ሲጀምር ምንም አይነት ምልክቶችን ላያሳይ ይችላል፡፡ በዚህም የተነሳ ቫይረሱ በሰውነት ውስጥ ገብቶ ምልክቶች ለማሳየት እስከ አስር ዓመታት ስለሚፈጅበት ምልክቶቹን በቶሎ አውቆ ወደ ሕክምና ለመሄድ አዳጋች ይሆናል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም ቫይረሱ በሰውነት ውስጥ የሚኖረው ሥርጭት እየበዛ እና እየተስፋፋ ሲሄድ ምልክቶቹ መታየት ይጀምራሉ››**

ነገር ግን በሽታው በቅድመ ካንሰር ደረጃ ላይ እያለ ሳይታወቅ በዛው ከቀጠለ እና ወደሙሉ ካንሰርነት ከተቀየረ ምልክት ማሳየት ይጀምራል። ምልክቶቹም በማህፀን አካባቢ የመድማት፣ እብጠት፣ የሕመም ስሜት እንዲሁም በሰገራ እና በሽንት ላይ የተለዩ እና ያልተለመደ ፈሳሽ መታየት ሊያጋጥም ይችላል፡፡

ከካንሰር ጋር የተያያዘ የተጠናከረ የምዝገባ ሥርዓት ባለመኖሩ የማህፀን በር ጫፍ ካንሰር በሽታ በኢትዮጵያ ያለበትን ደረጃ ከሕዝብ ቁጥር አንፃር ይህን ያህል ነው ብሎ ደፍሮ ለመግለፅ ያስቸግራል። በአጠቃላይ ግን በየዓመቱ ከአምስት ሺህ እስከ ስድስት ሺህ የሚሆኑ አዳዲስ የማህጸን በር ጫፍ ካንሰር ታማሚዎች እየተገኙ መሆኑን ከሆስፒታሎች ከሚገኙ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም በሽታው ከኢትዮጵያ አልፎ በአፍሪካ ደረጃ ከጡት ካንሰር ቀጥሎ በሴቶች ላይ የሚከሰት ሁለተኛ ደረጃን የያዘ የካንሰር ዓይነት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ዶክተር ማለደ እንደሚያስረዱት፣ የማህፀን በር ጫፍ ካንሰር ብዙ ሴቶችን ለሞት ከሚዳርጉ የካንሰር ዓይነቶች አንዱ ነው፡፡ ከሌሎች የካንሰር አይነቶች ለየት የሚያደርገው ግን አስቀድሞ መከላከል የሚቻል መሆኑ ነው፡፡ ጤናማ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ አንደኛው መከላከያ መንገድ ሲሆን ሁለተኛው እና በጣም የሚከረው ደግሞ ቫይረሱን የሚከላከል የኤች.ፒ.ቪ. (HPV) ክትባት መውሰድ ነው፡፡

እ.ኤ.አ ከ2018 ጀምሮ በተለይም ግብረ ስጋ ግንኙነት ያልጀመሩ እድሜያቸው ከ9 ዓመት ጀምሮ እስከ 15 ዓመት ድረስ ላሉ ልጃገረዶች የሚሰጠውን ክትባት መውሰድ በሽታውን በሚገባ ለመከላከል ያግዛል፡፡

ምናልባትም መከላከያ መንገዶች ሳይተገበሩ ቀርተው በሽታው በቅድመ ካንሰርነት ደረጃ ከታወቀ ማከም ይቻላል፡፡ በሽታው ታውቆ መከላከል እንዲቻል ግን ማኅበረሰቡን ለማስተማር የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች መሠራት ይኖርባቸዋል፡፡

እድሜያቸው ለአቅመ ወሊድ የደረሱ ሴቶችም ወደ ሕክምና ተቋማት በማቅናት ራሳቸውን ማወቅ ከበሽታው ራሳቸውን መከላከል ይኖርባቸዋል። በመንግሥት በኩልም ውጤታማ የሆኑ ሀገራት ልምድን በመቅሰም ክትባቱን ማስፋፋት ይገባል፡፡

በሌላ በኩል የማህፀን በር ጫፍ ካንሰር የተገኘባቸውን ሴቶችን ማከም ያስፈልጋል፡፡ ይህን ለማድረግም የሕክምና ተቋማት ዝግጁ ናቸው። ለአብነትም እንደ ቅዱስ ጳውሎስ፣ ጥቁር አንበሳ እና ሌሎች ሆስፒታሎች የቀዶ ህክምና በማድረግ፣ የጨረር ሕክምና በመስጠት ሕክምና የሚሰጡ ሲሆን፤ ከሁሉም በላይ ግን መለመድ እንዲሁም መተግበር ያለበት አስቀድሞ መከላከል ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሠራበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

የመከላከያ ዘዴዎችን በማስተማርና ግንዛቤውን ከገጠር እስከ ከተማ ድረስ በማስፋፋት በበሽታው የሚያዙ ሴቶች ቁጥር ለመቀነስ ብዙ መሥራት ይገባል፡፡ ምንም እንኳን በአዲስ አበባ እና በክልሎች መከላከል እንዲቻል የሕክምና ተቋማት ዝግጁነት ይኑር እንጂ በግንዛቤ እጥረትና በሌሎችም ምክንያቶችም ወደነዚህ ጤና ተቋማት ሄዶ ቅድመ ምርመራ የማድረጉ ልምድ በሴቶች በኩል እምብዛም አይታይም፡፡ ስለዚህ የቅድመ ማህፀን በር ጫፍ ካንሰር ምርመራ ልምድን ማዳበር ያስፈልጋል፡፡

የሚሰጠው ክትባት በዋጋ ደረጃ ውድ የሚባል በመሆኑ ወደ ኢትዮጵያ እየገባ ያለው በእርዳታ መልክ ነው፡፡ መንግሥትም ወጪን በመጋራት ከሌሎች ክትባቶች ጋር በማዛመድ ፕሮግራሙ ውስጥ በማካተት ቀጣይነት ባለው መልኩ ያለማቋረጥ እንዲቀጥል እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ተሳትፏቸው በማድረግ ክትባቱ ቀጣይነት ባለው መልኩ እንዲሰጥ ለማድረግ የድርሻቸውን ቢወጡ በበሽታው የሚያዙ ሴቶችን ቁጥር መቀነስ ይቻላል፡፡

የጤና ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ደረጀ ዱጉማ በወቅታዊ የጤና ጉዳዮች ላይ በቅርቡ በሰጡት መግለጫ፤ ከካንሰር ጋር የተጀመረው ርብርብ እልህ አስጨራሽ ቢሆንም በርካታ ርቀቶች መጓዝ መቻሉን ገልፀዋል፡፡ ርብርቡ አንድም ማኅበረሰቡ ስለ ካንሰር በደንብ እንዲያውቅ፤ አውቆም በቅርብ ወዳለው ጤና ተቋም በመምጣት አገልግሎት እንዲያገኝ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት ከ28 በላይ ጤና ተቋማት የካንሰር ታማሚዎች የኬሞ ቴራፒ ሕክምና አገልግሎት የሚያገኙበት ሁኔታ መመቻቸቱንና በእነዚህ 28 ተቋማት ላይ ተጨማሪ መድኃኒቶችን፣ የሰው ኃይልን በማሰማራት ሕክምና እንዲሰጡ እየተደረገ እንደሚገኝ አብራርተዋል፡፡

የጨረር ሕክምና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መሆኑንም የጠቀሱት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ቀደም ሲል በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ብቻ ይሰጥ የነበረው የጨረር ሕክምና አሁን ላይ ወደ ሰባት ማዕከላት ለማሳደግ ጥረት እየተደረገ እንደሚገኝ አስታውቀዋል፡፡ በአሁኑ ግዜ የጨረር ሕክምናውን ሀረማያ፣ ጅማ እና ጥቁር አንበሳ ሆስፒታሎች እየሠሩ መሆናቸውንና አራቱ ደግሞ በቅርብ ጊዜ ወደ ሥራ እንደሚገቡ ተናግረዋል፡፡

ከሌሎች የካንሰር አይነቶች በጣም አንገብጋቢና እናቶችን እየነጠቀ ያለው የማህፀን በር ጫፍ ካንሰር (cervical cancer) ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ከ1 ሺህ 300 በላይ ጤና ተቋማት በሽታውን የመለየት አቅም አላቸው ብለዋል፡፡ ተቋማቱ የመለየት አቅም እንዲያጎለብቱ የተደረገ መሆኑንና በሁሉም ወረዳዎች ቢያንስ አንድ ጤና ተቋም የማህጸን በር ጫፍ ካንሰርን መለየት እንደሚችል እንዲሁም ለይቶም እዛው ሕክምና መስጠት መቻላቸውን ተናግረዋል፡፡

ሚኒስትር ዴኤታው እንደተናገሩት፣ የማህፀን በር ጫፍ ካንሰር ገና በጅምር ያለ ከሆነ ማከም፤ ካልሆነ ደግሞ ወደሚቀጥለው ጤና ተቋም ሪፈር ማድረግ የሚችልበት አግባብ ተፈጥሯል፡፡ በዚህ ስድስት ወር ብቻ ከ264 ሺህ በላይ የማህፀን በር ጫፍ ካንሰር ከመለየት ባሻገር ተጨማሪ ሕክምና የሚፈልጉትን ወደ ሕክምና ተቋማት እንዲሄዱ ተደርጓል፡፡

የብዙ ሴቶችን ሕይወት እየነጠቀ ያለውን የማህፀን በር ጫፍ ካንሰር ለመከላከል ክትባቱን መውሰድ፣ ሲጋራ አለማጨስ፣ የአባላዘር በሽታ ካለ መታከም፣ ኤች አይ ቪ ኤድስን መከላከል እና መታከም እንዲሁም የቅድመ ካንሰር ምርመራ ማድረግ ወሳኝ እርምጃ ነው፡፡

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## የጅብ ችኩል ...

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

ይህ ማኅበራዊ ሚዲያ ይሉት ጉዳይ የራሱ ችግር ቢኖረውም ጥቅሙ ደግሞ የዚያኑ ያህል ነው:: ዕድሜ ለቴክኖሎጂ ይሁንና ትኩስ መረጃዎችን ሳያቀብለን ውሎ አያድርም:: ያለውን፣ የጠፋውን፣ የራቀ የመጣውን በእኩል እያራመደ ሰውን ከሰው ያገናኛል:: ዓለምን በሰንሰለት ያቆራኛል::

እንዲህ መሆኑ መልካም ነው:: ማንም ተገቢውን መረጃ በትክክለኛው መንገድ ማግኘትን አይጠላምና። አንዳንዴ ደግሞ መረጃ ከትክክለኛነት ይልቅ ፍጥነት ላይ ብቻ ያተኩራል:: እንዲህ በሆነ ጊዜ ጉድለቱ ይጎላል:: አጋጣሚውም ከማስደንገጥ አልፎ ከትዝብት መጣሉ አይቀሬ ነው::

ብዙ ጊዜ ሁነቱን ተጣድፈውና ተሽቀዳድመው የሚልኩ አካላት ሙሉ ትኩረታቸው ፍጥነት ላይ ሲሆን መረጃዎች ይዛባሉ:: መታረም፣ ለአንባቢ መቅረብና መቅረት የሚኖርባቸው ነጥቦችም ይዘነጋሉ:: አንዳንዴ ከእርጋታ ይልቅ ፍጥነት በቀደመ ጊዜ ከስህተት በላይ የሚሆኑ አጋጣሚዎች ሊስተናገዱ ግድ ይላል::

ከሰሞኑ ያስተዋልኩትን አንድ ትዝብት ላጋራችሁ:: በቅርቡ ነው፣ በሀገራችን በርካታ የሥነጽሑፍ ሥራዎችን ያበረከቱልን፣ አንድ ታዋቂ ደራሲ የመሞታቸው ዜና መዘገብ ጀምሯል:: እሳቸው ታላቅ አስተዋጽኦ እንደማበርከታቸው ለማንነታቸው ግብአት የሚሆኑ ማስረጃዎች በየአጋጣሚው እየተነበቡ ነው::

ይህን እውነታ በየአቅጣጫው የሚጽፉ ሰዎች የራሳቸውን አስተያየት ማቅረባቸውን ቀጥለዋል:: ኀዘኑን በድንገት የተጋሩ በርካቶች ስሜታቸውን እየገለጹ ስለእኚሁ ታዋቂ ሰው ያላቸውን ስሜት መጥቀስ ይዘዋል:: በድንገት አንድ ጽሑፍ ላይ ዓይኖቼ አተኮሩ:: ስለእሳቸው የሚያወጋ ረዘም ያለ መረጃ ነው::

ጽሑፉ ስለእኚሁ አንጋፋ ሰው ዳጎስ ያለ ሃሳብ ይዟልና በደቂቃዎች በርካታ ሰዎች እየተቀባበሉ አጋሩት። በዚህ መረጃ ውስጥ ስለግለሰቡ ውልደትና ዕድገት፣ ስላበረከቱት የሥነጽሑፍ አስተዋጽኦ፣ ድንቅ ሥራዎቻቸው ለዩኒቨርሲቲዎች የትምህርት ግብአት አስተዋጽኦ ማበርከታቸውንና ይህም በሀገሪቱ የሥነጽሑፍ ዘርፍ ታላቅ ግምት የሚሰጠው ስለመሆኑ ይተነትናል::

እውነቱን ለመናገር ይህ ጽሑፍ በወጉ የተቀመረና በቂ ማስረጃዎችን ያጣቀሰ በመሆኑ ማንም ሳያነበው የሚያልፍ አይሆንም:: የእኚህ ታላቅ ሰው ህልፈት በተሰማ አጭር ጊዜ ውስጥ ይህን መሰሉን ዘገባ ማቅረብ መቻል ደግሞ የሚያስገርምና የሚያስመሰግን ጭምር ነው::

እኔንም ሆነ ሌሎች ልብ ያሉ ሰዎችን ያስገረመን ግን የጽሑፉ መረጃ ጠገብነት ብቻ አይደለም:: የሕይወት ታሪኩ ዘገባ በአግባቡ ተጽፎ እንደተጠናቀቀ የተስተዋለው ስህተት እንጂ:: ጽሑፉ በሕይወት ስለተለዩን የሀገር ባለውለታ ሲያወጋን ቆይቶ በመጨረሻው መስመር ላይ «ነፍስ ይማር» ማለት ሲገባው «ረጅም ዕድሜና ጤና ለታላቁ ደራሲ» ሲል ይደመድማል::

ከዚህ እውነት መረዳት የሚቻለው ለሚቀርቡ መረጃዎች ከጥንቃቄ ይልቅ ለፍጥነት ቅድሚያ መሰጠቱን ነው:: አስገራሚው ጉዳይ ደግሞ ይህን መረጃ በጥልቀት ያላስተዋሉ አብዛኞች የመጀመሪያውን ዝርዝር ብቻ አይተው ለሌሎች ማጋራታቸው ነው::

በሕይወት የሌለን ሰው ረጅም ዕድሜ ያስመኘው ጽሑፍ የቀረበው ብዙዎቻችን እንዳሰብነው በዕለቱ ተጽፎ ሳይሆን ቀድሞ ከተጻፈው መረጃ ላይ በቀጥታ ተወስዶ ነው:: ይህ ሲሆን ጽሑፉ ጊዜን፣ እውነታንና ወቅታዊ መረጃን ያካተተ አልነበረም::

ወደ ሌላው ትዝብቴ ልሻገር:: አሁንም ማኅበራዊ ሚዲያው ላይ የወጣን መረጃ ይመለከታል:: ዘገባው ሰሞኑን ለአፍሪካ ኅብረት ጉባኤ ወደ ሀገራችን ከመጡት የሶማሊያ ፕሬዚዳንት ጋር ይገናኛል:: የሶማሊያው ፕሬዚዳንት ሀሰን ሼክ መሐመድ ለጉባኤው ተሳትፎ ወደ ኢትዮጵያ በመጡ ጊዜ በቦሌው ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ አቀባበል ተደርጎላቸው ነበር::

ሰውየው የአንድ ሉአላዊት ሀገር ፕሬዚዳንት እንደመሆናቸው ለማንኛውም የሀገር መሪ የሚደረገው የክብር አቀባበል አልተጓደለባቸውም:: ይህን እውነት ያላስተዋሉ አንዳንዶች ግን በራሳቸው የማኅበራዊ ገጽ ላይ የተሳሳተ መረጃን ለማቀባበል አልዘገዩም::

እንደእነሱ ሃሳብ ፕሬዚዳንቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር በሚዘመርበት ጊዜ ያለምን ክብር ከመድረክ ወርደው ሲሄዱ ታይተዋል:: ቆየት ብሎ የወጣው መረጃ ግን እንግዳው እንደተባሉት ሆኖ ከመድረክ ወርደው ለመሄድ ፈጽሞ አልሞከሩም:: አጋጣሚው የሆነው አቀባበሉን ያደረጉላቸው አንድ የሀገሪቱ ሚኒስትር በፕሮቶኮሉ መሠረት ከመድረክ እንዲወርዱ በእጃቸው ምልክት በማሳየታቸው ነበር::

ይህችን አፍታ በካሜራ ዓይን አይተናል ያሉቱ ግን ጉዳዩን ከወቅታዊ ሁኔታ ጋር ለማቀናጀት አልዘገዩም። ይህ መረጃ እንዲህ ዓይነቱን ትርጉም አዝሎ በማኅበራዊ ሚዲያው ከተሰራጨ በኋላ ስህተት መሆኑን የተረዱ ሌሎች በግልጽ ተቃውመውታል::

ጥድፊያን ያዘለው ዜና አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የዲፕሎማሲ ግንኙነቶችን የሚጎዳ ነውና ከፍጥነት በፊት ቆም ብሎ ማስተዋል እንደሚገባ አፅንኦት ተሰጥቶታል። ይህ «የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል» ይሉት ዓይነት ዘገባ እንደቀላል ቢታይም የሚያስከትለው ግለሰባዊና ሀገራዊ ጉዳት የዋዛ አይሆንም::

በተመሳሳይ ሁኔታ በዚሁ የማኅበራዊ ገጽ ላይ ተዘግቦ ሰዎች በተዛባ እሳቤ ሲነጋገሩበት የነበረውን አንድ ጉዳይ ላክል:: ዘገባው በሀገራችን አንድ ታዋቂ ሚዲያ ላይ የተዘገበ ነው:: ይህን ዘገባ በራሳቸው ገጽ የለጠፉ አንዳንዶች ደግሞ መልዕክቱን «ይድረስ» ሲሉ አጋርተውታል:: በእኔ ግምት ይህ መረጃ ለብዙዎች ትምህርትና ጥንቃቄ የሚበጅ በመሆኑ የተለጠፈ ነው ብዬ አምናለሁ ::

የዘገባው ሃሳብ በአጭሩ የሦስት ዓመት ሕፃንን ከእንግሊዝ ወደ ኬንያ በመውሰድ ስላስገረዘችው እናት የሚያስረዳ ነው:: ይህች እናት የሦስት ዓመት ሴት ልጇን ኬንያ ድረስ በመውሰድ በማስገረዟ የእስር ቅጣት ተጥሎባታል:: እናት ድርጊቱን የፈጸመችው እሷ ያለፈችበት የሕይወት መንገድ በመሆኑና ባህል ነው ብላ ስለምታምን እንደሆነ አስረድታለች::

«ትክክል ነኝ» በሚል የፈጸመችው ግርዛት ግን በእንግሊዝ ሕግ መሠረት ወንጀል በመሆኑ የሰባት ዓመት እስራት እንደተፈረደባት ዘገባው ያስረዳል:: ወዳጆቼ! እዚህ ላይ ልብ እንድትሉልኝ የምፈልገው ይህ ዘገባ የግርዛት ጉዳይ መሆኑን ብቻ ነው::

በዜናው የመጀመሪያ መስመር ላይም የሦስት ዓመቷን ሕፃን ወደ ኬንያ በመውሰድ ያስገረዘችው ሴት እስር ተፈረደባት በሚል ተጠቅሷል:: አነጋጋሪው ጉዳይ ግን እንዲህ መሆኑ ላይ አይደለም:: ዜናውን በጨረፍታ ያነበቡና ለአስተያየት የተጣደፉ አንዳንድ ሰዎች የሚሰጡት ሃሳብ ማስገረሙ ነው::

የዚህ ጽሑፍ አንባቢዎች «ያስገረዘችው» የሚለውን ሃሳብ እንድትይዙልኝ እሻለሁ:: እነዚህ አንዳንድ ያልኳቸው ሰዎች ግን ይህን ቃል በተጻፈው መሠረት ተገንዝበው አላነበቡትም :: በራሳቸው ጥድፊያ ሞልተው እንዳሻቸው በማድረግ አቀባብለውታል::

አንባቢዎቹ «ያስገረዘችው» የሚለውን ቃል «ያስረገዘችው» ብለው አንብበውታል:: አንብበው ደግሞ ዝም ብቻ አላሉም:: በጽሑፉ ግርጌ በተቀመጠው የሃሳብ ማስፈሪያ ቦታ ላይ በንዴትና በብስጭት ተሞልተው ያልተገባ ሃሳብ ተቀባብለውበታል::

አስገራሚው ነገር የእነሱን የንዴት ሃሳብ የሚጋሩ ሌሎች የተሳሳተውን ጽሑፍ ከመነሻው ደግመው ከማንበብ ይልቅ ሃሳቡን እየደገሙና እየተቀባበሉ እሳት ሲጭሩና ነገር ሲያጋግሉ መቆየታቸው ነው::

ይህ ዓይነቱ የጅብ ችኩልነት ድርጊት አሁንም ከራስ አልፎ ብዙኃንን ለመጉዳት የዘገየ አይሆንም:: «ከአፍ ከወጣ አፋፍ» እንዲሉ ሆኖ እንደዋዛ የምንሠራቸው ስህተቶች ስር ሰደውና አጉል ትርጉም ተሸክመው የሚያስከትሉት ጥፋት የበዛ ነውና ጠንቀቅ ብንል ይበጃል::

# ዓለም አቀፍ

## የየመኑ ሁቲ አማጺ ቡድን በቀይ ባሕር የሚወስደውን እርምጃ እንደሚገፋበት ገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የየመኑ ሁቲ አማጺ ቡድን በቀይ ባሕር የሚወስደውን እርምጃ እንደሚገፋበት ገለጸ::

ለፍልስጤም ነፃነት እታገላለሁ የሚለው ሐማስ በእሥራኤል ላይ ድንገተኛ ጥቃት ማድረሱን ተከትሎ የተጀመረው ጦርነት አምስት ወሩ ላይ ይገኛል::

እሥራኤል በወሰደችው የአየር እና ምድር ላይ ጥቃት የተገደሉ ፍልስጤማውያን ቁጥር 30 ሺህ የደረሰ ሲሆን ጦርነቱ እንዲቆም ብዙዎች ቢጠይቁም እስካሁን ሊቆም አልቻለም::

የየመኑ አማጺ ቡድን ከፍልስጤም ጎን ነኝ በሚል ከእሥራኤል፣ አሜሪካ እና ብሪታንያ ጋር ንክኪ የሆኑ የንግድ መርከቦችን በመምታት ላይ ይገኛል::

የሁቲ አማጺያን በቀይ ባሕር ላይ በሚያደርሰው ጥቃት ምክንያት የዓለም ንግድ በመጎዳት ላይ ሲሆን የግብጹ ስዊዝ ካናል መስመርም የሚያስተናግዳቸው መርከቦች ቁጥር በመቀነሱ ገቢውም ቀንሷል::

አማጺ ቡድኑ በባብኤል ማንዲብ እና ኤደን ባሕረ ሰላጤ የንግድ መስመር ላይ በሚመላለሱ መርከቦች ላይ የሚያደርሰውን ጥቃት እንደሚቀጥልበት አስታውቋል ሲል አል ዐረቢያ ዘግቧል::

የሁቲ አማጺ ቡድን መሪ አብዱል ማሊክ አል ሁቲ በቴሌቪዥን የቀጥታ ስርጭት በተላለፈ ንግግራቸው እንዳሉት የቀይ ባሕር እና አረቢን ባሕር ላይ እየተወሰደ ያለው ኦፐሬሽን ስኬታማ ነው ይህንንም እንቀጥልበታለን ብለዋል::

የቀይ ባሕር ትራንስፖርት ከዓለም ንግድ የ35 በመቶ ድርሻ ያለው ሲሆን 12 በመቶ የሚሆነው የቀይ ባሕር ትራንስፖርት በሁቲ አማጺያን ጥቃት ምክንያት እንደተስተጓጎለ ተገልጿል::

ግብጽ በበኩሏ ከስዊዝ ካናል ስታገኘው ከነበረው ገቢ የ50 በመቶ ቅናሽ እንዳሳየባት አስታውቃለች::




በእሥራኤል ጥቃት የተገደሉ ፍልስጤማውያን ቁጥር 30 ሺህ አልፏል

## ፑቲን የሩሲያ ኑክሌር ኃይል 95 በመቶ መዘመኑን ገለጹ



ሩሲያ እያመረተች ያለችውን ዘመናዊ መሣሪያዎች ተወዳዳሪ እንደሌላቸው በተደጋጋሚ እየገለጸች ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን የሩሲያ ኑክሌር ኃይል 95 በመቶ መዘመኑን ገለጹ።

የሩሲያው ፕሬዚዳንት ፑቲን 95 በመቶ የሚሆነው የሩሲያ ስትራቴጂክ ኑክሌር ኃይል መዘመኑን ገልጸዋል።

ፑቲን የሩሲያ አየር ኃይል አራት ኑክሌር የመሸከም አቅም ያላቸው ሱፐርሶኒክ ቦምብ ጣይ አውሮፕላኖችን ማምረቱን በምሳሌነት ጠቅሰዋል።

ፕሬዚዳንት ፑቲን ይህን ያሉት ቱ-160ኤም በተባለችው ኑክሌር ተሸካሚ ቦምብ ጣይ አውሮፕላን ላይ ሲበሩ ከታዩ ከአንድ ቀን በኋላ በተከበረው 'የአባት ሀገር ተከላካይ' አመታዊ ቀን ላይ ነው።

ፑቲን በዩክሬን የተጀመረው ጦርነት ሁለተኛ አመት ዋዜማ ላይ በዩክሬ «ለእውነት እና ለፍትህ» እየተዋጉ ነው ያሏቸውን ወታደሮች ጀግኖች ሲሉ አሞግሰዋቸዋል።

የሩሲያ የመሬት፣ የባሕር እና የአየር የኑክሌር አቅም መዘመኑን እና በየጊዜው እየዘመነ እንዲሄድ እየተደረገ መሆኑን ፑቲን ተናግረዋል።

«በአሁኑ ወቅት ዘመናዊ መሣሪያዎች በስትራቴጂክ ኑክሌር ኃይላችን ውስጥ 95 በመቶ ድርሻ ይዘዋል። የባህር ኃይል 'ኑክሌር ትሪያድ' ወይም ኑክሌር ኃይል ሙሉ በሙሉ ዘምኗል።»

ሩሲያ ፑቲን ግልጽ ያላደረጉት የተኩስ ሥርዓት ያለውን አዲሱን ዚርኮን ሚሳይል ማምረት ጀምራለች ብለዋል።

ፑቲን «ቀጣዩ ሥራ አስተማማኝ የሆኑ ሞዴሎችን መሥራት ማምረት እና በወታደራዊ ዘርፎች ሰውሠራሽ አስተውሎትን ማስተዋወቅ ነው» ሲሉም ተናግረዋል።

ሩሲያ እያመረተች ያለችውን ዘመናዊ መሣሪያዎች ተወዳዳሪ እንደሌላቸው በተደጋጋሚ እየገለጸች ነው።

በትናንትናው ዕለት ፑቲን ሲበሩባት የታየችው ቱ-160ኤም የተሰኘችው ኑክሌር ተሸካሚ ቦምብ ጣይ አውሮፕላን 12 ሚሳይሎችን ተሸክማ 12ሺ ኪሎሜትር መብረር እንደምትችል ተገልጿል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ትልቅ የልማት እና የሰላም አቅም የሚፈጥር ውይይት!

የኦሮሞ ሕዝብ ለፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ፍትህ ለዘመናት ከሌሎች የሀገሪቱ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ጋር በመሆን ከፍተኛ ትግል አድርጓል። ለውጡ ስኬታማ እንዲሆንም ታላቅና ውድ መስዋዕትነት ከፍሏል። በዚህም እንደ ሀገር የተጀመረው ለውጥ እያስገኘ ካለው ትሩፋት ተጠቃሚ እየሆነ ነው።

በአንድ በኩል ከይስሙላ እራስን በራስ የማስተዳደር የፖለቲካ ፌዝ ወጥቶ በተጨባጭ እንደ አንድ ፌዴራል የክልል መንግሥት የራሱን ጉዳይ በራሱ የሚወስንበትን፤ ከዚህም ባለፈ በሀገራዊ ጉዳይ ቁመናውን በሚመጥን መልኩ ተሳታፊ የሚሆንበትን የተሻለ ዕድል አግኝቷል።

ለውጡ ከመቼውም ጊዜ በተሻለ፤ ላለፉት ስድስት አስርት ዓመታት የኦሮሞ ሕዝብ ሲታገልላቸው የቆዩትን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መብቶች በማጎናጸፍ፤ ሕዝቡ ወደ ልማት የሚገባበትን አስቻይ ሁኔታ ፈጥሯል፤ ይህንንም ብዙዎች ተገንና ተስፋ አድርገው ወደ ሥራ ገብተዋል። ውጤታማ የሆኑበት እውነታም ታይቷል።

የኦሮሞ ሕዝብ እንደ ሁሉም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ካለው በልማት የመበልጸግ መሻት አንጻር፤ ያለውን የተፈጥሮ እና የሰው ሀብት በማቀናጀት እንደ ሀገር ድህነትን ታሪክ ለማድረግ የተጀመረው ትግል አካል በመሆን ከፍ ባለ መነቃቃት ሲንቀሳቀስም ተስተውሏል።

በክልሉ ካለው ገና ያልተነካ ሰፊ የተፈጥሮ ሀብት እና ብቁ አምራች የሰው ኃይል አንጻር፤ በክልሉ ከለውጡ ማግስት ጀምሮ በብዙ ተግዳሮቶች ውስጥ የተመዘገቡ ውጤቶች፤ በርግጥም የክልሉ ሕዝብ ለልማት መሻቱ ስኬት የሚሆን ሰላም ካገኘ ድኅነትን ተሻግሮ ከትናንት የተሻለ ሕይወት መምራት ብዙ ፈተና እንዳይሆንበት ያመላከቱ ሆነዋል።

ይህ የክልሉ ሕዝብ የመበልጸግ መሻት ግን ከለውጡ ማግስት ጀምሮ በብዙ ፈተናዎች እየተናጠ ስለመሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነው። ሕዝቡ እንደ ሀገር ለውጡን ካጋጠመው ፈተና ባለፈ በስሙ በሚንቀሳቀሱ ኃይሎች በብዙ ተፈትኗል ፤ ብዙ ዋጋ ለመክፈል ተገድዷል።

በአንድ በኩል በኃይል ሥልጣን ለመያዝ ብረት ያነገቡ ኃይሎች፤ በሌላ በኩል ትናንት እንደ ሀገር ከፍ ያለ ዋጋ እንድንከፍል ያስገደደን የሴራ ፖለቲካ በሚያራምዱ ከአብራኩ በወጡ ልጆቹ፤ ያልተገባ ዋጋ ከፍሏል። የዕለት ተዕለት ሕይወቱ ሳይቀር ባልተለመደ መልኩ በስጋት የታጠረ ሆኗል።

ይህን ከኦሮሞ ሕዝብ መንፈሳዊ፣ ባህላዊና ማኅበራዊ እሴት ያፈነገጠ የጥፋት መንገድ ለማረም በክልሉ ሰላምና መረጋጋት ለማስፈን በመንግሥትና በራሱ በኦሮሞ ሕዝብ ብዙ ሥራዎች ተሠርተዋል። ባልተገባ መንገድ ለሚንቀሳቀሱ ኃይሎች በተለያዩ ወቅቶች ተደጋጋሚ የሰላም ጥሪዎችም ቀርበዋል።

በመንግሥትና በሕዝብ ስለ ሰላም እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች በየጊዜው እመርታ እያሳዩ ክልሉ በተሻለ የሰላም መንገድ ላይ ቢሆንም፣ የክልሉ ሕዝብ ለሚፈልገው በሁለንተናዊ ልማት ብልጽግናን ለማምጣት ያለውን መሻት እውን ለማድረግ አሁንም የሰላም ጉዳይ ወሳኝ ስለመሆኑ ብዙም ለጥያቄ የሚቀርብ አይደለም።

ከሰሞኑ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)፤ ከኦሮሚያ ክልል ከተውጣጡ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጋር ያደረጉት ውይይት በክልሉ ዘላቂ ሰላም በማምጣት የተጀመሩ የልማት ሥራዎችን ለማስቀጠልና ውጤታማ ለማድረግ ትልቅ ሕዝባዊ አቅም መፍጠር የሚያስችል እንደሚሆን ይታመናል።

በተለይም የክልሉ ሕዝብ ከሰላም ማጣት በስተጀርባ ያሉ እውነታዎችን በአግባቡ ተረድቶ፤ ዘላቂ ሰላም በማስፈን ሂደት ውስጥ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን የሚያስችለውና፤ ከተለያዩ ውዥንብሮች ወጥቶ የራሱን ነገዎች ብሩህ አድርጎ መሥራት እንዲችል የተሻለ ዕድል የሚፈጥርለት ነው።

መንግሥትም ቢሆን በሕዝቡ ውስጥ ያሉ ቅሬታዎችን ከባለቤቱ አንደበት በመስማት የማስተካከያ ርምጃዎችን በመውሰድ፤ ከሕዝቡ ጋር ያለውን መልካም ግንኙነት በማደስ ለቀጣይ ሰላም ማስፈን ሆነ የልማት ሥራዎች የሕዝቡን ልብ መግዛት የሚያስችለውን ዕድል የሚፈጥርለት እንደሚሆን ይታመናል!

**አዲስ ዘመን**

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የምክክር ኮሚሽኑ ተልዕኮ ለስኬት እንዲበቃ ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ ይገባል

በኢትዮጵያ ሀገራዊ ለውጡ ከመጣ ወዲህ በመንግሥት በኩል የተወሰዱ መልካም እርምጃዎች እንዳሉ ሆነው በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች አለመግባባቶች፣ የፖለቲካ ልዩነቶች፣ የእርስበርስ ግጭቶች፣ ሌሎችም ሀገርን የሚያናጉ የፀጥታ ችግሮች ተከስተዋል። ችግሮቹ አድገውና ጎልብተው የኋላ ኋላ ሀገሪቷን ወደለየለት ጦርነት ውስጥ ከትተዋል፡፡

በተለይም በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል የተከሰተው ጦርነት ሀገሪቷን ከባድ ዋጋ አስከፍሏታል። ይኸው ጦርነት ለበርካታ ዜጎች ሕይወት መቀጠፍ፣ መፈናቀልና ስደት ብሎም ለተለያዩ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ምክንያት ሆኗል። በሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎችም እንዲሁ በተዛቡ ትርክቶች እና ጀብደኝነት በተፈጠሩ ምክንያቶች የሰላም ማጣቶች ተከስተዋል።

እነዚህን ችግሮች ጨምሮ እንደሀገር ይዘናቸው የምጓዛቸውን የአለመግባባትና የግጭት ምንጭ የሆኑ ችግሮችን ለዘለቄታው በውይይት እና በምክክር ለመፍታት ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ ተቋቁሟል። ኮሚሽኑ እስካሁን በተጓዝንባቸው የታሪክ ጅረት ውስጥ በዜጎች መካከል በልዩ ልዩ መልኩ የተፈጠሩ ቅራኔዎችንም ጭምር ለመፍታት ዓላማ የሰነቀ ስለመሆኑም ተነግሯል።

አሁን ላይ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ ከተቋቋመ ሁለት አመት አገባዶ ወደ ሦስተኛ አመቱ እየተጓዘ ነው። በእነዚህ አመታት ውስጥ ከምስረታው ጀምሮ ለሀገራዊ ምክክሩ ጠቃሚ የሆኑ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን ሲሠራና ለምክክሩ አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶችን ሲያሰባስብ ቆይቷል። በዚህም ቀደም ሲል በሌሎች ሀገራት ተሞክረው ውጤት ያመጡና በዚያው ልክ ደግሞ ባለመስማማት የተጠናቀቁ ሀገራዊ ምክክሮች በምን ምክንያት ሊከሽፉ እንደቻሉና ያለውጤት ሊጠናቀቁ እንደቻሉ ተሞክሮ ወስዷል።

ምክክሩ ሀገራዊ ነባራዊ ሁኔታን በተከተለና ሁሉንም ዜጋ ባሳተፈ፤ ሁሉንም አካል ሊያረካ በሚችል መልኩ እንዲካሄድ የሚያስችሉ የቅድመ ሁኔታ ሥራዎች (ከትግራይና ከአማራ ክልል ውጪ) በመላው ሀገሪቱ እያከናወነ ነው። በዚህም ዋናውን ሀገር አቀፍ ምክክር ለማካሄድ የሚያስችሉ ጠቃሚ ግብአቶችን ለመሰብሰብ እንደቻለ ይታመናል።

በዚህ ሀገራዊ የምክክር ሂደት የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች፤ ሴቶች፣ ወጣቶች የማኅበረሰብ መሪዎች፣ የመንግሥት ሠራተኞች፣ የተገለሉ የማኅበረሰብ ክፍሎች፣ መምህራንና ሌሎችም ይገኙበታል፡፡ ለዚህም የሚሆን የተሳታፊነት መስፈርቶችን ኮሚሽኑ በዝርዝር አስቀምጧል፡፡

በምክክር ሂደቱም የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበራት ምክር ቤት፣ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት፣ የኢትዮጵያ ሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ፣ የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር ተባባሪ አካላት ሆነው እንደሚሠሩም ተገልጿል፡፡

በፌዴራል ደረጃ በተመሳሳይ የአጀንዳ መሰብሰብ ሥራ እንደሚከናወን፤ በተመሳሳይ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ዲያስፖራዎችን በዚሁ የምክክር አጀንዳ ውስጥ እንዲካተቱ የማድረግ ሥራ እየሠራም ነው ፡፡

ኮሚሽኑ ሥራው ከአንዱ ምዕራፍ ወደሌላኛው ምዕራፍ እየተሸጋገረ አሁን ላይ፤ የአጀንዳ ማስባሰብ ጀምሯል፤ በዚህም ለሀገሪቱ ሰላምና መረጋጋት ምክንያት የሆኑ አሁናዊ እና የአደሩ ችግሮችን አንጥሮ በማውጣት በውይይት መፍትሔ የሚያገኙበትን ሁኔታ ይፈጥራል። በተለያዩ ጊዜያት ኅብረተሰቡን ወደ ግጭት የመሩ አለመግባባቶች፣ ቅራኔዎችና ሌሎችም የፀጥታና የሰላም መድፍረሶች ምክንያት ጉዳዮችን ነቅሶ ለሀገራዊ ምክክሩ እንዲቀርቡ የማድረግ ሥራ እንደሚሠራም ይጠበቃል፡፡

ኮሚሽኑ ባለው አቅም በብዙ ቁርጠኝነት እስካሁን ባለው ሂደት የሚያስመሰግን ሥራ እየሠራ ቢሆንም፤ በሀገሪቱ እዚህም እዚያም የሚታዩ ግጭቶች ለሥራው ፈተና ሆነዋል። ለዚህ ደግሞ በሰላም ዙሪያ ያለውን

**በአጠቃላይ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ ሥራውን ሠርቶ በሀገሪቱ የሚፈለገው ሰላምና መረጋጋት እንዲመጣ ከራሱ ከኮሚሽኑ፣ ከመንግሥት፣ ከልዩ ልዩ የፖለቲካ ቡድኖችና ከሕዝቡ ብዙ ይጠበቃል**

ችግር ለመፍታት በግጭትና ሰላም ማደፍረስ ሥራ ተጠምደው ያሉ አካላት እጃቸውን መሰብሰብ፤ ሕዝቡ በየጊዜው ለሚያነሳቸው የሰላም ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡

ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ በቅርቡ ከተሳታፊዎች ልየታ ወደ አጀንዳ ማሰባሰብ ምዕራፍ መሸጋገሩ እንደ አዎንታዊ እርምጃ የሚታይ ቢሆንም፤ ወደ ዋንኛው የውይይት ምዕራፍ ገብቶ በሀገሪቱ እየታዩ ያሉ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን በመፍታትና ሰላምና ደህንነትን ለማረጋገጥ ጥርጊያ መንገድ ማመቻቸት እንዲችል የመላውን ኅብረተሰብ ተሳትፎና የፖለቲካ ቡድኖች ይሁንታና ትብብርን ይሻል፤ ከብዙዎችም ብዙ ሥራ ይጠበቃል፡፡

የሀገራዊ ምክክሩ ቢያንስ ቢያንስ ሕዝቡ በችግሮቹ ዙሪያ እንዲወያይ ዕድል ይፈጥራል የፖለቲካ ቡድኖችና ቅር የተሰኙ አካላት በችግሮቻቸው ዙሪያ እንዲያወሩና ለችግሩም ሀገርና ሕዝብን ተጠቃሚ የሚያደርግ ዘላቂ መፍትሔ እንዲያበጁ ዕድል ይፈጥራል፡፡ በሀገሪቱ በልዩ ልዩ መልኩ ለተፈጠሩ አለመግባባቶችና መቋሰሎች ማከሚያ ይሆናል ተብሎም ይገመታል፡፡ ለዚህ ታዲያ መፍትሔው በሁሉም ኅብረተሰብ ክፍል እጅ ላይ ነው፡፡ ሁሉም አካል ለሀገራዊ ምክክሩ ስኬት የበኩሉን አስተዋፅኦ ሊያደርግ ይገባል፡፡

በአጠቃላይ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ ሥራውን ሠርቶ በሀገሪቱ የሚፈለገው ሰላምና መረጋጋት እንዲመጣ ከራሱ ከኮሚሽኑ፣ ከመንግሥት፣ ከልዩ ልዩ የፖለቲካ ቡድኖችና ከሕዝቡ ብዙ ይጠበቃል። የኃይል አማራጭን ወስደው በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ላይ እየተንቀሳቀሱ ያሉ የፖለቲካ ቡድኖች በዚህ ሀገራዊ ምክክር ተሳታፊ ለመሆን ዝግጁነታቸውን ከወዲሁ ማሳየት ይኖርባቸዋል። ሕዝቡም ቢሆን ይህን ሀገራዊ ምክክር በእጅጉ የሚፈልገው ነውና ለሀገራዊ ምክክሩ መሳካት የራሱን አስተዋፅኦ ሊያበረክት ይገባል።

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል፡፡ ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል፡፡ አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል፡ ፡ ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ፡፡ የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ፡፡ በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ፡፡ ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ፡፡ በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ፡፡ ስአስተያየቶቻችሁ፤ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ፡፡

# ትናንትን በዛሬ መስታወት...

መልካምሥራ አፈወርቅ

ወጣቷ ቆንጆ ዓይነ ግቡ ናት፡፡ ያዩዋት ሁሉ የሚወዷት፣ ለቁምነገር፣ የሚያስቧት ውብ፡፡ እሷ ከእኩዮቿ ትለያለች፡፡ ፍጥነት ቅልጥፍናዋ፣ ጨዋታ ለዛዋ ከብዙዎች ያግባባታል። ይህ ማንነቷ በልጅነት ዕድሜዋ ትዳር እንድትይዝ ጎጆ እንድትወጣ ምክንያት ሆኗል፡፡ ትዳሯ ብዙ አልዘለቀም፡፡ በፍቺ ተለያይታ ብቸኛ ሆነች፡፡፡

ካሡች አደራ ትግራይ ውቅሮ ላይ ተወልዳ አድጋለች። በረጅሙ ዞማ ፀጉሯ በውብ መልኳና ቁመናዋ ብዙዎች ያደንቋታል፡፡ ታላቅ እህቷ ባሕር ማዶ ይመላለሱ ነበርና ለሠለጠነው ዓለም ወሬ ጆሮዋ አዲስ አይደለም፡፡ ባጋጣሚ የካሡች ታላቅ እህት በድንገት ሀገራቸውን ትተው፣ ወዳጅ ዘመድ ተሰናብተው ወደ ጅዳ በረሩ ፡፡

እህት አካሄዳቸው ለመመለስ አይደለም፡፡ ሙሉ ቤት ንብረታቸውን ለካሡች ሰጥተዋል፡፡ ቤት ጠባቂዋ ወጣት የዛኔ ከባሏ ተለያይታ ብቻዋን ነበረች፡፡ ይህ ግዜ በራሷ የምታዝበት፣ በሀሳቧ የምትጓዝበት ነፃነቷ ሆኗል፡፡ ከእጇ አንዳች ያጣችው የለም፡፡ በቂ ገንዘብና ትልቅ መኖሪያ ቤት የራሷ ነው፡፡ እንዲያም ሆኖ ልቧ አርቆ ያስባል፡፡ ባታጣ ባትነጣም ባለችበት መቀመጥን አትሻም፡፡ ብቸኝነት ብዙ እያሳሰበ አርቆ ይመልሳታል፡፡

አንድ ሰሞን ባልና ሚስት ጎረቤቶቿ አዲስ አበባ ለመሄድ መዘጋጀታቸውን ሰማች፡፡ ይህኔ ብዙ አሳቢዋ ካሡች የልቧ ሞላ፡፡ ለጥንዶቹ አብራቸው መጓዝ እንደምትፈልግ ነገረቻቸው፡፡ ባልና ሚስት በውሳኔዋ ቢገረሙም አልከለከሏትም፡፡ ከእነሱ ጋር እንድትሄድ ፈቀዱላት፡፡ አልዘገየችም፡፡ ፈጥና ጓዟን አነሳች፣ ቤቷን ዘግታ ቀልጠፍ ብላ ተከተለቻቸው፡፡

### የውቅሮዋ ቆንጆ በአዲስ አበባ

ግዜው የአፄ ኃይለሥላሴ ዘመን ነው፡፡ በወቅቱ ጥቂት በሚባሉት እጅ ብቻ ገንዘብና ንብረት ይገኛል፡፡ ሥልጣኔና፣ ዘመናዊነት እምብዛም ባልነበረበት በዛ ዘመን በርካቶች ለባሕልና ወግ ይገዛሉ፡፡ ጨዋነት፣ ሰው አክባሪነት ይሉት ጉዳይ ትርጉሙ ሰፊ ነው፡፡ በተለይ ሴቶች የዚህ እውነት ማሳያና መገለጫዎች ናቸው፡፡

እግሯ አዲስ አበባ የረገጠው ካሡች ከተማውን እንዳየች ተማረከች፡፡ ሀገሩን ወደደችው፡፡ ውላ ስታድር እንግድነቷ ተረሳ፡፡ ከብዙዎች ተግባባች፡፡ ይህኔ ፈጣን አዕምሮዋ አርቆ እያሰበ ብዙ አቀደች፡፡ አሁን በዚህ ስፍራ ራሷን የሚቀይር ሥራ መገኘት ሕልሟ ሆኗል፡፡ ይህን ዕውን ለማድረግ ዕንቅልፍ የላትም፡፡

አሁን ካሡች ካገሯ ያመጧት ሰዎች ከአንድ ሆቴል ሥራ አስገብተዋታል፡፡ ይህ አጋጣሚ የኑሮ መንገዷን እንድትለይ ምክንያት እየሆነ ነው፡፡ ጠንካራዋ ወጣት የሥራን ታላቅነት፣ ገንዘብ የማግኛውን ዘዴ አላጣችውም፡፡ ውሎዋ፣ ብዙ ቢያሳያት ስለነገዋ አሰበች፡፡ ራሷን ችላ የምትሠራበትን አጋጣሚ እያቀደች የገንዘብ አቅም ያዘች፡፡

### ራስን ፍለጋ...

ከጊዜያት በኋላ ካሡች ከሌሎች ዘንድ መቀጠር ይሉትን ትታ የራሷን ሥራ ጀመረች፡፡ ሀብተ ጊዮርጊስ ድልድይ አካባቢ የከፈተችው ቤት የብዙዎችን ዓይን ሳበ፡፡ በ‹‹መቀሌ›› በተባለው ቡናቤቷ በርካታ ደንበኞች ተመላለሱ፡፡ ገበያዋ ደራ፡፡ ከራሷ አልፋ ለሌሎች እንጀራ የከፈተችው ሴት በስሯ በርካታ ሠራተኞች ማስተዳደር ያዘች፡፡ ዓመታትን የዘለቀው ሥራዋ ከብዙዎች አስተዋውቆ አግባባት፣ ታዋቂ ሆነች፡፡ ጥሪት ቋጥራ በቂ ሀብት አፈራች፡፡

ውሎ አድሮ ሥራዋን የሚፈትን አጋጣሚ አላጣትም። ዓመታትን የሠራችበት አካባቢ ሊፈርስ መሆኑን ሰማች፡፡ ካሡች ለዚህ ችግር መፍትሔ አላጣችም፡፡ ስፍራውን ለቃ በሌላ ቦታ ተገኘች፡፡ ሥራ የጀመረችበት ቤት እንደ ቀድሞው የኪራይ አልነበረም፡፡ በጥሩ ዋጋ የገዛችው ታዋቂ ሆቴል እንጂ፡፡

‹‹ማሞ ካቻ›› ከተባሉት ታዋቂ ሰው የተገዛው ባለፎቁ ‹‹ሳሙኤል ሆቴል›› በአጭር ፍጥነት ሥራውን ጀመረ። ሆቴሉ ሰፊ መስተንግዶን ጨምሮ በርካታ ቤርጎዎች ነበሩት። መሐል ከተማ ላይ መሆኑ ደንበኞችን አላሳጣም። ዕለት በዕለት ገበያው ደራ፣ ሠራተኞች፣ ከላይ ታች የሚተራመሱበት ሆቴል ለውቧ ካሡች የሀብት ምንጭ ሊሆን አልዘገየም፡፡

ካሡች አሁን ታዋቂ ባለ ሆቴል ሆናለች፡፡ ‹‹ፔጆ›› መኪናዋን ይዛ ‹‹ሽር›› ስትል አላፊ አግዳሚው ይማረክባታል። ቅላጼዋ ውበት አለው፡፡ ትግርኛን ከአማርኛ ቀላቅላ ስታወራ አንደበቷ ይጣፍጣል፡፡ በዘመኑ በተለይ በሴቶች ዘንድ ያልተለመደው ሀብት ማፍራት በእሷ ዘንድ መሆኑ ለብዙዎች እያስደነቀ ነው፡፡ ቅልፍጥናዋ ይለያል፡፡ ያሰበችውን ከማድረግ ወደ ኋላ አትልም፡፡


ፎቶ፡- ገባቡ ገብሬ፤
እማማ ካሡች አደራ፣

ለሥራዋ ከወንዶች በላይ የምትሮጠው ካሡች በወቅቱ በገበያው የሚታወቀውን የሜታ ቢራ በገፍ በማስገባት የሚያህላት አልነበረም፡፡ በአካባቢዋ የሚፎካከሯትን እነ ‹‹አሥመራ ሆቴልን›› ልቃ ለመገኘት መኪናዋ ጉልበቷ ነበረች። ሁሌም የውስኪ አይነትና ልዩ መጠጦች ከእሷ ሆቴል ተጠይቆ አይጠፋም፡፡ ‹‹ሁሉ በእጇ ሁሉ በደጇ›› ነው፡፡

ኑሮዋ መሐል ቦሌ በገዛችው ቪላ ቤት ሆኗል፡ ካሡች ሰው ወዳድና እንግዳ ተቀባይ ናት፡፡ በየበዓላቱ ካህናትን ሰብስባ ታበላለች፤ ሁሌም ሰፊ እጇቿ ለመስጠት አይሰስቱም፡፡ ድሆችን ታስባለች፣ ላጡ ለነጡት ትቸራለች።

እረፍት አልባዋ ሴት ዛሬን አሸንፋ ከነገ ለመድረስ ሩጫዋ ፈጣን ነው፡፡ በሽንፈታቸው ሰበብ የሚያነውሯትን ሰምታቸው አታውቅም፡፡ ያለ እረፍት በጥንካሬ ትተጋለች። በሆቴሏ ምግብ መጠጡ ይሸጣል፡፡ የቤርጎው አልጋ ይከራያል፡፡ እንግዶች፣ ደንበኞች፣ ሠራተኞች ሲጋፉ የሚውሉበት ቦታ ታዋቂነቱ ጨምሯል፡፡

ካሡች የቦሌውን ቪላ አከራይታለች፡፡ አሁንም የሆቴል ሩጫዋ ቀጥሏል፡፡ የእሷ ኑሮ የግሏ ብቻ አይደለም። በርካታ ሠራተኞች ከእጇ በረከት ያገኛሉ፡፡ ቤቷ የታዋቂ ሰዎች መገኛ፣ የወጣት አዋቂው መናኸሪያ ነው፡፡ አሁን ካሡች በ1960 ዎቹ በአዲስ አበባ ከታዩት ብርቱ ሴቶች፣ ከታወቁ ባለ ሆቴሎች መሐል አንዷ ሆናለች፡፡ ወጣትነቷ ከቁንጅናዋ ተዳምሮ አድናቆት ይጎርፍላታል፡፡

### የአብዮቱ ፍንዳታ...

እነሆ! በመላው ሀገሪቱ የለውጡ ነፋስ ተዳርሷል። ንጉሡን ከዙፋናቸው ለማውረድ ያሰቡ ኃይሎች ጦር እየሰበቁ ነው ፡፡ በገጠር ከተማው የአብዮቱ ክንዶች በርትተዋል፡፡ ‹‹መሬት ላራሹ›› ያሉ፣ ‹‹መብታችን ይከበር›› የሚሉ፣ በደል ግፉ ይብቃን ከሚሉት ጋር ተዳምረው የለውጡ አካል ሆነዋል፡፡ ይህ ግዜ ለብዙዎች የልባቸውን ሀሳብ ሞልቷል፡፡ ለበርካቶች ማንነትም የበዛ ስጋት ሆኗል፡፡

ካሡች አሁንም ሥራ ላይ ናት፡፡ ከአብዮተኞች፣ ከለውጥ ፈላጊዎች ወገን አይደለችም፡፡ ሕይወቷ እንደቀድሞው ቀጥሏል፡፡ ቪላ ቤቷ እንደተከራየ ነው፡፡ ሆቴሏ ይሠራል፣ በመኪናዋ ካሡች ደርሳ፣ ካሰበችበት ትውላለች፡፡ ውሎ አድሮ ግን ሁኔታዎች እንደነበሩ አልቀጠሉም፡፡ እሷን በተለየ ዓይን የሚቃኟዋት በዙ፡፡ ቤቷን የሚፈትሹ በጥያቄ የሚያዋክቧት በረከቱ ፡፡

ከቀናት በአንዱ ካሡች ‹‹ለጥያቄ ትፈለጊያለሽ›› በሚል ከቤቷ ተወሰደች፡፡ የትግራይ ተወላጅ በመሆኗ በወቅቱ አጠራር /ለወንበዴዎች/ የስንቅ ድጋፍ እያደረገች ስለመሆኑ ተነገራት፡፡ የተወነጀለችበት ክስ ሐሰት መሆኑን ልታስረዳ ሞከረች፡፡ ሰሚ አላገኘችም፡፡

ጠያቂዎቿ ደርግን ለሚዋጉ ወንበዴዎች ድጋፍ ስለማድረጓና ማስረጃ ስለመገኘቱ አረጋገጡላት፡፡ ካሡች አቅም ጉልበት አጣች፣ የልቧን እውነት የውስጧን ሐቅ ለማሳየት ቃል አጠራት፡፡ መርማሪዎቹ አላዘኑላትም፡፡ እጇን ይዘው ወደ ወህኒ ወረወሯት፡፡ የአብዮቱ ለውጥ ያመጣው አጋጣሚ የቆንጆዋን፣ የባለሆቴሏን ሀብታም ሴት ታሪክ በአንዴ ቀያየረው፡፡

ካሡች ወህኒ ወርዳ ለእስር ስትዳረግ ስላፈራችው ሀብት ንብረት ያሰበ፣ የተጨነቀ አልነበረም፡፡ እሷም ብትሆን በቅርብ ለምታውቃቸው ሰዎች አደራ ከማለት ሌላ ምርጫ አልነበራትም፡፡ መቼ እንደምትፈታ ባታውቅም በአሳሪዎቿ የተፈረደባትን እስር ልትጀምረው ‹‹ከርቸሌ›› ወርዳለች፡፡

### ሕይወት በከርቸሌ ...

ካሡች ሳታስበው የገባችበት የእስር ሕይወት ታሪኳን ለውጧል፡፡ ትናንት ያለ ድካም የምትሮጠው ሴት ዛሬ ከዓላማ አልባ ኑሮ ላይ ቆማለች፡፡ ያለ ፍርድ የታሰረችበት ክስ ከሌሎች ጋር ደምሯታል፡፡ አብረዋት የንጉሣውያን ቤተሰቦች ታስረዋል፡፡

አንዳንዴ ከቤተመንግሥት ሰዎች ጋር መሆኗን ስታስብ በራሷ ትጽናናለች፡፡ ትካዜ ኃዘኗን ረስታ ‹‹ተመስገን›› ትላለች፡፡ አንዳንዴ ደግሞ የትናንቱን ከዛሬ አወዳድራ መጨረሻዋ ይናፍቃታል፡፡ የእስር ጊዜው በጨመረ ቁጥር በትካዜ ትዋጣለች፡፡ ያለፈችበት መንገድ የሰነቀችው ዓላማ፣ ያገኘችው ስኬት ሁሉ ውል ይላታል፡፡ አሁን ግን በዚህ ጎዳና ላይ አይደለችም፡፡ ታሪኳ ተቀይሯል፡፡ ሕይወቷ ተለውጧል።

ከካሡች ጋር የጃንሆይ ልጆች፣ የአልጋወራሽ ልዑል መኮንን ባለቤት፣ የሚኒስትሮቹ ሚስቶችና የታዋቂ ሰዎች ቤተሰቦች ታስረዋል፡፡ የጄኔራል አማን አምዶም እህት ወይዘሮ ጽዮንን ጨምሮ የራስ ሥዩም ሚስትም ከወህኒው ይገኛሉ፡፡ በእስርቤቱ የነበረው መተሳሰብ ይለያል፡፡ አንዱ ሌላውን የሚደግፈው በሙሉ ቅንነትና ፈቃደኝነት ነበር፡፡

ካሡች ሀብት ንብረቷን ትታ ወህኒ መግባቷን የሰሙት ታላቅ እህት ከነበሩበት ሀገር ተመልሰዋል፡፡ አመጣጣቸው ስለ እህታቸው ነበርና ያሻትን፣ የጎደላትን እያሟሉ ከጎኗ ቆመዋል፡፡ በወቅቱ ካሡች የእህቷን መመለስ ባየች ግዜ ከመደንገጥ በላይ አዝናለች፡፡ ‹‹ለምን መጣሽ›› ስትልም ሞግታለች፡፡ እሳቸው ግን እንደ ልጅ ያሳደጓት እናት ነበሩና ድካማቸውን አላዩም፡፡

እህት ስለ ካሡች ፍቅር የእጃቸውን ጥሪት አሟጠዋል። ወርቃቸውን ሳይቀር ሸጠዋል፡፡ ከእሳቸው በቀር ስንቅ የሚያመላልስ የቅርብ ሰው አልነበረም፡፡ ከካሡች ጋር ከሀያ ዓመት በላይ የኖረች ሠራተኛዋም አልካደቻትም፡፡

ካሡች የወህኒ ቆይታዋ ብዙ አሳይቷታል፡፡ የደግ ሰዎችን ውለታ አትረሳም፡፡ የክፉዎቹን ድርጊትም አዕምሮዋ መዝግቧል፡፡ ቤቷን በውክልና የያዘው አንድ አጎቷ ከታሰረች በኋላ በገንዘቧ አዟል፣ በሀብት ንብረቷ ተንቀባሯል፡፡ ለእሷ ቁራሽ ለማቀበል ግን ልቡ አይፈቅድም፡፡ ታማኟ ሠራተኛ ከእሱ እየተናጠቀች፣ ከሰዎች ዱቄት እየለመነች የዕለት ጉርሷን ታቀብላታለች ፡፡

### ሰንሰለቱ ሲበጠስ ...

ጊዜያት እንደዋዛ አልፈው ሰባት የእስር ዓመታት አንድ ሁለት ብለው ተቆጠሩ፡፡ ሰባቱ ፈታኝ ዓመታት፡፡ የሕይወት የኋልዮሽ ጉዞ ፣ የኑሮ ርምጃ እንቅፋት፣ የጽኑ ዓላማ ስብራት። እነዚህ እውነታዎች በጠንካራዋ ካሡች ማንነት ውስጥ ሲመላለሱ ኖረዋል፡፡ አሁን የትናንቷ ጠንካራ ካሡች ቆማ አትታይም፡፡ ዛሬ ላይ ብዙ ታሪኮች ተቀይረዋል፡፡ የስኬት የሕልም ድልድዮቿ ተሰባብረዋል፡፡

ከሰባት ዓመታት የአስር ቆይታ በኋላ ካሡችና አብረዋት የታሰሩት አንዳንዶች ከወህኒ ቤት በነፃ ተሰናበቱ፡፡ እሷ በተፈታች ግዜ ውስጧ በድብልቅልቅ ስሜት ተዋጠ፡፡ ዛሬ ሌላ ሰው ሆናለች፡፡ እንደቀድሞው በራስ የመተማመን ማንነቷ ከእሷ የለም፡፡ ያለፍርድ ዓመታትን የገፋችው ሴት ግን ‹‹ነፃ ›› ተብላለች፡፡

ካሡች ከእስር መፈታቷ በኋላ ወደ ትናንቱ ሆቴሏ ተመለሰች፡፡ ግቢዋ በደረሰች ግዜ ‹‹እንኳን ተፈታሽ›› ያሉ ወዳጆቿ በአክብሮት ተቀበሏት፡፡ ቀናት አልፈው ቀናት ተተኩ፡፡ እንግዳው ጋብ ሲል ወደ ጓዳዋ ገብታ ያለውን ከጎደለው ቃኘች፡፡ አጎቷን አስጠርታም ስለሰጠችው አደራ ጠየቀች፡፡ ያገኘችው ምላሽ አስደንጋጭ ነበር፡፡

አጎት ለሰባት ዓመታት በሆቴሉ ገቢ ሲጠቀም ኖሯል፡፡ የሚጠበቀውን ግብር ግን በወጉ አልከፈለም፡፡ በየአጋጣሚው ቤቱን በብድር እያስያዘ ዕዳ ሲያስቆጥርበት ነበር፡፡ ይህን ሁሉ የማታውቀው ካሡች ከቤቷ ተመልሳለች። ብዙ ያልዳኑ ችግሮቿ ከፊቷ ናቸው፡፡ እነሱን በወጉ አክሞ ነፍስ ለመዝራት አጋር ትሻለች፡፡ ከሰባት ዓመታት በኋላ ሕይወትን በአዲስ መጀምሩ ይከብዳል፡፡ ብዙ የጠፉ፣ የተበላሹ፣ የጎደሉ ጉዳዮች አሉ፡፡ ካሡች ያለፉትን ዓመታት በወህኒ ማሳለፏን ለበጎ ቆጥራዋለች፡፡ ዘመኑ ቀይ ሽብር የተፋፋመበት ነበርና አጋጣሚውን ለማምለጥ አግዟታል፡፡

ካሡች ጊዜ ወስዳ ቤት ግቢዋን ቃኘች፡፡ ቤቱ እንደፊቱ ሙሉ አይደለም፡፡ ብዙ ሀብቷ ባክኗል፡፡ የሞላቸው ጎድሏል፡፡ የሚያምረው ሕንጻ አርጅቶ ተጎሳቁሏል፡፡ ይህን ስታይ ውስጧ አዘነ፡፡ በላብ በወዟ ያፈራችው ንብረት ባክኖ መቅረቱ አስከፋት፡፡ በአደራ የተቀበለው አጎት እንደቃሉ አልተገኘም፡፡ ይህ ሁሉ እውነት ለካሡች ከባድ ሆኖ ከረመ።

### ሴሳው መርዶ...

አንድ ቀን የሀገር ውስጥ ገቢ ሰዎች ከሆቴሏ ደረሱ። አመጣጣቸው ለበጎ አልሆነም፡፡ ሆቴሉ የዓመታት ዕዳ እንዳለበት ዘርዝረው ነገሯት፡፡ የሰማችውን አላመነችም። በወቅቱ ዕዳዋን ከፍላ ከችግሩ ማምለጥ አልተቻላትም። ዓይኗ እያየ ብዙ የለፋችበት ፣ልጅነቷን የከፈለችበት ሆቴሏ በሐራጅ ተሸጠ፡፡

አሁን የካሡች ታሪክ ተቀይሯል፡፡ ከእስር መፈታት ማግስት የሆነባትን ሁሉ ማመን ባትችልም ተቀብላዋለች። አሳዳጊ ጠያቂ እህቷን ቀብራለች፡፡ አግኝታ አጥታለች፡፡ ከዚህ በኋላ ያላት ተስፋ መሐል ቦሌ ላይ የሠራችው ቪላ ብቻ ነው፡፡ ይህን ቤት ከመታሰሯ በፊት ለአንዲት ሴት አከራይተዋለች፡፡

አካባቢው ስትደርስ የተመለከቷት ሁሉ ተገረሙ፡፡ አብዛኛው መሞቷን እንጂ በሕይወት መኖሯን አያውቅም፡ ከግቢው ደርሳ ወይዘሮዋን አናገረች፡፡ ቤቱን ልትኖርበት መሆኑን ተናግራም እንዲለቀቅላት በትህትና ጠየቀች፡፡ ይህን የሰማችው ሴት የካሡችን ቃል አልተቀበለችም፡፡ ቤቱ የእሷ ባለመሆኑ እንደማትለቅ ነገረቻት፡፡

ካሡች ለምን? ማለቷ አልቀረም፡፡ ተከራይዋ ቤቱን የሰጣት ደርግ እንጂ እሷ እንዳልሆነች ተናግራ ከደጅ መለሰቻት፡፡ ሴትየዋ በሽማግሌ ተጠየቀች፡፡ ‹‹እምቢኝ አሻፈረኝ›› አለች፡፡ የነበረው እንዳልነበረ የሆነባት ሴት ቤቷን ለማስመለስ ጠበቃ አቁማ ፍርድቤት ተመላለሰች። ዓመታት የፈጀው ክርክር የቤቱን ባለቤትነት ለካሡች ሲወስን ንብረቷን ተረከበች፡፡ ቤቱ በትናንት አቋሙ አይደለም፡፡ ብዙ ጎድሎበታል፡፡ እንዲያም ሆኖ ዘመናዊነቱ ዓይን ይስባል፡፡

በወቅቱ ካሡችን የሚዞሯት አንዳንዶች ቤቱን ብትሸጠው እንደምትጠቀም አሳመኗት፡፡ ‹‹እምቢ›› አላለችም፡፡ የወደፊቱን አስባ ለገበያ አቀረበችው፡፡ ግዜው ደርሶ ሲሸጥ ግን አንዲት ሳንቲም ከእጇ አልገባም። የቀረቧት የዋህነቷን አይተው አታለሏት፡፡ ከዚህ በኋላ በቀላሉ የማይነገሩ የችግር፣ የመከራ፣ የመራብ ዓመታት አለፉ፡፡

### እማማ ካሡች...

የወደቁትን አንሱ የነዳያን መርጃ ማዕከል ተገኘቻለሁ። ዓይኖቹ አንዲት ቀጭን አዛውንት ላይ አርፏል። ልግባባቸው አልቸገረኝም፡፡ ሴትዬዋ ቀልጣፋና ንቁ ናቸው። ልብሳቸው ፀዓዳ ነው፡፡ በትግርኛ ቋንቋ የተዋዛው አንደበታቸው ይጣፍጣል፡፡ ዕድሜያቸው ዘጠና መሙላቱን ነግረውኛል። እማማ ካሡችን ጠጋ ብዬ አስተዋልኳቸው። ዕድሜ የተሻገረው ቁንጅናቸው አሻራው እንዳለ ነው፡፡ ጥርሶቻቸው በወጉ አልታዩኝም፡፡ በቦታው ስለመኖራቸው ተጠራጠርኩ፡፡

እማማ ካሡች እርጅና ተጭኗቸዋል፡፡ እግርና ወገባቸው ጤና ውሎ አያድርም፡፡ በዚህ ስፍራ የተገኙት ጧሪና ረዳት በማጣታቸው ነው፡፡ ያለፉባቸውን ክፉ ደግ አጋጣሚዎች በትዝታ ከማውሳት በቀር ፈጽሞ አያማርሩም፡፡ ፊታቸው ሳቅ ፈገግታ ሞልቶታል ፡፡

እማማ ሁሌም ፈጣሪንና ሰዎችን አመስጋኝ ናቸው። ሕይወት ማለት በእሳቸው ማንነት እንዲህ ተገልጧል። ካሡች ዝቅ ብሎ መነሳት፣ ከፍ ብሎ መውደቅ መኖሩን አሳይተውናል ፡፡ የትናንቷ ሀብታምና ቆንጆ ዝነኛ ባለታሪክ የዛሬዋ ተመጽዋች አዛውንት እማማ ካሡች አደራ ፡፡

# ነፃ ሃሳብ

# ሕጋዊ የፖለቲካ ሥርዓት ተከትሎ ስልጣን መያዝ ለፖለቲካ ስብራቶቻችን ፈውስ ነው

## ታሪኩ ዘለቀ

ሰላም ሉአላዊነቱ የተረጋገጠ ሀገር ሕዝባዊ ህልውናው ይቀጥል ዘንድ መሰረቱን ሊያፀናበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች ለሰላም ረብ የለሽ ዋጋ ሲሰጡ የተመለከትናቸው የትኞቹም ሀገራት ሲፈርሱ እንጂ ሲፀኑ አልሰማንም፤ ደግሞም አላየንም። በታሪክ ግን ውስጣዊ የሰላም ያለመረጋጋት ጉዳዮቻቸውን በጠረጴዛ ዙሪያ ለመፍታት ሲጥሩ የታዘብናቸው ሀገራት ከፈተናዎቻቸው በላይ ሆነው ህልውናቸው ዛሬም ድረስ ቀጥሏል፡፡

እኛ ኢትዮጵያዊያን ስለሰላም ስናወራ፣ የሰላምን አስፈላጊነት በትምህርት ቤት ስለተማርነው፣ ሰዎች ስለነገሩን ወይም ቃሉን ብቻ ስላወቅነው አይደለም፤ የሰላምን አስፈላጊነት ከየትኛውም ሀገር ሕዝቦች ይልቅ በተግባር ስለምናውቀው ነው፡፡ ባለሙያዎች እንደሚሉት አንዳንድ ሃሳቦች በቀጥታ ከሚተረጎሙ ይልቅ በተቃርኖ ሲተረጎሙ ትርጉማቸው በቀላሉ ይገባል፡፡ ለምሳሌ ሰላም ማለት ምን ማለት ነው? ከማለት ይልቅ ሰላም ማለት ምን ማለት አይደለም? ቢባል የበለጠ ይገባናል፡፡

ከታሪኳ ከግማሽ በላይ የጦርነት ታሪክ በሆነባት ሀገር፣ ጀግና ሲባል እንኳ የጦር ሜዳ ጀብዱ ብቻ የሚታሰብባት ሀገር፣ የውጪው ሲለቃት የእርስ በርሱ፣ ይህም ጋብ ሲል የውጪው የሚፈራረቁባት ሀገር፣ ጦርነት ከስልጣኔ ማማ አውርዶ ወደ ድህነት አዘቅት ለወረወራት ሀገር ስለ ሰላም መካሪም አስተማሪም አያስፈልገውም፡፡ የቅርብ ጊዜ ታሪካችን እንኳ ይህንን ይነግረናል፡፡ የአርባና የሃምሳ ዓመታት ታሪካችንን መለስ ብለን ብንቃኝ ከአራትና አምስት ታላላቅ ጦርነቶች በላይ አካሂደናል፡፡

ጦርነቱ የእርስበርስ ሲሆን ደግሞ ክፋቱም ጥፋቱም እጅግ የከፋ ነው፡፡ በዚህም በዚያም ወገን የሚጎዳው የሚሞተውም የራስ ወገን ነው፡፡ የዓለም መገናኛ ብዙኃን ከዩክሬኑ ጦርነት እጅግ የከፋ ውድመትና እልቂት የደረሰበት ነው ያሉት የሰሜኑ ጦርነት በመቶ ሺህዎችን አሳጥቶን ከ20 ቢሊዮን ዶላር በላይ አውድሞብን ገፅታችንን አጠልሽቶት የዘወትር ጠላቶቻችንን አሰባስቦብን በመጨረሻ የተቋጨው ግን በንግግር፣ በድርድር፣ በሰላም ስምምነት/በፕሪቶሪያ የሰላም ስምምነት ነው፡፡

መጨረሻው ይሄ ሊሆን ካወደመው በላይ ቅራኔ ፈጥሮ ፤ቁርሾን ተክሎ ባይሄድ ምን ነበረበት ያስብላል። በዚያ ጦርነት የሞተው ራሱ ብቻ ሳይሆን የተጎዳው ቤተሰቡ ቢቆጠር ለማገገም ዓመታት ያስፈልገዋል፡፡ የተተከለው እሾህ፣ የተረጨው መርዝ፣ የቆሰለው ልብ ለማገገም ዓመታት ያስፈልጉታል፡፡

እንደነአውጎስጢኒዎስ ያሉ ሊቃውንት ተገቢ የሆነ ጦርነትና ተገቢ ያልሆነ ጦርነት /ጀስቲስ ዋር እና አንጀስቲስ ዋር/ እያሉ ለሁለቱም ተገቢውን ትርጉም ይሰጣሉ፡፡ በሀገር ህልውና በህዝብ የመኖርና ያለመኖር ላይ የሚነሳ ጦርነትን መከላከል አስፈላጊ እንደሆነ ያሰምሩበታልና ግቡና አላማው ግን መጠፋፋት እንዳልሆነ ጦርነት አንሺውም ይሁን ተከላካዩ ክፍል እስከገባቸውና ለመነጋገር ዝግጁ እስከሆኑ ድረስ ለሰላም ቦታ መስጠት አስፈላጊነቱን ላይ ይደመድማሉ፡፡

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ባህል ከሃሳብ የበላይነት ይልቅ በግጭት እና የእርስበርስ ጦርነት ውስጥ ማለፍን ምርጫው ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ ይህ ጉዞ በሀገራችን ታሪክ ውስጥም በርካታ ጊዜያት ተደጋግሞ ተመልክተነዋል። አሁን በምንገኝበት የዘመናዊ የፖለቲካ ሂደታችን ውስጥም ካለፈው ባልተማረ መልኩ ግጭት ላይ ሙጥኝ እንዳለ አለ፡፡

ለጉዞው በዚህ ደረጃ መውረድ ባለሙያዎች የፖለቲካው መንገድ አለመቀየሩን እንደችግር ሲያነሱ ፤ሌሎች ደግሞ ለአካሄዱ በተዋንያኖች በኩል የሚሰጠው ቦታ ራስን ብቻ የተመለከተ ሆኖ መዝለቅን ምክንያት ያደርጋሉ፤ ዞሮ ዞሮ ኃይልን/ ጠበመንጃን መፍትሄ አድርገው መሄዳቸው ሀገርና ሕዝብም ያልተገባ ዋጋ እያስከፈለ ነው፡፡

በርግጥ ባለንበት በ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኃይልና በጦር መሳሪያ ስልጣን ለመያዝ ማሰብም ሆነ መመኘትም ዘመኑን የሚዋጅ እሳቤ እንዳልሆነ የአደባባይ ምስጢር ነው። በጦር መሳሪያ ወይም በኃይል የሚደረግ የስልጣን መሻት ወይም ስልጣን ለመያዝ የሚደረግ ማንኛውም ሙከራ ተገቢ አይደለም።

ለዚህ ደግሞ በዋናነት መቀየር ያለበት የራስ አስተሳሰብ ነው ፤ እዚህ ላይ መስራት ደግሞ ከፖለቲካ ከተዋንያኖቻችን የሚጠበቅ ትልቁ ኃላፊነት ነው። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ከዚህ አንፃር መንግሥታቸው ለሰላማዊ የሀገር ጉዞና ለዜጎች መስተጋብር በጋራ ለመስራት ከተቃራኒ ኃይላት ጋር ዝግጁ መሆናቸውን ደጋግመው ተናግረዋል፡፡ በተለይ ደግሞ አፈሙዞቻቸውን ካነሱ አካላት ጋር የተጀመሩ ንግግሮች እንዲቀጥሉ ዛሬም በመንግስት በኩል ተነሳሽነቱ እንዳለ ገልጸዋል።

ግጭትና ጦርነት የሕዝብ ሀብትና ንብረት ከማውደም ባለፈ ለሀገርም ሆነ ለሕዝብ የሚያመጣው ትሩፋት የለም። ያለፍንባቸው የግጭት ዓመታትም ይህን በሚገባ አሳይተውናል፡፡ ብዙ ወንድሞቻችንን አሳጥተውናል ፣ አካለ ጎዶሎ አድርገውብናል፣ በቢሊዮን የሚቆጠር ሀብት አውድመውብናል።

መነጋገር የሰለጠነ ማህበረሰብ መገለጫው ሲሆን፤ የተፈጠሩ ቁርሾዎችም በቀላሉ የሚፈቱበት መንገድ ቀና ሲሆኑ ተመልክተናል። ሰላም የሁሉ መሰረት ነው። በእያንዳንዱ የሀገር ጉዞ ውስጥ ከቃል በላይ የሆነው የሰላም ሂደት ቁልፉን ሚና ይጫወታል፡፡ እኛም ብንሆን ተግባርና አካሄዳችንን መዳረሻ አድርገን ካስቀመጥነው ግብ ጋር ማስላት ይኖርብናል። ለመደራደር የመነጋገሪያ ነጥቦቻችን ሁሉንም ማህበረሰብ የሚወክሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

ተዋናይ አካላት የኢትዮጵያ ህዝብ የጦርነት፣የመፈናቀል፣የሰቆቃ ህይወት ይበቃዋል ብለው ሊያስቡ ይገባል፡፡ ከምንም በላይ ከራሳቸው የጥቅም ፍላጎት ይልቅ የህዝባቸውን መፈናቀል፣ መሰደድ፣ መንከራተት፣ መሞት ከግምት በማስገባት ህዝባቸውን ይቅርታ በመጠየቅ፣ ለህዝባቸውና ለሀገራቸው በማሰብ በተረጋጋ መንፈስ በመደራደር በመነጋገር ህጋዊ የሆነ የፖለቲካ ስርአትን በመከተል ስልጣን መያዝ እንደሚቻል ማመን ይኖርባቸዋል፡፡

ጦርነት የሀገርን ኢኮኖሚ የሚያደቅ ሰላምንና መረጋጋትን የማያመጣ ነው፡፡ ስለዚህ በተቻለ መጠን በዚች ሀገር የዴሞክራሲ ሥርዓት የሚያብብበትን፣ የውይይት ባህል የሚለመድበትን መንገድ መከተል ይገባል። ይህንን ማድረግ ካልቻልን ዘላቂ ሰላም ማምጣትና የሕዝባችንን የልማት መሻት ማሟላት የሚታሰብ አይሆንም፡፡

> **መነጋገር የሰለጠነ ማህበረሰብ መገለጫው ሲሆን፤ የተፈጠሩ ቁርሾዎችም በቀላሉ የሚፈቱበት መንገድ ቀና ሲሆኑ ተመልክተናል። ሰላም የሁሉ መሰረት ነው።**

በእርግጥ በተለያዩ ወቅቶች መንግሥት ለሰላም ዝግጁ መሆኑንና ግማሽ መንገድ ሄዶ ለሰላም እንደሚሠራ እየተነገረ ይገኛል። ትጥቅ ይዘው ከሚንቀሳቀሱ ኃይሎች ጋር ጉዳዮችን በሰላም ለመፍታት ዝግጁ መሆኑንም አስታውቋል። ከሰሞኑ የብልፅግና ፓርቲ ባወጣው መግለጫ ይሄንኑ የሰላም አማራጭ እንደሚገፋበት መግለፁም ይታወሳል፡፡ ይህን መልካም አጋጣሚ የታጠቁ ኃይሎች ሊጠቀሙበት ይገባል፡፡

ኢትዮጵያ በአሁኑ ሰአት እንደሀገር ከገባችበት የሰላም መደፍረስ ችግር ለመውጣት መንግሥት ቀዳሚውን ተነሳሽነት በሰላም ዙሪያ ሲወስድ እየተመለከትን ነው። መንግሥት ወደ ንግግር መምጣቱ ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ በትጥቅ ትግል የሚገኝ ድል አይኖርም፡፡ ይገኛል ብሎ ማሰብ ሀገርና ሕዝብን ወደ ከፋ እልቂት ከመምራት ባለፈ ትርጉም አይኖረውም።

የሰላምን ዋጋ የተረዳ ማህበረሰብ ለቅፅበት አንድነቱን የሚያጠናክርለትን ይህንን የተረጋጋ ስነምህዳር ከእጁ እንዲወጣበት አይሻም፡፡ በዚህ ረገድ ውስጣዊ ችግራችንን በራሳችን አቅም ለመፍታት የሚደረጉ ጥረቶች የሚበረታቱ ናቸው፡፡ በቅርብ ጊዜም ሆነ ቀደም ባሉት ጊዜያት እየተደረጉ ያሉት የሰላም አማራጭ መድረኮች ዘላቂ ሰላም ለማምጣት መልካም መንገዶች ናቸው፡፡

መንግሥት እየሄደበት ያለው የሰላም አማራጭ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ሊያጤኑትና ሊከተሉት የሚገባ ነው፡፡ ሀገርን ከማስቀጠል አንፃር ቅድሚያውን ወስዶ ለውይይት የሚቀርብ የትኛውም አካል ይበረታታል፡፡ አብዛኞቹ ችግሮቻችን የመነጩት በቅርብ ጊዜ ሳይሆን ሲንከባለሉ የመጡ ናቸው፡፡ በመሆኑም በቀላሉ የሚፈቱ ባለመሆናቸው ቁጭ ብሎ መወያየትን፣መነጋገርን ይጠይቃሉ፡፡

ማንኛውም ኃላፊነት ያለበት አካል ስለሀገሪቱ የሚመለከተው የተሻለችና ለሁሉም ዜጎቿ ምቹ የሆነች ሀገር ለመፍጠር የበኩሉን ሊያደርግ ይገባል፡፡ ይህንን ለማሳካት የሚደረግ ውይይት ከአስፈላጊ በላይ ነው፡፡ ትርጉሙም የሀገርን የወደፊት እጣ ፈንታ የመወሰን ያህል አቅም ያለው ነው።ይህ የሰላም አማራጭ ውጤታማ የሚሆነው ግን በሰላም መድረኩ ላይ የሚገኙት አካላት ተገቢውን ፍላጎትና ጥረት ሲያደርጉ ነው፡፡

ዛሬም ቢሆን ነገ ሀገራችን ሰላሟ ተረጋግጦ እንዲቀጥል፤ ሰላምን መሰረት ያደረጉ የውይይት መድረኮች መተኪያ የማይገኝላቸው አማራጮቻችን ናቸው፡፡ ጡንቻ መፈታተን በየዘመኑ ካስከፈለን ዋጋ አንጻር በችግሮቻችን ዙሪያ በሰከነ መንፈስ ቁጭ ብለን መነጋገር ግዴታችን ነው።

በቀላሉ የሚፈቱ ችግሮች ላይ ነዳጅ በመጨመር የሚያቀጣጥሉ በዙሪያችን ባሉ ጠላቶቿ ሁኔታ ሁላችንም ብልህ ካልሆንን ጦርነቱ ግጭቱ ሁሉንም ይዞ የሚጠፋ ነው፡፡ በብዙ መስዋእትነት አባቶቻችን ያስረከቡንን ውዲቷን ሀገራችንን ሊያሳጣን እንደሚችል መዘንጋት የዋህነት ነው፤ጥልቅ አለማወቅ ጭምር።

በቀደመው የአሸናፊ ተሸናፊ ትርክት የምንሻገረው ችግር የለም፤ ከዚህ ይልቅ የተዘረጉ የሰላም እጆችን ተቀብሎ፣ የተነሱለትን አላማ በድርድርና በንግግር ማሳካት ብልህነት ብቻ ሳይሆን ቅድስናም ጭምር ነው፡፡ ነባር ቁስልንም የሚሽር ነው፡፡

# ስፖርት




## የአፍሪካ ሀገር አቋራጭ ሻምፒዮና ከአራት ዓመት በኋላ ነገ ይካሄዳል

ብርሃን ፈይሳ

የአፍሪካ ሀገር አቋራጭ ሻምፒዮና ነገ በሰሜን አፍሪካዊቷ አገር ቱኒዚያ አዘጋጅነት ይካሄዳል፡፡ ከአራት ዓመታት መቋረጥ በኋላ ዘንድሮ ለ6ኛ ጊዜ ለሚደረገው ውድድር ቱኒዝያ መሰናዶዋን አጠናቃ ባለፉት ቀናት እንግዶቿን ተቀብላለች፡፡ በዚህ ሻምፒዮና ላይ ኢትዮጵያን ጨምሮ የተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት የሚካፈሉ ሲሆን፤ በመጪው ወር መጨረሻ ለሚካሄደው የዓለም አገር አቋራጭ ሻምፒዮና ከወዲሁ ራሳቸውን የሚፈትሹበት ፉክክር ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

ኢትዮጵያ ይህንን ውድድር ጨምሮ ለዓለም አቀፉ የሀገር አቋራጭ ሻምፒዮና የሚወክሏትን አትሌቶች ባለፈው ጥር/2016 ዓም በተካሄደው የጃንሜዳ አገር አቋራጭ ኢንተርናሽናል ውድድር ላይ መርጣለች፡፡ በዚህም መሠረት በ14 ሴቶች በ14 ወንዶች በአጠቃላይ በ28 አትሌቶች ትወከላለች ። በዚህ ውድድር ላይም ከ20 ዓመት በታች በሴቶች 6ኪሎ ሜትር እና በወንዶች 8ኪሎ ሜትር፣ በአዋቂዎች 10ኪሎ ሜትር ወንድና ሴት እንዲሁም በድብልቅ ሪሌ አትሌቶቿን የምታሳትፍ ይሆናል፡፡

ለዚህም ቡድኑ ዝግጅቱን ከየካቲት 8 ቀን 2016 ዓም አንስቶ ለገጣፎ ለገዳዲ በሚገኘው ስለሺ ስኅን ሆቴል ተሰባስቦ ሲያካሂድ ቆይቶ ከትናንት በስቲያ ሌሊት ወደ ሰሜን አፍሪካዊቷ ሀገር አቅንቷል፡፡

ብሔራዊ ቡድኑ በለገጣፎ እንዲሁም በሱሉልታ አካባቢዎች ሲያደርግ የቆየውን ዝግጅት መጠናቀቅ ተከትሎ ፌዴሬሽኑ ከትናንት በስቲያ የሽኝት መርሐ ግብር አድርጓል፡፡ በሽኝት መርሐ ግብሩ ላይ



በውድድሩ የሚሳተፈው የኢትዮጵያ ቡድን ከትናንት በስቲያ ሽኝት ተደርጎለታል፣

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ረዳት ኮሚሽነር ደራርቱ ቱሉ ለብሔራዊ ቡድኑ ‹‹ሁላችሁም በመተጋገዝ፣ ለጋራ ድል በአንድነት ኢትዮጵያን የምትወክሉ አትሌቶቻችን፤ የምንወዳትን የሀገራችንን ሰንደቅ ዓላማ በዓለም አደባባይ በማውለብለብ የበኩላችሁን እንድትወጡ አደራ›› በማለት መልዕክቷን አስተላልፋለች፡፡

በኢፌዴሪ ባሕልና ስፖርት ሚኒስቴር የስፖርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር መስፍን ቸርነት፣ የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ተወካዮች እንዲሁም የፌዴሬሽኑ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትም በሽኝት መርሐግብሩ ላይ በመገኘት አትሌቶችን አበረታተዋል፡፡

በዚህ ውድድር ላይ የተካፈሉ አትሌቶች በዘንድሮው የጃንሜዳው አገር አቋራጭ ሻምፒዮና ተሳትፈው ውጤት ያስመዘገቡ ሲሆኑ፤ በመጪው ወር በሰርቢያ ቤልግሬድ በሚደረገው የዓለም አገር አቋራጭ ሻምፒዮና ላይ በድጋሚ ኢትዮጵያን ወክለው የሚሳተፉም ይሆናል፡፡

በአፍሪካ አትሌቲክስ ኮንፌዴሬሽን አዘጋጅነት የሚደረገው ይህ ውድድር በየሁለት ዓመቱ የሚካሄድ ቢሆንም ላለፉት አራት ዓመታት ተቋርጦ ቆይቷል፡፡ እአአ በ1985 ለመጀመሪያ ጊዜ በኬንያ የተካሄደው ይህ ውድድር ከዚያ በኋላ መቀጠል ባለመቻሉ ለዓመታት ሳይካሄድ ቆይቷል፡፡ እአአ በ2011 በደቡብ አፍሪካ አዘጋጅነት በድጋሚ ቢጀመርም በድጋሚ ተቋርጦ ዘንድሮ ዳግም ይካሄዳል፡፡

ኮንፌዴሬሽኑ በተለያዩ ችግሮች ሻምፒዮናውን በተከታታይ ለማዘጋጀት አዳጋች ቢሆንበትም እንደ ኬንያ እና ኢትዮጵያ ያሉ ሀገራት ግን በየዓመቱ ሌሎች ጎረቤት ሀገራትን ጭምር የሚያሳትፍ የሀገር አቋራጭ ውድድሮችን ያከናውናሉ፡፡

ነገ ለስድስተኛ ጊዜ ሰሜን አፍሪካዊቷ አገር ቱኒዚያ በምታዘጋጀው ሻምፒዮናም ኢትዮጵያን ጨምሮ 12 ሃገራት ተሳታፊ ሲሆኑ፤ አዘጋጇን ሀገር ጨምሮ ኢትዮጵያ፣ አልጄሪያ፣ ሞሮኮ፣ ሊቢያ፣ ኬንያ፣ አንጎላ፣ ሲሼልስ፣ ላይቤሪያ፣ ኮንጎ፣ ኬፕቨርዴ እና ዑጋንዳ ተፎካካሪ ይሆናሉ፡፡ በርቀቱ ለረጅም ዓመታት ውጤታማ ሆነው የዘለቁት የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት ዘንድሮም ውጤታማ እንደሚሆኑ ይጠበቃል፡፡ በተለይ በዚህ ርቀት ከአህጉር አልፈው በዓለም አቀፍ ደረጃ ተፅዕኖ ፈጣሪ የሆኑት የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት ኢትዮጵያ፣ ኬንያ እና ዑጋንዳ አትሌቶች የተዘጋጁት ሜዳሊያዎች ባለቤት እንደሚሆኑም ይጠበቃል፡፡ በዚህ ሻምፒዮና በርካታ ሜዳሊያዎችን በመሰብሰብ ኬንያ ቀዳሚ ስትሆን እአአ በ2018 ኢትዮጵያ በድብልቅ ሪሌ (ዱላ ቅብብል) አሸናፊ ነበረች፡፡